የዘራፊው ቡድን መጨረሻ
ገጽ 10

ሕዳር እና ፅዳት
ገጽ 11

የአየር መንገዱ የስኬት በረራዎች
ገጽ 13



# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

83ኛ ዓመት ቁጥር 075 ኅዳር 15 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# የማዕድን ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገት አይተኬ ሚና እየተጫወተ ነው


ሄለን ወንድምነው


አዲስ አበባ፡- የማዕድን ዘርፉ ለኢኮኖሚ እድገት አይተኬ ሚና እየተጫወተ መሆኑን የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚሊኒየም አዳራሽ የተዘጋጀውን ሁለተኛውን ዓለም አቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ትናንትና መርቀው ከፍተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በዚሁ ወቅት ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ ያለንን የማዕድን ሀብት በአግባቡ ማወቅና መጠቀም ከቻልን ለሀገሪቱ የብልጽግና ጉዞ መሠረት መጣል ይቻላል።

መንግሥት ለሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ትኩረት


የማዕድን ዘርፉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# በዓመት ከ8 ሺ በላይ ዜጎች በኤች አይ.ቪ ቫይረስ ይያዛሉ


ራስወርቅ ሙሉጌታ


አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በዓመት 8 ሺ 257 ሰዎች በቫይረሱ እንደሚያዙና 11 ሺ 300 የሚደርሱ ሰዎች በኤድስ እንደሚሞቱ ጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የኤች አይቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ የዘርፈ ብዙ የኤይ. አይ.ቪ. ምላሽ ዴስክ ሃላፊ አቶ ሀብታሙ ካሳ በተለይ ለኢፕድ እንደተናገሩት በኢትዮጵያ በዓመት 8 ሺ 257 ሰዎች በቫይረሱ ይያዛሉ። ከእነዚህም ውስጥ ሰባ በመቶውን የሚይዙት እድሜያቸው ከሰላሳ ዓመት በታች መሆናውን ጠቁመዋል። በተለይ እድሜአቸው ከ15 እስከ ሃያ ዓመት የሆናቸው አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙ


በዓመት ከ8 ሺ በላይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# የገበያ ማዕከላቱ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ምንድነው?


ማርቆስ በላይ


የዋጋ ንረትንና የምርት አቅርቦት እጥረትን ለመቅረፍ የገበያ ማዕከላትን የማስፋፋት ሥራ ልዩ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ መሆኑን በርካቶች ይስማሙበታል። የገበያ ማዕከላትን ማስፋፋቱ በተለይም አምራቹን ከሸማቹ ማህበረሰብ በቀጥታ በማገናኘት ጥራት ያለው ምርት ከማቅረብ ባሻገር የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት እንደሚያስችል በዘርፉ የተሰማሩ ምሁራን ይናገራሉ።

በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህሩ ፍሬዘር ጥላሁን ፤ በመዲናዋ የተገነቡትና በመገንባት ላይ የሚገኙት የግብርና ምርት መሸጫ ማዕከላት ለገበሬውና ለተጠቃሚው ማህበረሰብ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ


የገበያ ማዕከላቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




በኮልፌ ክ/ከ የተገነባው የግብርና ምርት ማከማቻና መሸጫ ማዕከል

# በኢትዮጵያ ከ168 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ስደተኞች የትምህርት እድል ተሰጥቷል


ሳሙኤል ወንደሰን


አዲስ አበባ፡- ከ168 ሺህ በላይ ስደተኞች በኢትዮጵያ የትምህርት እድል እንዲያገኙ መደረጉን ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትምህርት ሚኒስቴር የስደተኛ ትምህርት መርሃ-ግብር ከፍተኛ የኮሚዩኒኬሽን ባለሙያ እንግሊዝ ከተማ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ትምህርት ሚኒስቴር ከግብረ-ሰናይና ልማታዊ ድርጅቶች ጋር


በኢትዮጵያ ከ168 ሺህ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል










ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ

# ሀገራዊ ምክክሩ ኢትዮጵያ ታሪኳን የምትገነባበትን አጋጣሚ ይፈጥራል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክር ሰፊ ጊዜ የሚወስድና አንዴ ተደርጎ የሚቆም ባይሆንም ኢትዮጵያ ታሪኳን የምትገነባበትን አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑን የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ ገለጹ።

የሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ ለመገናኛ ብዙኃን እንደገለጹት፤ ሀገራዊ ምክክር ሰፊ ጊዜ የሚወስድና አንዴ ተደርጎ የሚቆም ነገር ባይሆንም ኢትዮጵያ ታሪኳን የምትገነባበትን አጋጣሚ የሚፈጥር ነው።

በመሆኑም በሚደረገው ሀገራዊ ምክክር ላይ ምክክር ባህል ሆኖ እንዲቀጥል መሠረት ተክለን ልናልፍ ይገባል ብለዋል።

ግጭት ሰላማዊ ባልሆነ መንገድ ሊፈታ ይችላል ፤ ነገር ግን በሃይል ሲፈታ ለትውልድ ቁርሾ የሚያስተላልፍ በመሆኑ ዘላቂ ሰላምን ሊያመጣ አይችልም። በጉልበት የሚመጣ አሸናፊነት ሕዝብን ያስከፋል፤ በመሆኑም የአሸናፊና የተሸናፊ ትርክቶችን በመተው ሀገራዊ ምክክሩ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን ገለፃ፤ ሀገርን በሰላም ለማስቀጠል ምክክር ወሳኝ ነው። በምክክር ውስጥ መከባበር፣ መደማመጥና ሃሳብን መቀበል አለ። በምክክር ሃሳቦች ይንሸራሸራሉ፣ ይጋጫሉ እንዲሁም ደግሞ አሸናፊ ይሆናሉ። ይህም በሰዎች መካከል አዲስ የመከባበር፣ የመተማመን እና የመተባበርን ባህል በማዳበር የዜጎችን ግንኙነት ከፍ ያደርጋል።

በምክክር አንዱ የአንዱን ሃሳብ በአግባቡ በማድመጥ የዚያን ሰው ሃሳብና ፍላጎት ለመረዳት ጥረት ያደርጋል ያሉት ፕሮፌሰር መስፍን፣ በሂደቱም የጋራ የሚሉትን እና የሚያግባቧቸውን መፍትሔዎች ያመነጫሉ፤ ሂደቱም ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርግ እና ተሸናፊ የሌለበት ይሆናል ብለዋል።

እንደ ዋና ኮሚሽነሩ ገለፃ፤ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ የፖለቲካና የሃሳብ መሪዎች መካከል እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሃሳብ ልዩነትና አለመግባባት ላይ ምክክሮችን ለማድረግ እና ሁሉን አቀፍና አካታች ሀገራዊ መግባባት ለመፍጠር እየሠራ ነው።

ምክክር ለማካሄድ ማቀዳችንና ለመደማመጥ መሞከራችን በራሱ አንድ ርምጃ ይሆናል የሚሉት ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን፤ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ለመሳተፍ በሩ ክፍት መሆኑን በማወቅ ዕድሉን እንዲጠቀምበት መክረዋል።

# “በቂ መምህራን ባለመኖራቸው ልጆቻችን ተገቢውን ትምህርት እያገኙ አይደለም”

- የተማሪ ወላጆች

# “የመምህራን ቅጥር እየተፈጸመ በመሆኑ ችግሩ በቅርቡ ይፈታል”

- የኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት

ሳሙኤል ወንደሰን



አዲስ አበባ፡- በሸገር ከተማ ኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ በኮዬ ቁጥር ሁለት የመጀመሪያ ደረጃና መካከለኛ ትምህርት ቤት በቂ መምህራን ባለመኖራቸው ልጆቻችን ተገቢውን ትምህርት እያገኙ አይደለም ሲሉ የተማሪዎቹ ወላጆች ገለጹ። የኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽህፈት ቤት በበኩሉ የመምህራን ቅጥር እየተፈጸመ በመሆኑ ችግሩ በቅርቡ ይፈታል ብሏል።

ወይዘሮ አለሚቱ ታደሰ (ስማቸው የተቀየረ) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የ2016 የትምህርት ዘመን ከተጀመረ ወራት ቢያልፉትም በትምህርት ቤቱ በቂ መምህራን ባለመኖራቸው ልጆቻችን ተገቢውን ትምህርት እያገኙ አይደለም። ስለዚህ ጉዳዩ አሳሳቢ በመሆኑ የሚመለከተው አካል ችግሩን በጊዜ ሊፈታ ይገባል።

በተጨማሪም ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች ንጹህ አይደለም። በዚህም የተነሳ ትምህርት ቤቱን ወላጆች እየመጡ የሚያጸዱበት ሁኔታ አለ ብለዋል። ተማሪዎች ምቹና ንጹህ አየር በሚገኝበት ቦታ ሊማሩ ይገባል ያሉት ወይዘሮ አለሚቱ፤ ስለዚህ የትምህርት ቤቱን ንጽህና ለመጠበቅ የሚችል ሠራተኛ መቅጠር ያስፈልጋል ብለዋል።

አቶ አበበ ተስፋዬ (ስማቸው የተቀየረ) በበኩላቸው፤ ትምህርት ቤቱ አሁን ባለበት ሁኔታ ልጆችን ለማስተማር የሚችልበት ደረጃ ላይ አይደለም ሲሉ ገልጸዋል። የመምህራን እጥረት በመኖሩ ልጆቻቸው በአግባቡ ትምህርት እየተማሩ ካለመሆኑም ባሻገር የትምህርት ቤቱ ፅዳት ላይም ችግር እንዳለ አብራርተዋል።

ልጆቻቸው ለግማሽ ቀን ብቻ ትምህርት እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በፈተና ጊዜ ከሙሉ ቀን ተማሪዎች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ስለሚጠበቅባቸው ጉዳዩ እንደወላጅ እንደሚያሳስባቸው ነው የተናገሩት። ትምህርት ከተጀመረ በርካታ ወራት ቢያልፉም ሦስቱም ልጆቼ እስከ አሁን ድረስ ከሦስትና ከአራት ገጽ በላይ በደብተራቸው አልጻፉም ያሉት ደግሞ የተማሪ ወላጅ ወይዘሮ ሐዊ ጋዲሳ (ስማቸው የተቀየረ) ናቸው።

“ልጆቼ ምን እንደተማሩ ባለማወቄ ማስጠናት አልቻልኩም። ልጆቼም በትምህርታቸው ከነበሩበት ደረጃ ዝቅ እያሉ ነው” ብለዋል ወይዘሮ ሐዊ። የኮዬ ፈጬ ክፍለ ከተማ የትምህርት ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ደሳለኝ ፈጠነ በሰጡት ምላሽ ችግሩ መኖሩን አምነው፤ የመምህራን ቅጥር እየተፈጸመ በመሆኑ ችግሩ በቅርቡ ይፈታል ብለዋል።

16 ትምህርት ቤቶች በአዲስ አበባ ሥር የነበሩ መሆናቸውን አንስተው፤ ከሐምሌ 2015 ዓመተ ምህረት ጀምሮ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ወደ ሸገር ከተማ በመቀላቀላቸው እና አንድ ሺህ 810 አስተማሪዎች ወደ አዲስ አበባ እንዲሄዱ በመደረጉ ችግሩ ሊፈጠር ችሏል ብለዋል።

በዚህም በትምህርት ቤቶቹ የመምህራን እጥረት ሊያጋጥም መቻሉን ጠቅሰው፤ ችግሩን ለመፍታት የመምህራን ቅጥር እየተፈጸመ መሆኑን አብራርተዋል። በክፍለ ከተማው ቀደም ሲል 927 አስተማሪዎች ቅጥር መፈጸሙንም ተናግረው፤ አሁንም የመምህራን እጥረት ያለ ቢሆንም የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዳይስተጓጎል ማድረግ ተችሏል ብለዋል።

በዚህም የተነሳ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች በፈረቃ እየተማሩ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል። ተማሪዎቹ የሙሉ ቀን ትምህርት እንዲያገኙም ይደረጋል ብለዋል።

ከጽዳት ሠራተኛና ከጥበቃ ጋር የሚነሱ ጥያቄዎች ተገቢና ትክክለኛ ናቸው ያሉት ኃላፊው፤ ይህም ችግር ሙሉ ለሙሉ በታህሳስ ወር የሚፈታ ይሆናል ብለዋል። አሁን ላይ ከተማው እየተዋቀረ ስለሆነ የከተማው ነዋሪዎች በትዕግስት እንዲጠብቁም ጠይቀዋል።

# ለ50 ሚሊዮን አርሶ አደሮች የማማከር አገልግሎት ተሰጥቷል

መዓዛ ማሞ




አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሶስት ዓመታት ለ50 ሚሊዮን አርሶ አደሮች በነጻ የስልክ መስመር የመረጃና የማማከር አገልግሎት መስጠቱን የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ገለጸ።

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ "ሜርሲ ክሮፕ" እና "ዩ አስ አይዲ ፊድ ዘ ፊውቸር" ከተሰኙ ሁለት ግብረሰናይ ድርጅቶች ጋር እንዲሁም "ክፍያ ቴክኖሎጂስ" ከተሰኘ ድርጅት ጋር የስራ ስምምነት ውል ተፈራርሟል።

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ማንደፍሮ ንጉሴ (ዶ/ር) በዚሁ ወቅት እንዳሉት፤ የተፈጸመው ስምምነት ለአርሶ አደሩና ለአርብቶ አደሩ በነጻ የስልክ መስመር ሲሰጥ የነበረውን የምክርና የመረጃ አገልግሎት ተደራሽነቱን ለመጨመር የሚያግዝ ነው።

ባለፉት ሶስት ዓመታት በ8028 ነጻ የስልክ መስመር ለ50 ሚሊዮን አርሶ አደሮች የመረጃና የምክር አገልግሎት መስጠቱን ጠቁመው፤ ከዚህ ውስጥ ደጋግመው በመደወል መረጃ የሚያገኙ ስድስት ነጥብ አራት ሚሊዮን የተመዘገቡ አርሶ አደሮች መኖራቸውንም ተናግረዋል።

የምርት ዋጋ መረጃ በሚሰጥበት 6077 የነጻ የስልክ መስመርም በርካታ ደዋዮች የምርቶች ዋጋ መረጃዎችን እያገኙ እንደሆነ ገልጸዋል። "ሜርሲ ክሮፕ"ና "ዩ አስ ኤይዲ ፊድ ዘ ፊውቸር" ከተሰኙት ድርጅቶች ጋር የተደረገው ስምምነት ድርጅቶቹ ለአርሶ አደሩና አርብቶ አደሩ በሁለት የነጻ የስልክ መስመሮች እየተሰጠ ያለውን የምክር አገልግሎትና የምርት ዋጋዎች መረጃ የመስጠት አገልግሎት ድርጅቶቹ በገንዘብ እንደሚደግፉ ጠቁመዋል።

"ከክፍያ ቴክኖሎጂስ" ጋር የተደረገው ስምምነት ለአርሶ አደሩ የማዳበሪያ ግዢ ሂደትን ዲጂታላይዝ ለማድረግ ያለመ እንደሆነም አመላክተዋል።

በነጻ የስልክ መስመር 8028 ለሚደውሉ አርሶ አደሮች በባለሙያ የምክር አገልግሎት እንደሚሰጥ እንዲሁም በ6077 በመደወል የየአካባቢው የምርት ዋጋ መረጃዎችን እንደሚያገኙ ገልጸዋል።

ዶክተር ማንደፍሮ እንደተናገሩት፤ መረጃ የመሰብሰብና የማሰራጨት ዋነኛ ዓላማ የአርሶ አደሩን ምርታማነትና ገቢ ለመጨመር እንዲሁም ለገጠሩ ማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ኑሮውን ለማሻሻል ማገዝ ነው።

የምርቶች ዋጋ መረጃው በዋናነት የሚያገለግለው ለአርሶ አደሮችና ለአርብቶ አደሮች ቢሆንም ለሸማቾችና ለነጋዴዎችም ምርቶችን ከየት ቦታ በተሻለ ዋጋ ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ የሚሰጥ በመሆኑ ሸማቾችና ነጋዴዎችም ደውለው አገልግሎቱን እያገኙ እንደሆነ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ሲንየር ዳይሬክተርና የዋና ሥራ አስፈጻሚ አማካሪ ጪምዶ አጫላ(ዶ/ር) በበኩላቸው እንዳሉት፤ የተደረገው ስምምነት ለአርሶ አደሮችና ለአርብቶ አደሮች በነጻ የስልክ መስመር ሲሰጥ የነበረውን የግብርና የምክር አገልግሎትና የምርቶች የዋጋ መረጃ ተደራሽነት የሚያስፋፋ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በተለይ አፋርና ሶማሌ ክልሎች የሚሰጠው አገልግሎት በእንስሳት ሀብት ላይ ያተኮረ እንዲሆን ያደርጋል ብለዋል።

በቅርብ ጊዜ አገልግሎቱ መጀመሩን አስታውሰው እስከአሁን ድረስ 130 ሺህ አርብቶ አደሮች በአገልግሎቱ እየተጠቀሙበት ነው ብለዋል።

"ከክፍያ ቴክኖሎጂስ" ጋር የተደረገው ስምምነትም በማዳበሪያ ስርጭት የነበረውን የልምድ አሠራር አርሶ አደሩ በቀጥታ በተንቀሳቃሽ ስልኩ ግዢ እንዲፈጽም በማድረግ ደላሎችን ከመሃል እንደሚያስወጣ ተናግረዋል።

የስምምነት ፊርማውን በኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርማሽን ኤጀንሲ በኩል የኤጀንሲው ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ማንደፍሮ ንጉሴ እንዲሁም የየድርጅቶቹ ኃላፊዎች ተፈራርመዋል።

# “የጤና አገልግሎት እየሰጠን ስንታመም የምንታከመው ግን በራሳችን ወጪ ነው”

## - የህክምና ባለሙያዎች

# “ባለሙያዎች አገልግሎቱን እንዲያገኙ የሚያስችል ጸድቆ የመጣ መመሪያ የለም”

## - ጤና ሚኒስቴር

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የጤና አገልግሎት እየሰጠን ስንታመም የምንታከመው ግን በራሳችን ወጪ ነው ሲሉ የህክምና ባለሙያዎች ገለጹ። የጤና ሚኒስቴር በበኩሉ ለተለያዩ ህመሞች ተጋላጭ ለሆኑ ባለሙያዎች የተለየ ገንዘብ ክፍያ ከመፈጸም ውጪ በባለሙያዎቹ የተነሳውን ቅሬታ ለመፍታት የሚያስችል ጸድቆ የመጣ መመሪያ የለም ብሏል።

ቅሬታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያቀረቡት ባለሙያዎቹ እንደገለጹት፤ በርካታ ተግዳሮቶችን በማለፍ የህክምና አገልግሎት ለሕዝቡ እየሰጠን ብንገኝም በምንታመምበት ጊዜ ግን በራሳችን ወጪ ነው የምንታከመው። ይህም ወጪው ከአቅማችን በላይ ሲሆን ለምነን ለመታከም ተገደናል ይላሉ።

የኢትዮጵያ ህክምና ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት የሆኑት ዶክተር ተግባር ይግዛው እንዳሉት፤ የጤና ባለሙያዎች በህክምና ሥራቸው ላይ ለሚገጥም ህመም ህክምና የሚያገኙት በሚቀጥራቸው የህክምና ተቋም ይሁንታ ላይ በመመስረት እንጂ በሕግ የተደገፈ መብት የላቸውም።

የጤና ባለሙያው ህመም ሲገጥመው የሚታከምበት ሕጋዊ የሆነ ማዕቀፍ እንደሌለው ያመላከቱት ዶክተር ተግባር፤ ይህም ህክምና ማግኘት መብት ይኑረው ወይም አይኑረው የሚያረጋግጥበት ሁኔታ የለም ብለዋል።




ዶክተር ተግባር አንዳንድ የጤና ተቋማት ሠራተኛ ስለሆኑ ብቻ በመልካም ፍቃድ የተወሰኑ ነገሮችን በነፃ ሊያክሙ እንደሚችሉ የጠቆሙ ሲሆን ይህ ግን ለባለሙያው ሕጋዊ መብት እንደማይሰጠው ጠቅሰዋል።

ዶክተር ተግባር አንድ በሀገሪቱ የትኛውም ስፍራ ላይ ያለ የጤና ባለሙያ ባለበት አካባቢ ላይ እንደምንም አገልግሎት ቢያገኝ እንኳን ወደ ሌላ አካባቢ ሲሄድ አገልግሎት እንደማያገኝ በመጥቀስ፤ ይህም የጤና ባለሙያዎች የሚሰጡትን አገልግሎት ለራስ መንፈግ የሞራል ጥያቄ ያስነሳል ብለዋል።

ለጤና ባለሙያ የሚሰጠውን አገልግሎት በነፃ እንዲያገኝ ማድረግ በጤና ዘርፍ ላይ ያለውን ጥራትና ዘመናዊነት ለማስጠበቅ ስለሚኖረው ጉልህ አስተዋፅኦም ዶክተር ተግባር ጠቅሰዋል።

የጤናው ዘርፍ የዓመታት ዕቅድ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎትን በሁሉም ስፍራ የማዳረስና በገንዘብ ምክንያት አገልግሎት የሚያጡ ዜጎችን መታደግ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ተግባር፤ በሀገራት ተሞክሮም የጤና መድን መተግበር የሚመከር መሆኑን ገልጸዋል።

የጋምቢ ሜዲካል ቢዝነስ ኮሌጅ ባህርዳር ካምፓስ ዲን ዶክተር አዱኛ ጣሰው በሰጡት አስተያየት እንዳሉት፤ የጤና ባለሙያዎች የሚሠሩበት ተቋም ሊደግፋቸው ካልተንቀሳቀሰ በቀር ሲታመሙ በነፃ የሚታከሙበት የተደራጀ ሥርዓት የለም።

የጤና መድህን ጉዳይ በየመሥሪያቤቱ የሚሠራበት ሂደት መኖሩን የጠቀሱት ዶክተር አዱኛ፤ይህ አሠራር በጤና ተቋማት ባለመዘርጋቱ የህክምና ባለሙያዎች ችግሮችን በመጋፈጥ ላይ ናቸው ነው ያሉት።

በጤና ሚኒስቴር የሰው ሀብት አስተዳደር የሠራተኛ አገልግሎትና ማበረታቻ ቡድን መሪ ወይዘሮ ፍቅረሰላም ጋሜ በሰጡት ምላሽ እንዳሉት፤ ለተለያዩ ህመሞች ተጋላጭ ለሆኑ የጤና ባለሙያዎች የተለየ የገንዘብ ክፍያ ከመፈጸም ውጪ በባለሙያዎቹ የተነሳውን ቅሬታ ለመፍታት የሚያስችል ጸድቆ የወጣ መመሪያ የለም ብለዋል።

እንደ ኃላፊዋ ንግግር፤ ተጋላጭ የሥራ ክፍል ውስጥ ያሉ ማለትም በንክኪ በትንፋሽና በደም ለሚተላለፉ በሽታዎችን ለሚያክሙ የጤና ባለሙያዎች የተለየ ገንዘብ ይከፈላቸዋል። ተጋላጭ እንዳይሆኑ የሚያስችሉ ግብዓቶችም ይቀርብላቸዋል። ከዚህ ውጪ የጤና ባለሙያዎች ህመም በሚገጥማቸው ወቅት የተለየ ክፍያም ሆነ የጤና መድህን የሚያገኙበት በፅሁፍ የተደገፈ መመሪያ የለም ሲሉ ጠቅሰዋል።



# በሲዳማ ክልል ከተተከሉ ችግኞች 85 በመቶ ጸድቀዋል

## - ከሦስት ሺህ 600ኪሎ ግራም በላይ የችግኝ ዘር ተሠራጭቷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል በ2015/16 በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀግብር ከተተከሉ ችግኞች 85 በመቶ ያህል መጽደቃቸውን የክልሉ የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

በቢሮው የተፈጥሮ ሀብትና አነስተኛ መስኖ ልማት ዳይሬክተር አቶ በረከት አሰፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የአረንጓዴ ዐሻራ ዝግጅትና እንክብካቤ አፈጻጸም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል። የህብረተሰቡ ተሳትፎም በተመሳሳይ እያደገ መጥቷል። በ2015/16 የተተከሉ ችግኞች ላይ በተደረጉት የሁለት ዙር ቆጠራ 85 በመቶ ያህሉ ጸድቀዋል። በክልል ደረጃ ችግኞች ከተተከሉ በኋላ የዝናብ እጥረት አጋጥሞ እንደነበር የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ የተተከሉ ችግኞች እንዳይሞቱ ለማድረግ ህብረተሰቡ ውሃ ካለበት ሥፍራ እየቀዳ እንዲንከባከብ ማድረጉን ጠቅሰዋል። በዚህም ብዙ ችግኞችን መታደግ እንደተቻለ አስታውቀዋል። በዝናብ እጥረት ምክንያት ተግዳሮት ባያጋጥም የችግኞቹ የጽድቀት መጠን ከ90 በመቶ በላይ ሊደርስ እንደሚችልም ነው የተናገሩት።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ በክልሉ በብዛት የተተከሉት ለጥምር ደን እርሻ የሚውሉ ችግኞች ሲሆኑ፤ ከዚህ ውስጥም ወደ 30 በመቶ ያህሉ ለቡና ጥላ የሚሆኑ ሀገር በቀል ተክሎች ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ። ሰባት ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ የፍራፍሬ ችግኞች ናቸው። እነዚህ የፍራፍሬ ችግኞችን አርሶ አደሩ ገቢ እንዲያገኝበት ጭምር ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። የቀርከሃና የቡና ችግኞችም በክልሉ በስፋት ከተተከሉት ውስጥ ይገኛሉ። ህብረተሰቡ ውሃ ከማጠጣት ጀምሮ ችግኞችን ኮትኩቱ በመንከባከብ ደረጃ የነበረው ተሳትፎ የሚበረታታ ነበር።

ችግኝ ከተከላው ባሻገር በቂ እንክብካቤ ይፈልጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይ ከዘር ስርጭት ባሻገር በእንክብካቤው ረገድ በሁሉም ወረዳዎች ጠንካራ የክትትል ሥራዎች እንደሚኖሩ አስታውቀዋል። ተከላው አካባቢ የሚገኙ የውሃ አማራጮችን በመጠቀም እንክብካቤ እንዲደረግ ከወረዳዎች ጋር ይሠራል ብለዋል። በዚህ ዓመት ለሚደረገው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ቅድመ ዝግጅቶች በክልል ደረጃ እየተደረጉ እንዳለም ዳይሬክተሩ ገልጸዋል። በዚህም የዓመቱን ችግኝ በጊዜ ለማዘጋጀት የችግኝ ተከላ ቦታዎችን የመለየት እንዲሁም ከየስፍራው ዘር የመሰብሰብ ሥራ መሠራቱንና በዚህም ሦስት ሺህ 620 ኪሎ ግራም የችግኝ ዘር ለወረዳዎች መሠራጨቱን አስታውቀዋል። እስካሁን ባለው ሁኔታም 15 ሚሊዮን ችግኝ ማፍላት ተችሏል። የችግኝ ቁፋሮ እንዲደረግ፤ በችግኝ ተከላው መርሃ ግብር ወቅት እንደ ከዚህ በፊቱ ህብረተሰቡ በነቂስ ወጥቶ ተሳትፎ እንዲያደርግ አቅጣጫ መቀመጡን ተናግረዋል። ከገጠመው ተሞክሮ በመነሳት እንክብካቤው ላይም ሰፊ ሥራ ለመሥራት መታቀዱን ነው የገለጹት።

በሲዳማ ክልል በ2015/16 የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ከ 11 ሚሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸውን አስታውሰዋል።

# የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ነፃ ሆነው ሀገርን የሚገነባ ዕውቀት ማፍራት ይጠበቅባቸዋል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከፖለቲካና ከብሔር ጉዳዮች ነፃ ሆነው ሀገርን የሚገነባ ዕውቀት ማፍራት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ የትምህርት ሚኒስትርና የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ተናገሩ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ መሆንን መሠረት በማድረግ "በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚክ ነጻነት" በሚል ሃሳብ ትናንትና የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

በውይይት መድረኩ ላይ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንደገለጹት ፤ የአካዳሚክ ነጻነት ጉዳይ የዩኒቨርሲቲዎች ብቻ ሳይሆን የማህበረሰቡም ጭምር መሆኑ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ነጻነታቸውን በማወጅ ለሀገር የሚበጅ ሥራ ማከናወን አለባቸው።

በሀገሪቱ ያሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እስከዛሬ ድረስ በነጻነት ሲሰሩ አልነበረም ያሉት ሚኒስትሩ፤ የፖለቲካ፤ የባህል እና የብሄር ጫና ሲደርስባቸው መቆየታቸውን አንስተዋል።

በመሆኑም የዩኒቨርሲቲዎች የራስ ገዝ እሳቤው ዩኒቨርሲቲዎች በራሳቸው ነጻነት ተንቀሳቅሰው እንዲሠሩ፤ ተማሪዎቻቸውን በእውነተኛ እውቀታቸው የሚለኩበት አሠራር እንዲፈጥሩ ማድረግ በአጠቃላይ በየጊዜው የሚሻሻል ዕውቀት የሚፈራበት ሥፍራ መፍጠርን ያለመ ነው ብለዋል። የአካዳሚክ ነፃነት ሀገር የሚገነባ ሃሳብ ያላቸው ዜጎች ህብረተሰቡን የሚመራ ዕውቀት እንዲያመጡና በነጻነት እንዲያስቡ ቦታ የመስጠቱን ሂደት ያጠቃልላል ሲሉ ተናግረዋል።

ፕሮፌሰር ብርሃኑ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ዕውቀት ላይ ተመስርተው የሚሰሩ ሰዎች ያስፈልጓታል ፤ ለዚህም የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን በትምህርት ዘርፉ የሚደረገውን ለውጥ በማገዝ ውጤት ለማምጣት ይረዳል።



ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ



ሳሙኤል ክፍሌ ( ዶ/ር)

ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ራስ ገዝነት ጋር ተያይዞ በማህበረሰቡ ዘንድ የተሳሳተ ግንዛቤ መኖሩን አንስተው፤ ራስ ገዝ ማለት በአካዳሚክ ነጻነት ላይ ተመስርቶ በዕውቀት የተመራ ውይይት የሚደረግበት መድረክን መፍጠር መሆኑን ማወቅ ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠባባቂ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ (ዶ/ር) በበኩላቸው የራስ ገዝ መሆን ማለት በአካዳሚክ ጉዳዮች ፣ በአስተዳደር፤ በሰው ኃይልና ሀብት ከማፍራት ረገድ ነጻ ተቋም ሆኖ የመሥራት አቅምን የሚፈጥር አሠራር ነው ብለዋል።

የአካዳሚክ ነጻነት ሲባል ምሁራን ሀገርን የሚጠቅም ዕውቀት በነጻነት እንዲይዙና እንዲገልጹ ማድረግን ያካትታል ሲሉ ዶክተር ሳሙኤል ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እስከ 1969 ዓ.ም ድረስ እራሱን በራሱ ሲያስተዳድር እንደነበር አስታውሰው፤ ራስ ገዝ የመሆኑ አሠራር ለዓመታት ተቋርጦ መቆየቱን አብራርተዋል።

በቅርቡ መንግሥት ባደረገው ለውጥ መሠረት ዩኒቨርሲቲው የራስ ገዝ እንዲሆን በመወሰኑ ወደሥራ ተገብቷል፤ ይህም ለዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ነጻነት ይሰጣል ብለዋል።

አሰራሩ ተማሪዎችን በነፃ መርጦ ለማስተማር፣ የማስተማሪያ ፕሮግራሞችን በራስ አሠራር ለመቅረጽና መምህራንን በነጻነት የመቅጠር ዕድልን ይፈጥራል ሲሉ አስረድተዋል።

ራስ ገዝ የመሆን ነጻነት በአዋጅ ብቻ የሚሰጥ ሳይሆን በሥራ ሂደት የሚገኝም አቅም ነው ያሉት ዶክተር ሳሙኤል፤ ዩኒቨርሢቲው ነጻነቱን ለማስጠበቅ ለማህበረሰቡ ጠቃሚ ምርምሮችንና የውይይት መድረኮችን እንደሚያዘጋጅ አመላክተዋል።

# በኢትዮጵያ ከ168 ሺህ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በመተባበር 168 ሺህ 269 የሚሆኑ ስደተኞች የትምህርት እድል እንዲያገኙ አድርጓል።

ተማሪዎቹ በ65 ቅድመ አንደኛ ደረጃ፣ በ53 አንደኛ ደረጃ እና በ11 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት እድል እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን በአቅራቢያቸው በሚገኙት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ከአካባቢው ማህበረሰብ ልጆች ጋር ተቀላቅለው እየተማሩ ይገኛሉ ብለዋል።

በተመሳሳይ የማህበረሰቡ ልጆችም ለስደተኞች ተብሎ የተሠሩት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከስደተኞች ጋር ተቀላቅለው እንዲማሩ እድሉ የተመቻቸበት ሁኔታ አለ ያሉት ዶክተር እንግሊዝ፤ ይህም ቋንቋ፣ ባህል እና አብሮነትን እንዲለማመዱ እድል ፈጥሮላቸዋል ብለዋል።

12ኛ ክፍልን አጠናቀው መግቢያ ነጥብ ያገኙ ተማሪዎች እንደማንኛውም ተማሪዎች የዩኒቨርሲቲ ምደባ የሚሰጣቸው ሲሆን በርካቶች አሁን ላይ በዩኒቨርሲቲ ገብተው እየተማሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር እንግሊዝ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ስደተኞችን በማስተናገድ ከአፍሪካ ከዩጋንዳና ከሱዳን በመቀጠል በሶስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። በአሁኑ ሰዓት ሀገራችን በቁጥር 927 ሺህ 300 ለሚሆኑ ስደተኞች መጠለያ ሆና እያገለገለች ያለች ሀገር ስትሆን በብዛት ስደተኞቹ ከደቡብ ሱዳን፣ ከሶማሊያ፣ ከኤርትራና ጥቂት የሚባሉት ደግሞ ከሌሎች ሀገሮች የመጡ ናቸው።

በዋናነት ስደተኞቹ በጋምቤላ፣ በሱማሌ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ በአፋር፣ በአማራና በትግራይ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የተጠለሉ ናቸው። ኢትዮጵያ ካስጠለለቻቸው ስደተኞች ግማሽ የሚሆኑት እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ቢሆኑም ቀላል ቁጥር የማይባሉ በራሳቸውና በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ትምህርት ቤት ሊመጡ አልቻሉም ብለዋል።

የስደተኞች ትምህርት መርሃ-ግብር ዓላማ አንደኛው የመንግሥት ትምህርት ቤቶች የሚያገኙትን አገልግሎቶች ለስደተኞች ተማሪዎች ማዳረስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ማካተት የሚባል ነው። ይህም ሁለተኛ ደረጃ የስደተኞች ትምህርት ቤቶችን በመንግሥት አስተዳደር ስር ማስገባት እንደሚያስችል ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ለስደኞች ትኩረት በመስጠት ከሰብዓዊ አገልግሎት በተጨማሪ ከዜጎቿ ያልተናነሰ የትምህርት እድል በመፍጠሯ ከስደተኞቹና ከሌሎች ሀገሮች ጋር መልካም የዲፕሎማሲ ግንኙነት እንዲኖራት አድርጓል ያሉት ባለሙያው፤ "ሀገራችን የስደተኞች ትምህርት ላይ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ብታከናውንም ብዙ ተግዳሮቶች ተስተውለዋል" ብለዋል።

አንደኛው የበጀት ማነስ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በአንዳንድ ትምህርት ቤቶች የመብራት እጥረት፣ የመማሪያ ክፍል ማነስ፣ የተወሰኑ መምህራን የትምህርት ዝግጅት ከደረጃ በታች መሆን እና ሁሉንም እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱትን ህፃናት ወደ ትምህርት ገበታ ያለመምጣት በዋናነት የተለዩ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

እነዚህን ችግሮች ከማቅለል አንፃር የትምህርት ሚኒስቴር በራሱ መፍታት የሚችላቸውን መፍትሄ እየሰጠ ይገኛል። ሆኖም የስደተኞችን የትምህርት መርሀ-ግብር በታቀደው መልኩ እንዲካሄድና ተማሪዎቹ ጊዜውን ያገናዘበ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ መተባበር ያስፈልጋል።

# በዓመት ከ8 ሺ በላይ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሲሆን በጾታም የሴቶች ቁጥር ይጨምራል ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት የቫይረሱ የስርጭት መጠን ዜሮ ነጥብ ዘጠኝ በመቶ መሆኑን የጠቀሱት ሥራ አስፈጻሚው፤ በአጠቃላይ ከ610 ሺ. 350 በላይ ወገኖች በደማቸው ቫይረሱ ይገኛል ብለዋል።

ከአምስት መቶ ሺ. በላይ የሚሆኑት የጸረ ኤች. አይ. ቪ. ህክምና እየተከታተሉ ቢሆንም መድኃኒት ባለመጀመርና በአግባበቡ ባለመከታተል በየዓመቱ 11 ሺ. 300 የሚደርሱ ሰዎች ሕይወታቸው እንደሚያልፍም ሥራ አስፈጻሚው ገልጸዋል።

የስርጭት ምጣኔው ግን ከክልል ክልል እንዲሁም ከማህበረሰብ ማህበረሰብ በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛል ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ እ.አ.አ.የ 2022 ሀገራዊ የኤች አይ ቪ ስርጭት ግምት እንደሚያሳየው ከፍተኛው በጋምቤላ ክልል መሆኑንና የስርጭት መጣኔውም 3 ነጥብ 69 በመቶ መሆኑን ጠቁመዋል፤

አዲስ አበባ 3 ነጥብ 47፣ ሐረሪ በ2 ነጥብ 97፣ ድሬዳዋ በ 2 ነጥብ ዘጠኝ የስርጭት በመያዝ የሚከተሉ ሲሆን ዝቅተኛው ሶማሌ ክልል መሆኑንና የስርጭት መጠኑም 0 ነጥብ 18 በመቶ እንደሆነ ጠቅሰዋል። እንደ አጠቃላይ ሥርጭቱ በከተማ 2 ነጥብ 9 እንዲሁም በገጠር ዜሮ ነጥብ አራት መሆኑንም ሥራ አስፈጻሚው አብራርተዋል።

እንደ ሀገር የቫይረሱ ስርጭት ምጣኔ ዜሮ ነጥብ ዘጠኝ በመቶ ሲሆን ይህም በዓለም የጤና ድርጅት ከተቀመጠው ከአንድ በመቶ በላይ የወረርሽኝነት ደረጃ መለኪያ ዝቅ ብሎ ይገኛል።

የስርጭት መጠኑ እ.አ.አ በ2010 1 ነጥብ 26 የነበረ ሲሆን በስርጭት ምጣኔው ይበልጥ ተጋላጭ የሚሆኑት ሴተኛ አዳሪዎች፤ አደንዛዥ እጽ መድኃኒት ተጠቃሚዎችና የሕግ ታራሚዎች እንደነበሩም ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

ከዚህም በተጨማሪ የሀገር አቋራጭ አሽከርካሪዎች፤ ትዳር የፈቱ ግለሰቦች፤ በሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋ የደረሰባቸው አካባቢዎች እንዲሁም ወጣቶችና ሴቶች ይበልጥ የስርጭቱ ተጋላጮች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ከዚህ በፊት የመከላከሉም ሆነ የህክምናው ሥራ ይከናወን የነበረው ስርጭቱ በወረርሽኝ ደረጃ ላይ እያለ ስለነበር ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል አካቶ ይሠራ እንደነበር ጠቁመው፤ አሁን ግን ትኩረት የሚሹና ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ በተለየ ትኩረት እንደሚሠራ ተናግረዋል።

ይህም ሆኖ የመቀነሱ መጠን ግን በሚፈለገው ደረጃ ባለመሆኑ ሶስቱ የዘጠና አምስት ግቦች በሚል ዕቅድ ተቀምጦ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ይህም በደማቸው አንደኛ ቫይረሱ ከሚገኝባቸው ሰዎች ዘጠና አምስት በመቶ እንዲያውቁ ማድረግ፤ ሁለተኛ ራሳቸውን ካወቁት ዘጠና አምስት በመቶ መድኃኒት እንዲጀምሩ ማድረግ እንዲሁም ሶስተኛ መድኃኒት ከሚወስዱት ዘጠና አምስት በመቶ የቫይረሱ መጠን እንዲቀንስ ማድረግ እንደሆነ አቶ ሀብታሙ ተናግረዋል።

ይህ ጥሩ አፈጻጸም ያለው ቢሆንም ቫይረሱ የሚገኝባቸውን በመለየት ረገድ ክፍተት መኖሩን ጠቁመው፤ በመሆኑም ግንዛቤ በመፍጠሩ ረገድ የኃይማኖት ተቋማት፤ ሚዲያዎች፤ የትምህርት ተቋማትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

# የማዕድን ዘርፉ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከሰጠባቸው አምስት ዘርፎች አንዱ የማዕድን ዘርፍ መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ያለንን የማዕድን ሀብት ለማወቅ ጥረት ሲደረግ መቆየቱን አስታውቀዋል።

አሁን ላይ ያሉትን የማዕድን ሀብቶች አውቀን ባንጨርስም ኢትዮጵያ በርካታ የማዕድን ሀብት የታደለች ሀገር መሆኗን መረዳት ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል።

ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካትና የተለያዩ ማዕድናትን ወደተለያዩ ሀገራት በመላክ በርካታ የውጭ ምንዛሬን ማስገኘት መቻሉን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገት አይተኬ ሚና እየተጫወተ ይገኛል ብለዋል።

ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብት የታደለች ሀገር በመሆኗ ያለውን ሀብት በሚፈለገው ደረጃ አልምቶ ለተተኪው ትውልድ የተሻለች ኢትዮጵያን ማስረከብ አለብን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ከችግር ነጻ የሆነ የመልሚያ መንገድ ባለመኖሩ በዘርፉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጋራ በመፍታት ወደብልጽግና ከፍታ መገስገስና ለትውልዱ የተሻለ ሀብት መፍጠር ይገባል ብለዋል።

በኢትዮጵያ በሁሉም አካባቢዎች አስደናቂ የማዕድን ሀብቶች አሉ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ያለንን የማዕድን ሀብት በአግባቡ ማወቅና መጠቀም ከቻልን ለሀገሪቱ የብልጽግና ጉዞ መሠረት መጣል ይቻላል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የወርቅ፣ የከበሩ ድንጋዮችና የበርካታ ውድ ማዕድናት መገኛ እንደሆነች ኤክስፖው አመላካች ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ተማሪዎች፣ ተመራማሪዎች፣ ነጋዴዎች፣ ኢንቨስተሮችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በዘርፉ ምን እንዳለና ምን እየተሠራ እንደሆነ በመማር ኢኮኖሚውን ሊደግፉ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ኤክስፖው ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ክምችት የሚያሳይ፣ የማዕድን ሀብትን ወደውጭ ለመላክ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር እና ለሚቀጥለው የብልጽግና ጉዟችን መሠረት የሚጥል ዘርፍ መሆኑን የምንረዳበት መሆኑን አስታውቀዋል።

የምናስበው የእድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ በማዕድን ዘርፉ የተሰማሩ አልሚዎች በግል ማምረትና ኢንቨስት ማድረጋቸውን አቁመው በጋራ መሥራት የምንችልበትን፣ እውቀት የምናሰባስብበትንና የምንበለጽግበትን መንገድ መፍጠር ይገባል ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል።

የማዕድን ሚኒስትሩ ሀብታሙ ተገኝ (ኢ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ በሁሉም አካባቢዎች ከሚገኙት የማዕድን ሀብት ተጠቃሚ ለመሆን መንግሥትን ከባለሀብቶች፣ ባለሀብቶች ከባለሀብቶች ጋር እንዲገናኙ ኤክስፖው ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ያላትን የማዕድን ሀብት ለማስተዋወቅ መንግሥት፣ ባለሀብቶች እና በዘርፉ የተሠማሩ የግል ሴክተሮች ድርሻቸው የጎላ መሆኑን ገልጸው፤ ማዕድኑን በሚፈለገው ደረጃ አልምተን ተጠቃሚ መሆን ካልቻልን የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጥያቄ ውስጥ ይገባል ብለዋል።

በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ብሔራዊ የማዕድን ካውንስል መቋቋሙን አስታውሰው፤ ባለድርሻ አካላት በጋራ በመሆን ለችግሩ መፍትሄ ያመጣሉ ተብሎ ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

ከኤክስፖው ጎን ለጎን በማዕድን ዘርፉ የሚመክር ኮንፈረስ የሚካሄድ ሲሆን፤ በዘርፉ ልምድና ተሞክሮዎች ቀርበው ውይይት ይደረግባቸዋል ብለዋል።

ኤክስፖው ከህዳር 14 እስከ ህዳር 18 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ የሚቆይ ሲሆን፤ ከ90 በላይ ኩባንያዎች በኤክስፖው ተሳትፈዋል። ወርቅ፣ የድንጋይ ከሰል፣ የከበሩ ማዕድናትና ጌጣጌጦች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ማዕድን ቴክኖሎጂ ሲሚንቶና የተለያዩ ምርቶች በኤግዚቢሽኑ ቀርበዋል።

በኤክስፖው መክፈቻ የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አገኘሁ ተሻገር፣ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የሥራ ሃላፊዎች፣ ኢንቨስተሮች፣ የሀገር ውስጥና የውጭ የዘርፉ ምሁራን፣ የማዕድን አምራቾች፣ ላኪዎችና ተጠቃሚዎች እንዲሁም የፋይናንስ ተቋማት ተገኝተዋል።

# የገበያ ማዕከላቱ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የማዕከላቱ መገንባት ሻጭ ገበሬውንና ገዢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ይገልጻሉ።

ማዕከሉ ገዥና ሻጭን የሚያገናኝ፣ በወቅቱ ዋጋ ላይ በተመሠረተ ሁኔታ ምርት በማቅረብ የንግድ ውድድርን ጤናማ የሚያደርግና የምርት ጥራትን ለማሳደግ የሚረዳ መሆኑን ይናገራሉ።

በግብይት ሂደት ውስጥ የሚኖረውን የደላሎችን እንቅስቃሴ የሚያስቀር ነው። በመሆኑም የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር የሚያስችል መንገዶችን እንደሚፈጥር ያስረዳሉ።

ሻጭ ከገዢ ጋር በሚገናኝባቸው ሂደቶች ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶች ሲኖሩት የዋጋ መናርን እንደሚያስከትል የሚገልጹት መምህሩ የገበያ ማዕከላቱ መገንባት ጤናማ የገበያ ሁኔታዎችን በመፍጠር የሚኖረውን አላግባብ ተሳትፎና ወጪዎችን በመቀነስ የዋጋ ውድነትን ለመቆጣጠር ይረዳል ሲሉ ይናገራሉ።

የመሸጫ ማዕከላትን መገንባት ገበሬው ማግኘት የሚገባውን ትርፍ እንዲያገኝ ይረጋዋል። በሌላ በኩል በአነስተኛ ዋጋ ለሸማች ማድረስ የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚያስችል አብራርተዋል።

የገበያ ማዕከላቱ መገንባትና ወደ ሥራ መግባት ለአምራች ገበሬው የገበያ ትስስርን በመፍጠር ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖራቸው የተናገሩት የምጣኔ ሀብት መምህሩ የገበያ ትስስሩ ጥቅማቸውን የሚያስቀርባቸውን ደላሎች ሥርዓቱን ለማደናቀፍ የሚያደርጉትን ጥረት በሕግ አግባብ መቆጣጠር እንደሚያስፈልግ ነው ያመላከቱት።

በአንድ አካባቢ ተመሳሳይ ምርቶችን የሚያመርቱ ገበሬዎች በጋራ ወደ ምርት ገበያው የሚያመጡበት ሁኔታን መፍጠር ተገቢ መሆኑን አስረድተው፤ ገበሬዎች በህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ምርቶቻቸውን ወደ ማዕከላቱ ማቅረብ የሚችሉበት መንገድ ማመቻቸት እንደሚያስፈል ይገልጻሉ።

በግብይ ሂደት ውስጥ የደላላውን እንቅስቃሴ መቀነስ፣ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነቱን ለማርገብ የገበያ ማዕከላቱ ሚና የጎላ ነው። በገበያው የዋጋ መጠንን ለመወሰን በሚደረገው ድርድር ላይ የገዢ የበላይነት እንዳይኖር ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል ብለዋል።

ለገበሬውና ለማህበረሰቡ ማዕከላቱን ከማመቻቸት ባሻገር ሥርዓቱ የሚሄድበትን ሕግና ሥርዓትን መዘርጋት ተገቢ ነው። የግብይት ሥርዓቱ የሚመራበት ሕግ፣ ክትትል በማድረግ ማስፈጸም ያስፈልገዋል ሲሉ ነው የተናገሩት።

በተጨማሪም ገበሬው የምርት ውጤቱን የሚያቀርብባቸው የሰንበት ገበያዎች፣ ባዛርና መሰል የገበያ ማዕከላት ግንባታ ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል። በተለይም ገበሬው ወደ ምርት ገበያው ሲመጣ የመደራደር አቅም እንዲኖረው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ሊሰሩ ይገባል ይላሉ።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህሩ አጥላው አለሙ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደሚናገሩት፤ የግብርና ምርቶች ተመርተው ወደ ገበያ ማዕከላቱ ለማስገባት፣ ገበሬው እንደልቡ እንዲሠራ፣ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ እቃ አግኝተው አምርተው የውጭ ምንዛሬ እንዲያመጡ የሀገሪቱ የሰላም ሁኔታ ሊረጋገጥ ይገባል።

በገበያው ሂደት ላይ የሕገወጥ ደላሎችን እንቅስቃሴ ለመግታት ለአርሶአደሩ በቂ መረጃን መስጠት እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፤ አምራቹ ተንቀሳቅሶ የሚሸጥበትን ሁኔታ መፍጠር ሲቻል የደላላውን እንቅስቃሴ መቆጣጠር ይቻላል ሲሉ ተናግረዋል።

አምራቹ የዋጋ ተመን፣ የመሸጫ ቦታና ሸማች የት እንደሚያገኝ በቀላሉ የሚያውቅበት ሁኔታ አለመኖርና የትራንስፖርት ችግሮች አስቻጋሪ ሁኔታዎችን መፍጠራቸውን ነው የገለጹት።

ለገበሬው የገበያ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የገበያ መረጃ መስጠትና ተገቢ መሆኑን የገለጹት ዶክተር አጥላው በተለይም መሸጫ ቦታ ማመቻቸት፣ የዋጋ መረጃ መስጠትን ጨምሮ ሰላምን ማስፈንና በቂ የትራንስፖርት አገልግሎት እንደሚያስፈልጉ አመላክተዋል።

የኑሮ ውድነቱን ለማርገብ በመንግሥት በኩል የገንዘብ ፖሊሲን ማርገብ፣ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ መሥራትና ሰላምን በማስፈን ውጥረቶችን ማቃለል እንደሚገባ ነው ያስረዱት።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አምራቹን ከሸማቹ ጋር በቀጥታ ለማገናኘት በኮልፌ፣ በአያትና ሰሚት በሚገኙ የመግቢያ በሮች የግብርና ምርት ማከማቻና መሸጫ ተገንብተው ወደ አገልግሎት በመግባት ላይ መሆናቸው ይታወሳል።

# አገልግል

## የቅዳሜ መጽሔት

የውስጥ ገጾች



ኑሮን በፈተና - ሕይወትን በፅናት

ገጽ 16



የቃሊቲ ሞዴል መናኸሪያ ግንባታ - በማጠናቀቂያ ምዕራፍ

ገጽ 14

## ‹‹ለሀገር ዕድገት ከቴክኖሎጂ እና ካፒታል የበለጠ የሰው ኃይል በጣም ወሳኝ ነው››

ገመቹ ዋቅቶላ ዶ/ር



ገጽ 6

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

አፍሪቃዊቷ መልኅቅ

# የሀገር ውስጥ የጉብኝት ባህልን ለማሳደግ

ዳንኤል ዘነበ

ኢትዮጵያ ከዳሎል እስከ ራስ ዳሸን አስደናቂ መልክአ ምድር፤ በየትኛውም አካባቢ የሚያስደምሙ በርካታ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ መስህቦች ያሏት ሀገር ነች ። በዓድዋ ድል ለጥቁሮች ነፃነት ፋና ወጊ በመሆን ለፈፀመችው ገድል ብዙ ያልተዘመረላት፤ በሰው ዘር መገኛነቷ የሚገባትን ያክል ታውቃ የዓለም የጎብኚዎች መናገሻ ናት ። የበርካታ አስደናቂ መስህቦች ባለቤት የሆነችውን ኢትዮጵያ ዜጎቿ በተለያዩ መንገዶች ተንቀሳቅሰው መመልከትና ማወቅ ይኖርባቸዋል። ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ያላትን የተፈጥሮ ጸጋዎችና ታይተው የማይጠገቡ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ቅርሶችን እንዲሁም ከጫፍ ጫፍ ያለውን የተለያየ ባህል፣ አመጋገብ፣ አልባሳት፣ የተፈጥሮ ጸጋዎችና ታይተው የማይጠገቡ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ቅርሶችን ሊጎበኙ ይገባል። ነገር ግን ህብረተሰቡ የቀደመ ታሪኩንና ባህሉን የሚያንፀባርቁ ቅርሶችና መስህቦችን የመጎብኘት ልምዱ አነስተኛ ነው ። በመሆኑም የሀገር ውስጥ ጎብኚ ተንቀሳቅሶ የማየትና የማወቅ ልምዱ ዝቅተኛ በመሆኑ ሀገሪቷ ያሏትን ሀብቶች በቅጡ ሳያውቁ ኖረው ያልፋሉ።

በወርሃ መስከረም በ2012 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ዛሬ ላይ ለጎብኚዎች ክፍት የተደረገው የቤተ መንግሥቱን "የአንድነት ፓርክ " የግንባታ እንቅስቃሴ ሲያስጎበኙ የተናገሩትን ማስታወስ ያስፈልጋል ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፤"ብዙ ኢትዮጵያዊ ሀገሩ ውስጥ ያለውን አያውቅም ። አንድ ዜጋ በሀገሩ ያለውን ሀብት አስተካክሎ መጠቀም የገቢ ጥቅም ብቻ ሳይሆን የማንነትን ልክ ያሳያል፤ አዳዲስ ነገር ለመፍጠርም ያነሳሳል ። ያለውን ሀብት የቱሪዝም ጥቅም እንዲያስገኝ ማመቻቸት ወሳኝ ሥራ መሆኑ አንዱ ነው። አሁን ላይ ያጠረንን የውጭ ምንዛሬ ገቢን ከፍ ለማድረግም ትልቁና ሰፊው ምንጭ ይኸው ቱሪዝም መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። በተጨማሪም የሰው ኃይል በማሠማራት ረገድ ጥቂት የማይባል ሥራ ሊፈጥር የሚችል መስክ ነው" ሲሉ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው የሚገኙ የቱሪዝም ሀብታቸውን እንደማያውቁ እና የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እንቅስቃሴን ደካማ መሆኑን ያመላከቱት። የሀገር ውስጥ ቱሪዝም መስፋፋት ለአካባቢያዊ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መጠናከር እንዲሁም የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን በመፍጠር ብሔራዊ አንድነትን ለማጎልበት አስተዋኦ አለው ። ታዲያ ይህ በኢኮኖሚ አቅምን ለማጎልበት ቀዳሚ ተጠሪ ሊሆን የሚችል ዘርፍ ለምን እና እንዴት ተቆለፈበት? የሚል ቁጭት ያጭራል ። የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች ዝቅተኛ ከሆነባቸው ምክንያቶች መካከል የህብረተሰቡ የመጎብኘት ልምድ አነስተኛ መሆን ፤ ለጉብኝት ትኩረት አለመስጠት ፤ የፍላጎት ማነስም እንዲሁም የፋይናንስ እጥረት በዋነኝነት ተጠቃሽ ናቸው።





ቢሮው የሀገር ውስጥ የጉብኝት ባህልን ለማሳደግ ለዘርፉ ባለሙያዎች ሥልጠና ሰጥቷል

በውጭ ሀገር ቱሪስቶች ላይ የተንጠለጠለውን የከተማውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ በሀገር ውስጥ ቱሪዝም ስትራተጂ መቃኘት ይገባል። በመሆኑም የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እንቅስቃሴን ለማበረታታት ከዘርፉ ተዋናዮች ጋር በቅንጅት መሥራት እንዲሁም የሀገርህን እወቅ ክበባትን ማጠናከርና ማቋቋም ያስፈልጋል። የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የሀገር ውስጥን የጉብኝትን ባህል ለማሳደግ ከሀገርህን እወቅ ክበባት ጥምረት መሪዎች፣ የጉዞ ማህበራትና የዘርፉ ባለሙያዎች ጋር እየሠራ ይገኛል፡፡ ቢሮው የሀገር ውስጥን የጉብኝትን ባህል ለማሳደግ ለዘርፉ ባለሙያዎች ሥልጠና ሠጥቷል ፡፡

በወቅቱ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ማስፋፋት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሳምሶን አየናቸው እንደተናገሩት ፤ ቢሮው ለሀገርህን እወቅ ማህበራት ሙያዊ ድጋፍ በማድረግና በማስተባበር የከተማችን ማህበረሰብ አዲስ አበባን ለማወቅ የሚያስችል ተግባራትን እየሠራ ይገኛል። ለቱሪዝም ዕድገት ቁልፍ ሚና ላላቸው አካላት ሥልጠናውን መስጠቱ፤ ሀገር ወዳድ ትውልድን በማፍራት ረገድ ለሀገር ውስጥ የቱሪዝም ዕድገት ወሳኝ እንደሆነ ያምናል፡፡ በመሆኑም የሀገርህን እወቅ ክበባት ጥምረት ባለሙያዎች የከተማችንን የቱሪስት መስህቦች ለማስተዋወቅ እንዲያግዛቸው ለዘርፉ ተዋንያን አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

አቶ ሳምሶን ፤ የጉብኝት ባህላችን እና የማስተዋወቂያ መንገዶቻችን ደካማ መሆኑን ገልፀው ፤ ለዚሁ ክፍተት ዘመናዊ የማስተዋወቂያ /ዲጂታል/ ዘዴዎችን በመጠቀም የመዳረሻዎችን ታሪክና ፋይዳ መገንዘብ አስፈላጊ እንደሆነ አስታውቀዋል።

"ቱሪዝም ከአይሲቲ፣ ከማዕድን፣ ከግብርናና ከማኑፋክቸሪንግ ጋር ትኩረት ከተሰጠው የኢኮኖሚ ከፍተኛ አንቀሳቃሽ አንዱ ነው " ያሉት አቶ ሳምሶን፤ በቱሪዝም መዳረሻዎች እና በሀገር ውስጥ ቱሪዝም ማስፋፋት ልማት ሥራ ላይ ቢሮው በትኩረት እየሠራበት መሆኑን አንስተዋል። ዳይሬክቶሬቱ በባለፉት ሶስት ወራት ውስጥ በከተማዋ ባሉ ፓርኮች እና የሕዝብ መዝናኛ ቦታዎች ባለሙያዎች እና አጠቃላይ በቱሪዝም ዘርፍ ላሉ አካላት በዘመናዊ አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ሥልጠና መስጠቱንም አስታውቀዋል።

የከተማችን ነዋሪዎች ተወስነው በሚኖሩበት ብቻ ሳይሆን ተዘዋውረው መዲናችን ያላትን የቱሪስት ፀጋዎች መጎብኘትና የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን በማስፋፋት የጎብኚ ቁጥርን መጨመር እንደሚገባ የአዲስ አበባ የሀገርህን እወቅ ክበባት ጥምረት ፕሬዚዳንት አቶ ብርሃኑ ወዳጆ ገልፀዋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## «ለሀገር ዕድገት ከቴክኖሎጂ እና ካፒታል የበለጠ የሰው ኃይል በጣም ወሳኝ ነው»

- ገመቹ ዋቅቶላ ዶ/ር

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

ገመቹ ዋቅቶላ (ዶ/ር)፤ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በቢዝነስ አድምኒስትሬሽን፣ ማስተርሳቸውን በማርኬቲንግ ማኔጅመንትና ኢንተርናሽል ቢዝነስ ነው፡፡ ሦስተኛ ዲግሪያቸው (ዶክትሬታቸው) ደግሞ ሂዩማን ካፒታል ዲቨሎፕመንት ላይ ነው የሠሩት፡፡ በአሁኑ ወቅት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ መምህር ሲሆኑ ረዳት ፕሮፌሰር ናቸው፡፡ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከማቅናታቸው በፊትም በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ከሌክቸረር እስከ ረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ በመምህርነት አገልግለዋል፡፡ የአይ ካፒታል አፍሪካ ኢንስቲትዩት መሥራችና ዋና ሥራ አስፈፃሚም ናቸው፡፡ በዛሬው ዕትማችን ሂዩማን ካፒታል፣ ቴክኖሎጂ፣ ፋይናንስ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በማንሳት ቆይታ አድርገናል፡፡



**አዲስ ዘመን፡-ሂዩማን ካፒታል ምን ማለት ነው?**

**ገመቹ ዶ/ር፡-** በሀገር ሆነ በተቋም ደረጃ ስንወስድ ሃብቶች አሉን። አንድን ተቋም ውጤታማ የሚደርጉት ደግሞ በርካታ ሃብቶች ተደምረው ነው። ለአብነትም የፋይናንስ፤ የቴክኖሎጂ ብሎም የሰው ኃይል አቅም አለ። በአጠቃላይ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ሃብቶች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የሰው ኃይል ነው። አንድ ድርጅት ውጤታማ የሚሆነው በርካታ የሠው ኃይል ስለተቀጠረ አይደለም። ዕውቀት፣ ክህሎትና አስፈላጊውን ባሕሪ ወደ ሥራ ቦታ ይዞ ሲመጣ እና ለተቋም የአጭር እና ረጅም ጊዜ ውጤታማነት ማበርከት ሲችል የዚያ ተቋም ሃብት ይሆናል። የሰው ኃይል ልማት በደንብ ሲሠራበት ካፒታልም ይሆናል ማለት ነው።

የሰው ኃይል ልማት በጣም ወሳኝ ነው። ከጊዜ ጋር አያይዘን ብንመለከት ከዚህ ቀደም ሲል ድርጅቶች ውጤታማ የሚሆኑትና ተሞክሮዎች የሚያሳዩን ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያላቸው በተወዳዳሪነት ንፅፅራዊ እይታ ተጠቃሚ ናቸው። በተለያዩ ወቅቶች የስኬት መለኪያ ፋይናንስ ሆኖ ነበር። በቀመጠል ቴክኖሎጂ መጣ። ስለዚህ ቴክኖሎጂ በፋይናንሱ መግዛት የቻለ ተቋም ተወዳዳሪ መሆን ችሏል። ቴክኖሎጂ ለውጥ አመጣ ማለት ነው። በዚህ ዘመን ፋይናንስ እና ቴክኖሎጂ በቀላሉ ይገኛሉ።

ለአብነት የዛሬ 10 ዓመት ስልክ መግዛት እና ዛሬ ላይ ስልክ መግዛት አንድ ዓይነት አይደለም። በአሁኑ ወቅም ባንኮች ማንኛውንም ቴክኖሎጂ መግዛት ይችላሉ። ነገር ግን ልዩነቱን እያመጣ ያለው ዕውቀት ነው። አሁን በእውቀት የሚመራ ዓለም ውስጥ ነን። የዕውቀት ኢኮኖሚ ላይ ነን። ስለዚህ ስኬትና ተወዳዳሪነት የሚመጣው እውቀት ላይ ተመሥርተን ሥንሰራ ነው። ዕውቀትና ፈጠራ የሚመነጨው ደግሞ ከሰው ኃይል ነው። ስለዚህ ከቴክኖሎጂም እና ዕውቀት በበለጠ የሰው ኃይል በጣም ወሳኝ ነው። ጠንካራ ተወዳዳሪ የመሆንና ያለመሆን ልየታ የሚመጣው ከሰው ኃይል ነው ማለት ነው።

ስለዚህ ይህን ማድረግ የሚችል፣ የተፈጠረን አዳዲስ ነገር ወደ ገበያ የሚያመጣ፣ በተፈለገው ደረጃ ማምረት የሚችል፣ ደንበኛን በሥርዓት የሚያስተናግድ እና ቴክኖሎጂን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችለው የሰው ሃብት ነው። አንድ መታወቅ ያለበት ጉዳይ የሰው ኃይል ስንል ስለቁጥር እያወራን አይደለም። በበርካታ ሠራተኞች ውስጥ ቢሆን ለውጥ የሚፈጥሩ፣ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ፣ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ፣ ደንበኛን በአግባቡ የሚያስተናግዱ፣ የረጅም ጊዜ እቅድና ስትራቴጂ የሚነድፉ እና መሰል ሠራተኞችን እንዴት መፍጠር ይቻላል ለሚለው ሂዩማን ካፒታል ዲቨሎፕመንት ቁልፍ ሆኖ መጥቷል።

ስለዚህ ዛሬ ተወዳዳሪነት ብቁ ሰው ሃብት ያለው እና የሌለው መካከል ነው። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት ባንክ ብንሄድ አገልግሎት የምናገኘው ወይ በሰው ወይ ደግሞ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ነው። ዲጂታል ዓለምን የፈጠረው ሰው ነው፤ ይህን በአግባቡ እንድንጠቀም የሚያግዘንም ሰው ነው። ለዚህ ሁሉ ወሣኙ የሰው ሃብት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከነበረዎት የሥራ ልምድ እና ሂዩማን ካፒታል ዲቨሎፕመንት የትግበራ ሁኔታን ከኢትዮጵያ አኳያ እንዴት ይመለከቱታል?**

**ገመቹ ዶ/ር፡-** አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ከሁኔታዎች ጋር ለማነፃፀር ስንሞክር፤ 120 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሀገር ናት። ይህ ማለት ግን ከዚህ ሕዝብ ጋር ሙሉ ለሙሉ የሚመጥን ሥራ እንሠራለን ማለት አይደለም። በእርግጥ ሕዝብ ሲበዛ ጥቅም አለው። ከብዛት ውስጥ ጥራት ያለውን ለማግኘት ያግዛል። ይህን የሚወስነውና ያንን ለማፍራት የሚያግዝ ሥራ መሠራት አለበት። ነገር ግን ዋናው ዓላማ ሰዎችን ምርታማ ዜጋ ማድረግ ነው። በአንድ ድርጅት ውስጥ 100 ሠራተኞች መኖራቸው ሳይሆን የተቋሙን ቀጣይነትና ውጤታማነት የሚወስነው ሠራተኞቹን ብቁ ማድረግ ነው። ለአብነት በተመሳሳይ አንድ ቻይናዊ ፋብሪካ ውስጥ በአንድ ሰዓት የሚሠራውና አንድ ኢትዮጵያዊ በሰዓት የሚሠራው ማነፃፀር ብንጀምር ልዩነቶች አሉ።

ፈጠራንም ብንመለከት እዚህ ሀገር ውስጥ ፈጠራ በምን ደረጃ እየተበራከተ ነው የሚለውንም ማየት ተገቢ ነው። ስለዚህ ማነፃፀሪያችን ብዙ ነገር ነው። የተቋማት ወሳኝ መወዳደሪያቸው ሂዩማን ካፒታል ዲቨሎፕመንት ነው ካልን የእኛ ተቋማት ምን ያክል ተወዳዳሪ ናቸው የሚለውን ማወቅ ተገቢ ነው። እኛ አውሮፓ እና ኤዥያ ሳንሄድ ጎረቤት ሀገር ኬኒያ ጋር ካለው ጋር ብናነፃፅር በፋይናንስ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ልዩነቶች አሉ። አንድ ማወቅ ያለብን ግን በደንብ ከተሠራበት ሁኔታዎችን በተሻለ ደረጃ መለወጥ የሚያስችል አቅምም አለ።

የሕዝብ ቁጥር ጠቃሚ ነው፤ ግን ይህን በአግባቡ ለመጠቀም ትምህርት፤ ሥልጠና እና አስፈላጊ ባሕሪያት ሥርዓት የሚዳብሩበትን መንገድ እስከዘረጋን ድረስ የተሻለ ለውጥ ማምጣት እንችላለን። ግን ንፅፅራችን እንደየሁኔታው ይለያያል። በመሆኑም በደምሳሳው ሁሉንም ማነፃፀር ያስቸግራል። አንዱን ኢንዱስትሪ ከሌላው ጋር ለማነፃፀር የመሪነት አቅም፣ የፈጠራ ብቃትና አቅም፣ አምራችነት፣ አመለካከት በተለይም ነገን አሻግሮ የመመልከት ብቃት ምን ይመስላል የሚለውንና ዓለምን የምንረዳበት መንገድ ምን ይመስላል የሚለውን ማነፃፀር ተገቢ ነው። ከዚህ አኳያ በብዙ ሴክተሮች ብንወስድና ሥርዓታቸውን ብንመለከት፣ ሰዎች የሚለሙበትና የምናሳድግበት መንገድ ብንወስድ በርካታ ነገሮችን መገንዘብ እንችላለን።

ሁላችንም የሥርዓት ውጤት ነን። ስለዚህ ፈጠራን የሚያበረታታ ሥነ ምሕዳር አለን ወይ፣ ሌሎች የፈጠሩትንም ቢሆንም በአግባብ የመጠቀም አቅማችን ምንድን ነው የሚለውን በጥልቀት ማየት ይገባል። እንደ ኢትዮጵያ ግን ብዙ የሚቀሩን ነገሮች መኖራቸውን መጠቆም እፈልጋለሁ። መሥራት እየተገባን ብዙ ያልሠራናቸው ነገሮች አሉ። በተለይም ከሰው ሃብት ኃይል ልማት ጋር በተያያዘ ካፒታል ጋር ገና ብዙ መሥራት ይገባል። ይህን ስንል ሌሎችስ ሀገራት እንዴት ማድረግ ቻሉ፣ እኛስ በምን ደረጃ ላይ እንገኛለን ወደሚለው ንፅፅር እንገባለን። ይህ ከሆነ ብዙ አገራት ብዙ ነገር መፍጠር የሚችሉበት ሥነ ምህዳር ላይ መሆናቸውን እንረዳለን። የትምህርት ሥርዓታቸው፣ ሥልጠናቸው እና በድርጅቶች ውስጥ ከገቡ በኋላ ራሳቸው የሚያሳድጉበት መንገድ ሥርዓት ገንብተዋል። ሌሎች ሀገራት ይህን ለማድረግ ብዙ ርቀት ሄደዋል። ይህን ሳወራ ሀገርን ከሀገር ጋር እያነፃፀርኩ ሳይሆን የሰው ሃብት ሀገርን እንደሚገነባ፤ ድርጅቶችን ተወዳዳሪ እንደሚያደርግ ለማንሳት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በእኛ ሀገር ይህን መሠረት አድርገው የተሠሩ የጥናት ውጤቶች ምን ያሳያሉ?**

**ገመቹ ዶ/ር፡-** የሰው ሃብት ልማት ሰፊ ነው። በሀገር ደረጃ ማየት እንችላለን። በሀገር ደረጃ የትምህርት ሥርዓታችን፣ እንደ ሕዝብ፣ እንደ ሀገር፣ እንደ ሴክተር ደግሞ ግብርና ፋይናንስ የመሳሰሉት ብለን ልናነሳ እንችላለን። በሀገር ደረጃ በትምህርት ሥርዓት ሰው የሚለማበትን ጉዳይ ልናነሳ እንችላለን። ስለዚህ በርካታ ጥናቶች አሉ። ለአብነት ፋይናንስ ላይ ትኩረት አድርገን ብናይ፤ የኢትዮጵያ እና የሌሎች ሀገራት የፋይናንስ ሴክተር ተወዳዳሪነታቸው፣ አገልግሎት አሰጣጣቸው፣ ቴክኖሎጂ አጠቃቀማቸው፣ የሰው ኃይል እና የአመራር ብቃታቸው ብለን ማነፃፀር እንችላለን።

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ሴክተር ከዕውቀት አንፃር ሲታይ የተከፈተ አይደለም፤ የተዘጋ ሴክተር ነው። ይህ ማለት ደግሞ የሰው ኃይሉም የዚያኑ ያክል በሀገር ውስጥ ትምህርት፣ ሥልጠና እና ማዕቀፍ ውስጥ የተያዘ ነው። አልፎ አልፎ የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ ሄዶ ከማየት የዘለለ ዕይታ የለውም። ሌሎች ሀገራት በዚህ ረገድ ብዙ ርቀት ተጉዘዋል። ለምሳሌ ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው መሠረት የፋይናንስ ሴክተሩ ሁለት ከመቶ የሚሆን በጀታቸውን ለሰው ኃይል ልማት እንዲያውሉት ነው። ይህ በጣም ትልቅ አኃዝ ነው፤ እንደ ሀገርም ትልቅ ውሳኔ ነው። ይህ የፋይናንስ ሴክተር ትልቅ ቀጣሪ ከመሆን በዘለለ ለኢትዮጵያ ዕድገት ትልቅ አበርክቶ አለው። ሌላው ደግሞ ይህ ሴክተር ከሌላው አኳያ ሲታይ በጣም የተማረ የሰው ኃይል ይፈልጋል። ስለዚህ የተማሩ፣ ፈጠራን የሚያበረታቱ እና ጠንካራ አመራሮችን የምንፈልገውና እንዲሁ የምናገኘውም ከፋይናንስ ሴክተር ውስጥ ነው።

እኛ ሁሌም የምንጠይቀው ይህ የፋይናንስ ሴክተሩ ሁለት ከመቶ የሚሆን በጀታቸውን ለሰው ኃይል ልማት እንዲያውሉት የተወሰነው ምን እየሠሩበት ነው፤ በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እየዋለ የሚለው ነው። ለምሳሌ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ አለ። ባደጉትና ጠንካራ ባንክ ሴክተር ባላቸው ሀገራት ስንመለከት 70፤ 20፤ 10 የሚባል ጥናት አለ። እኛም ተቋማት እንዲተገብሩት የምንፈልገው ነው። 70፤ 20፤ 10 የሰው ኃይል ልማት አካሄድ ማለት 70 ከመቶ ሥልጠናና ልማት መካሄድ ያለበት በሥራ ቦታ ነው። ሥራው እየሠሩ መማር አለባቸው። ይህ ምርጥ ማሠልጠኛ ቦታ የሚባለው ሰው በሚሠራው ቦታ እየሠራ ስለሆነ ነው። 20 ከመቶ የሰው ኃይል ልማት አካሄድ ደግሞ ሰዎች እርስ በእርሳቸው ባላቸው ግንኙነት ይማራሉ። 10 ከመቶ የሰው ኃይል ልማት አካሄድ ደግሞ ከሥራ ቦታ ውጭ ወጣ በማለት ወርክሾፕ፣ ኮንፈረንስንና የመሳሰሉትን ያካትታል።

ይህ በጥናት የተደገፈ እና ብዙዎች ውጤታማ የሆኑበት ነው። እኛ ይህን መሠረት አድርገንና

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# «ለሀገር ዕድገት ከቴክኖሎጂ እና...

ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው መሠረት የፋይናንስ ሴክተሩ ሁለት ከመቶ የሚሆን በጀታቸውን ለሰው ኃይል ልማት እንዲያውሉት የሚለው መነሻ በማድረግ ረገድ ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ ጥናት አካሂደን ነበር። በዚህ አሠራር መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ እያንዳንዳቸው ባንኮች ከ50 ሚሊዮን እስከ አንድ ቢሊዮን ብር የሚበጅቱ አሉ። ነገር ይህን ገንዘቡን እንዴት እያወጡት ነው? 70፤ 20፤ 10 ሥርዓትን ይከተላሉ ወይ? ብሎ ለማየት ተሞክሯል። አሁን ባለው አሠራር 90 ከመቶ በላይ የእያንዳንዱ ተቋም ኢንዱስትሪን ጨምሮ የሚውለው 10 ከመቶ መዋል የነበረበት ወይንም እነዚህ ተቋማት 90 ከመቶ የሚሆነውን ሥልጠና የሚሰጡት በወርክ ሾፕ፣ ኮንፈረንስና በመሳሰሉት ነው።

ይህ ጥናቶች ከሚመክሩት በተቃራኒ ሆኗል። ይህ ማለት 90 ከመቶ የሚሆነው የሕዝብ ሃብት 10 ከመቶ አበርክቶ ባለው ጉዳይ ላይ እየዋለ ነው ማለት ነው። ይህ ክፍተት በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ያለ ሳይሆን በበርካታ ሀገራት የሚስተዋል ነው። በእርግጥ መሰል ችግሮችን በአንድ ጊዜ ማቃለል አይቻልም። ሆኖም ብሔራዊ ባንክ በዚህ ላይ በትኩረት መሥራት ይጠበቅበታል። 70፤ 20፤ 10 ወይንም አዲሱ የሰው ሃብት ልማት አሠራር ነው። ይህ በፋይናንስ ሴክተር ብቻ ሳይሆን በኢንዱስትሪ፣ በሲቪል ሰርቪስ እና በሌሎች ሴክተሮችም ይሠራል። ስለዚህ ይህ እንደሃገር መተግበር አለበት።

ሲቪል ሰርቪስ ተቋማት ውስጥ መተግበር አለበት፤ ፋይናንስ ሴክተር ውስጥ የትኛውም ቦታ የሚሠራ አሠራር ነው። ይህን ስናደርግ ወደ ፋይናንስ ሴክተሩ ስንመጣ ሁለት ክፍተቶች ነው የምናየው። አንደኛ የሥራ ላይ ሥልጠናው በእንደዚህ ዓይነት እየተካሄደ አይደለም። በዘልማድ የሚካሄደው ያለበጀት እንዲሁ ‹‹ስታራክቸርድ›› ያልሆነ ዝም ብሎ እንትና ጋ ቁጭ በልና ልምድ ውሰድ ዓይነት አሠራር፤ እንትና ጋ ቁጭ በልና እሱ የሚሠራውን እይ ተብሎ የሚሠራ ሥራ ውጤታማ አይደለም።

“ስትራክቸርድ ኦን ዘ ጆፕ ትሬንግ” የሚባል አሠራር አለ። የሥራ ላይ አሠራር ሥርዓት ራሱ ስትራክቸርድ ይደረጋል። ፕሮሰስ አለው። ሞጁል አለው፤ አሠልጣኞች አሉት። እነኝህ አሠልጣኞች ማን ናቸው? እዚያው ያሉ ሠራተኞች እንዴት ማሠልጠን እንዳለባቸው የሠለጠኑ ልምድ ያላቸው መሆን አለበት። የራስህን ሰው ነው የምትጠቀመው። ይህ ሲደረግ ሲስተም ነው የሚዘረጋው። በየጊዜው ሰዎች እየሠለጠኑ ይወጣሉ።

ሁለተኛው የሥራ ቦታ ሥልጠና በጀት የለውም። በጀት ያለው የቱ ነው? ሆቴል ሂደህ ውጭ ሄደህ የሚሠለጠን ሥልጠና ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ የሰው ኃይል በተለይ ፋይናንስ ሴክተር ላይ እንዲቀየር ከተፈለገ የሠው ኃይል እንዴት ይለማል የሚለውን አመለካከታችን መቀየር አለበት። ስለዚህ ቅድም እንዳልኩህ 90 በመቶ ለትምህርት የሚበጀት በጀት ወይ ብክነት ነው። ወደ 20 ፐርሰንቱ ልምጣልህ፤ 20 ፐርሰንቱ ስትመጣ በልምድ (ኢንፎርማል) ነው የሚመራው።

በባንኮች ከሄድን ጥሩ የጀመሩት ሥራ አለ። ወደሌሎች ሀገራት ይሄዳሉ። ከሌሎች ሃገራት ጋር በመገናኘት ልምድ ይቀስማሉ። ምክንያቱም ልምድ መቅሰም ሌላ ሃገር መሄድ ያለባቸው እዚህ ሀገር ሆቴል ሄደው የሚሠለጥኑትን ሥልጠና መሆን የለበትም። ጃፓን እንደዚህ አደገች እያልክ ሦስት ቀን ክፍል ውስጥ አስቀምጠህ ብትነገረው ዋው! ሊልህ ይችላል። ኢንተርናላይዝ ግን አያደርገውም። ጃፓን ሂዶ ጃፓኖች እንዴት እንደሠሩት ፤የሠሩትን ማሽን ሲያይ፤ እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት ሲያይ የሆነ ነገር ይማራል።



**ኢንዱስትሪው በሰው እጦት ይሰቃያል እዚህ ጋ ለአንድ ሥራ 10ሺ፤ 30ሺ ሰው ለሥራ ቅጥር እያመለከተ ብቁ ባለሙያ ፈልጌ አጣሁ ይላል። ኢንዱስትሪው የምቀጥረው አጣሁ፤ የሚሆነኝ ሰው አጣሁ ይላል። ይህ በየጊዜው የምንሰማው ነገር ነው**

ግን እዚህ የሦስት ቀን ክላስ የሚያስፈልጋቸውን የግድ ውጭ መሄድ ላያስፈልጋቸው ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- የሰው ሃብት በዋናነት ከትምህርት ሥርዓት ጋር የሚያያዝ ነው። በዚህ ረገድስ ያለው ምን ይመስላል?**

**ገመቹ ዶ/ር፡-** የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት መንገዱን የሳተ ነው። ከኢንዱስትሪው ጠቀሜታ አንፃር ከመዘነው ትልቅ ክፍተት አለበት። አሁን የኢትዮጵያን የትምህርት ሥርዓት ኢንዱስትሪው ቀድሞታል። በማስተርስም፣ በመጀመሪያ ዲግሪም በለው ኢንዱስትሪው በብዙ እርቀት ነው ያሉት። ቴክኖሎጂን ከወሰድክ ዩኒቨርሲቲዎች የሌላቸውን ቴክኖሎጂ ዘመናዊ የሆነውን ቴክኖሎጂ ኢንዱስትሪው አለው። በልምድም ከወሰድን ኢንዱስትሪዎች ዛሬ የሚሠሩት ዓለም ዛሬ የደረሰችበትን አሠራር ስለሆነ ኢንዱስትሪዎች ይበልጣሉ። በሊደር ሺፕ አቅምም ኢንዱስትሪዎች ይበልጣሉ። አሁን ላይ ያለው የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ኢንዱስትሪን ማብቃት ሳይሆን ከኢንዱስትሪው መማር ነው ያለበት።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ አልተናበበም ማለት ነው?**

**ገመቹ ዶ/ር፡-** የሰው ሃብት ገበያ የሚመራው በፍላጎት እና አቅርቦት ነው። አቅራቢው ማን ነው? የትምህርት እና የሥልጠና ተቋማት ናቸው። የትምህርት ተቋማት ማምረት ያለባቸው ገበያው የሚፈልገውን ነው። ገበያው የሚፈልገውን ታመርታለህ እንጂ አምርተህ ቢገዛኝም ባይገዛኝም ብለህ ወደ ገበያ ዝም ብለህ አትለቅም። የእኛ የትምህርት ሥርዓት እንደዚያ ነው። የሚገዛ ኖረም አልኖረም እያመረተ ገበያ ውስጥ ነው የሚያራግፈው።

ኢንዱስትሪው በሰው እጦት ይሰቃያል እዚህ ጋ ለአንድ ሥራ 10ሺ፤ 30ሺ ሰው ለሥራ ቅጥር እያመለከተ ብቁ ባለሙያ ፈልጌ አጣሁ ይላል። ኢንዱስትሪው የምቀጥረው አጣሁ፤ የሚሆነኝ ሰው አጣሁ ይላል። ይህ በየጊዜው የምንሰማው ነገር ነው። ሳፋሪኮም በቅርቡ ሥራ ቅጥር አውጥቶ የተመዘገበው ሰው ብዛት የጉድ ነው። ባንኮችም ሰው ይፈልጋሉ። እኛም በአቅማችን እንፈልጋለን። ነገር ግን ገበያው የሚፈልገው ብቁ ሰው አይገኝም። ብዙ ድርጅቶች ውስጥ ብንሄድ ቦክስ ፈጥረው ቦክሶቹ ባዶአቸውን የሚቀጥር ሰው አጥተው ተቀምጠዋል። ይህ ማለት ምን ማለት ነው? የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የሰው ሐብት ልማት አካሄድ የለንም ማለት ነው።

የኢትዮጵያ የሰው ልማት አካሄድ ስንመለከት አቅርቦት ላይ የተመሠረተ እንጂ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ አይደለም። እነዚህን የሚሠሩ ተቋማትን ከተመለከትክ በራሳቸው ደሴት ላይ ያሉ ነው የሚመስላቸው። ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በራሳቸው ደሴት ላይ ቁጭ ብለው፤ የቲቪቲ ተቋማትንም ብትጨምር ኦኮፔሽናል ስታንዳርድ ብለው የሚፈጥሩት ቁጭ ብለው እራሳቸው ናቸው። ኢንዱስትሪው አይደለም እየፈጠረ ያለው። ይህ ማለት ኢንዱስትሪው የሰው ሃብት የተራበ ኢንዱስትሪ ነው። የሰው ሃብት ይህን ካልቀየረ እና በፍላጎት የሚመራ ካላደረግነው የኢትዮጵያ የሰው ሃብት ልማት ለሚቀጥሉት አስርተ ዓመታት እንደተራበ ይቆያል። የሆነ ጊዜ ላይ ከውጭ ለማምጣት የሚጠበቅበት ጊዜ ላይ እንደርሳለን። ወይም ኢንዱስትሪዎቻችን በሰው ማጣት የሚሰቃዩበት ጊዜ ላይ እንደርሳለን።

አሁን ላይ በሲሚንቶ ፋብሪካዎች በባንኮች እና መሰል መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞችን መቀማማት አለ። ስንት ሥራ ፈላጊ ባለበት ሀገር ሠራተኛ መቀማማት አለ ቢባል የሚገርም ነው። ይህ ብክነት ነው። ምክንያቱም ሃገር ኢንቨስት አድርጋባቸዋለች። እንደገና ኢንዱስትሪው ደግሞ ኢንቨስት ያደርግባቸዋል። ይህን ለማስተካከል በሀገር ደረጃ ትልቅ የሆነ የተደራጀ ፖለሲ ያስፈልጋል። በሴክተር ደረጃም ትልቅ ሥራ ያስፈልጋል።

ከፊታችን አንድ እውነታ አለ። ከዩኒቨርስቲ የሚወጡ ሰዎች ዲግሪ ይዘው በሚወጡበት ጊዜ ጊዜውን የዋጀ ዕውቀት ይዘው መሆን አለበት። መምህራንም ብንመለከት ኢንዱስትሪ ምን እንደሆነ የማያውቁ እና ኢንዱስትሪ ውስጥ ገብተው ሠርተው የማያውቁ መምህራን አሉ። ቢዝነስ ምን እንደሆነ የማያውቁ፤ ስለቢዝነስ ሲያስተምሩ፣ ስትራቴጂ ምን እንደሆነ የማያውቅ መምህር ስትራቴጂ ሲያስተምር ታገኛለህ። በመሆኑም ትልቅ የአቅም መበላለጥ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- ይህን ለማስተካከል ምን መደረግ አለበት?**

**ገመቹ ዶ/ር፡-** ይህ እንዳለ ሆኖ በባሕሪው እውቀት በቴክኖሎጂ ምክንያት ቀደም ሲል የነበረ ዕውቀት ዋጋ ቢስ እየሆነ እየመጣ ነው። የትምህርት ሥርዓታችን ዲግሪ መያዝ እና አለመያዝ ልዩነት የሌለበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። አንድ ልጅ ዲግሪ ተምራ ሊስትሮ ስትሠራ የሚያሳይ አርቲክል አነበብኩ። ይህች ልጅ እንዲሁ ነው አራት ዓመት ያባከነችው። እዚህ ላይ በሚቀያየር ዓለም ውስጥ ዜጎች እንደዜጋ አስፈላጊ የምንሆነው ምን ብናደርግ ነው የሚለውን መገንዘብ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ትናንት የነበረኝ ዕውቀት ዛሬ አያስፈልገኝም። ስለዚህ ‹‹ሪስኪሊንግ፣ አፕስኪሊንግ›› ተጀምሯል። እንደ ሀገርም ‹‹ሪስኪሊንግ፣ አፕስኪሊንግ›› ወደሚባሉ ነገሮች ላይ መሄድ አለብን።

የቴክኖሎጂ እና የፋይናንስ ሴክተር ለዚህ የተጋለጠ ነው። አሠራሩ ሁሉ እውቀትን መሠረት ያደረገ ነው። ክህሎትን መሠረት ያደረገ ነው። ቴክኖሎጂን መጠቀም አለብን። ፋይናንሻል ቴክኖሎጂ የምንላቸው ዲጂታል ሶሉዩሽን የምንላቸው በየቀኑ ሲፈበረኩ ነው የሚውሉት። ይህንን ተጠቅሜ ደንበኛን የማላረካ ከሆነ ራሴ ብቁ አይደለሁም ማለት ነው። ቴክኖሎጂን እገዛለሁ እንጂ መጠቀም እየቻልኩ አይደለም። ትልቅ ገንዘብ አውጥቼ ቴክኖሎጂ እየተለማመድኩ እያለ አዲስ ቴክኖሎጂ ይመጣል። ሌላውን እንተወውና የደንበኞች ፍላጎትም በኢትዮጵያ በጣም በፍጥነት እየተቀያየረ ነው። የደንበኛ ፍላጎትን ማርካት አልተቻለም። ይህን ለማደርግ ሥርዓት ካለበጀንለት፤ የትምህርት ሥርዓታችንን ካልቀየርን፣ ኢንዱስትሪው የሰው ኃይል ልማቱን ካልመራው፣ኢንዱስትሪው የሚመራበት ፖለሲ ፍሬም ወርክ ካልተፈጠረ መቀየር አይቻልም የሚል ሐሳብ አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- የዝግጅት ክፍላችን እንግዳ ሆነው ሙያዊ ማብራሪያ ስለሰጡን አመሰግናለሁ።**

**ገመቹ ዶ/ር፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
Berhanena Selam Printing Enterprise

## ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት የ2015 በጀት ዓመት ሒሳቡን በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ (IFRS) መሰረት አዘጋጅቶና በውጭ ኦዲተር አስመርምሮ ያጠናቀቀ ሲሆን የሒሳብ መግለጫው እንደሚከተለው ቀርቧል።

**BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE**
**STATEMENT OF PROFIT OR LOSS AND OTHER COMPREHENSIVE INCOME**
**FOR THE YEAR ENDED 07 JULY 2023**

**Currency: Ethiopian Birr**

| | Notes | 07 July 2023 | 07 July 2022 |
|---|---|---|---|
| Revenue | 4 | 1,073,615,022 | 679,903,126 |
| Cost of sales | 5 | (489,412,282) | (327,998,126) |
| **Gross profit** | | 584,202,740 | 351,905,000 |
| Other operating income | 6 | 42,599,580 | 38,819,456 |
| Termination benefit expenses | 8 | 2,019,207 | 1,505,159 |
| General and administration expenses | 7 | (240,034,711) | (133,620,850) |
| Impairment losses on trade Recivables | 13.2 | (4,142,073) | (2,525,144) |
| **Operating profit** | | 384,644,744 | 256,083,622 |
| Finance costs | 8 | (3,147,677) | (4,234,330) |
| **Profit before tax** | | 381,497,067 | 251,849,292 |
| Income tax expense | 9(b) | (130,975,564) | (75,464,701) |
| **Profit for the year** | | 250,521,503 | 176,384,591 |
| **Other comprehensive income** | | | |
| Net other comprehensive income to be reclassified to profit or loss in subsequent periods | | - | - |
| Net other comprehensive income not to be reclassified to profit or loss in the subsequent period. | | - | - |
| **Total comprehensive income for the year net of tax .** | | **250,521,503** | **176,384,591** |

The notes on page 7 to 38 with appendix a and b are an integral part of these financial statements

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## የምሥጋና በረከቱ

**የመነሻ ወግ፤**

ኅዳር በበርካታ የዓለም ሀገራት የሚታወቀው "የምሥጋና ወር" እየተባለ ነው:: ከሰሜን አሜሪካ እስከ ላቲኑ የዓለማችን ክፍል፣ ከሩቅ ምሥራቅ እስከ አውሮፓና የእኛይቱ አህጉር አፍሪካ ድረስ ብዙ ሀገራት "የኅዳር ቀናትን አየር የሚያጥኑት" በምሥጋናና በመመሥጋገን ነው:: በእኛ ሀገር የኅዳር ወር በአብዛኛው የሚታጠንለት ከመቶ ዓመት በፊት ተከስቶ በርካታ ሺህ ወገኖቻችንን በፈጀው ወረርሽን ወይንም ክፉ ቀን እየተባለ የሚጠራውን "በላ" (Spanish flue) በማስታወስ ነው::

በተጠቀሱት ሀገራት በኅዳር ወር ውስጥ የሚከበረው ብሔራዊ የምሥጋና ቀን (Thanksgiving Day) የቀናት መለያየት ቢታይበትም የዝግጅቶቹ ድምቀት፣ በዓሉን በሚያከብሩ ዜጎች ዘንድ የሚስተዋለው ደስታና መፍለቅለቅ፣ በጋራ የሚታደሙበት ማዕድ ሞገስና ክብር የሁሉም ሀገራት የጋራ መለያ ተደርጎ ይቆጠራል::

በአሜሪካ፣ በካናዳ፣ በጃፓን፣ በጀርመን፣ በአውስትራሊያ፣ በግሪናዳ፣ በቅዱስ ሉቺያ፣ በላይቤሪያ፣ በብራዚል፣ በፊሊፒንስና በሌሎችም በርካታ ሀገራት በኅዳር ወር የሚከበረው የምሥጋና ቀን ታሪካዊ አመጣጥ የተለያየ ቢሆንም ዓላማው ግን እጅግም ልዩነት የማይስተዋልበት ተመሳሳይና ተቀራራቢ ነው::

ፈጣሪ የገበሬዎቻቸውን አዝመራ ስለባረከላቸው ያመሠግናሉ:: ተፈጥሮ በተለያዩ ቀለማት ዛፍ ቅጠሉን አሽሞንሙና ለምታሳምራቸው የመፀው ወራት በሠላም ስለመድረሳቸው ያመሠግናሉ:: የመፀው ወራት ልክ እንደ እኛው ሀገር (ከመስከረም 26 እስከ ታኅሣሥ 25 እንደሚዘልቀው) በሌሎች ሀገራትም እንዲሁ የኅዳር ወር የአበባና የተፈጥሮ ውበት ጎልቶ የሚደምቅበትና የሚታይበት ወር ነው። ዛፎች በተለያዩ ኅብረ ቀለማት አብበውና ፈክተው ማየት ስሜትን በሐሴት ያረሰርሳል::

ይህም ብቻ አይደለም:: ሀገራቱ ሰላምና መረጋጋት የሕዝባቸው ትሩፋት ስለሆነ ያመሠግናሉ። የተራራቀ ቤተሰብ ከየቦታው ተሰባስቦ በፍቅር ማዕድ የሚቆርስበት በዓል በመሆኑም ያመሠግናሉ። የምሥጋናቸው ዓይነትና ብዛት፣ የአከባበራቸው ዘይቤም እንደየሀገራቱ ባህልና ወግ መሠረት የሚከናወን ቢሆንም የሚፈጥረው ስሜትና ድባብ ግን ሁሉም ሀገራት የሚጋሩት የጋራ መገለጫቸው ነው::

ይህ ጸሐፊ በኅዳር አራተኛው ወር "የምሥጋና ቀን - Thanksgiving day" የብሔራዊ ክብር ተጎናጽፎ በሚከበርበት በአሜሪካ ሀገር በቆየባቸው ዓመታት በምን ምክንያት ሳምንቱና ዕለታቱ በደማቅ በዓልነት እንደሚከበሩ በንባብ ካገኘው ዕውቀት በተጨማሪነት ይኖርበት በነበረው ክፍል ግዛት ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ወዳጆቹን የቃል ምሥክርነት እንዲሰጡት መጠየቁን ያስታውሳል:: የተሰጠው የቃል ትረካም የሚከተለውን ይመስላል::

"በሚኒሶታ ክፍለ ግዛት የሰፈሩት የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚ ቅድመ አያቶቻችንና ምንጅላቶቻችን ኑሯቸው እንዲህ እንደ ዛሬው ያማረና የተሳካላቸው አልነበሩም። ክፍለ ግዛቱ በክረምት ወራት ከሚጥለው የበረዶ ዶፍ የተነሳ እንኳንም ሊኖርበት ቀርቶ ለአንድ ቀንም ቢሆን የሚቆይበት አልነበረም:: እንደዛሬው የረቀቀ ሥልጣኔ ባልነበረበት በዚያ "የኋላ ቀርነት ዘመን" ክረምት በመጣ ቁጥር ከፍተኛ የምግብ እጥረት ስለሚከሰት የተለመደ የክፍለ ግዛቱ መከራ ነበር::"

> **እንደ ሀገር ከተቆራኙን ብሔራዊ በሽታዎቻችን መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው አንዱ ችግራችን ለማመሥገንና ለመመሠጋገን ንፉግ መሆናችን እንደ ባሕል የተጣበቀ ደዌ ሆኖብን ይሆንን ብለን ብንጠይቅ ክፋት የለውም**

"ብዙ ዜጎችም ነፍሳቸውን ከክረምቱ ‹መቅሰፍት› ለማትረፍ ይጥሩ የነበረው የዱር ዳክዬዎችን (ተርኪ በመባል የሰየሟቸውንና ያላመዷቸውን ዶሮ መሰል ዝርያዎች) በማደንና የበረዶውን ግግር ተቋቁሞ የሚበቅለውን ድንች ‹ለነፍስ አድንነት› በመመገብ ነበር። ስለዚህም ያንን ክፉ ጥንታዊ ዘመን ለማስታወስና ፈጣሪን ለማመስገን ሲባል በዓሉ እንዲከበር ተወሰነ። በእነዚህ የምሥጋና ቀናት የሚቀርበው ማዕድም ሙሉ አካሉ እንዳለ ተጠብሶ የሚቀርበው የተርኪ ሥጋ የድንችና የበቆሎ ገንፎም ያንን ዘመን ለማስታወስ ታስቦ የሚዘጋጅ ማዕዳችን ነው::" በሀገራችን "አውጥ" የሚባለው ዓይነት የዱር ፍሬም ከማዕዳቸው ጋር አብሮ ሲቀርብ ተመልክቻለሁ::

የምሥጋና ቀናቱ ተከብረው የሚውሉት ከላይ በዝርዝር በቀረቡት ውስን ምክንያቶች ብቻም አይደለም:: በጋራ ማዕዳቸው ዙሪያ የተሰባሰቡት ልጆችና ወላጆችም ይመሠጋገናሉ:: በየመሥሪያ ቤቱም አለቃና ምንዝር ይደናነቃሉ:: ተማሪዎችና መምህራን ይሞጋገሳሉ:: ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችም ሕዝባቸውን ያመሠግናሉ፤ ሕዝቡም የፌዴራል፣ የክልልና የአካባቢ መሪዎቻቸው ለፈጸሟቸው መልካም ተግባራት ምስጋና ያቀርባሉ።

ከዚሁ ጎን ለጎንም በዓሉ ሲከበር አንዳንድ ወጣ ያሉ ድርጊቶች በየሀገራቱ መስተዋላቸው አልቀረም:: ድርጊቶቹም የፌሽታቸውን ቀናት ለየት ስለሚያደርጉላቸው በልዩ ትዝታ የሚታወሱ ይሆናሉ። አንዱን ብቻ ለምሳሌ እናስታውስ። በቀደም ኅዳር 11 ቀን 2016 ዓ.ም የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የ2023 ዓ.ምን የምሥጋና ዕለታት ምክንያት በማድረግ በስጦታ ለእርድ ከቀረቡላቸው ሁለት ባለ ነጭ ላባ ግዙፍ ተርኪዎች መካከል ሁለቱ "እንዳይታረዱ ምሕረት አድርጌላቸዋለሁ" በማለት መግለጫ መስጠታቸው ይታወሳል::

ይህ ዜና በዓለም ብዙኃን መገናኛ የናኘውም እንደሚከተለው ተዘግቦ ነበር፡- "United States president Joe Biden pardoned two enormous white plumed Turkeys from Minnesota on Monday, granting liberty and Bell freedom from Thanksgiving dinner tables as Americans prepared for their annual feasts." ይህ ድርጊት ምሳሌነቱ በኅዳሩ የምሥጋና ወር እንኳንስ ለሰብዓውያን ዜጎች ቀርቶ ለእንስሳትም ቢሆን ፍቅርና ርህራሄ ማሳየት ተገቢ እንደሆነ መልዕክት ለማስተላለፍ ታስቦ ይመስላል::

**የአንጋፋው ቤተ ኅትመት ተጠቃሽ አርዓያነት፤**

በሀገራችን የኅትመት ታሪክ 102 ዓመታትን በማስቆጠር በዕድሜ የተባረከው የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በዚሁ በያዝነው ወር ኅዳር 8 ቀን 2016 ዓ.ም በምርት ዕቅድ አፈጻጸሙ ከፍተኛ ስኬት ያስመዘገበበትን የ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመት ውጤት ምክንያት በማድረግ በቅጥር ግቢው ውስጥ የሠራተኞችን ዓመታዊ በዓል አክብሮ ነበር::

በዕለቱ የማተሚያ ድርጅቱ ሠራተኞች ላስመዘገቡት ስኬታማ ውጤት የሥራ አመራር ቦርዱና የማኔጅመንት አባላት ምሥጋና አቅርበዋል። ሠራተኞቹም በበኩላቸው ለተገኘው ውጤት የማስተባበሩንና የአመራሩን ድርሻ በከፍተኛ ትጋት ለተወጡት የማኔጅመንት አካላትና የቦርድ አባላት ዋንጫዎችንና ልዩ ልዩ ሽልማቶችን በማበርከት ምሥጋናቸውን በምልአት ገልጸዋል::

መመሠጋገኑ ከተጠናቀቀ በኋላም የተቋሙ ሠራተኞች በራሳቸው ተነሳሽነት በ2016 ዓ.ም የበጀት ዓመት ሌትና ቀን በመሥራት የላቀ ውጤትና ስኬት ለማስመዝገብ በጋራ ቃል ኪዳን ገብተዋል:: ይህን መሰሉ አርዓያነት በሌሎች ተቋማት ዘንድም እንደ ባሕል ተወስዶ ቢለመድ የነገይቱ ኢትዮጵያ መልክ እንደምን ሊፈካ እንደሚችል ለመገመት አይከብድም::

በዚህ አጋጣሚ ይህ ዓምደኛ የኮሌጅ ትምህርቱን ባጠናቀቀበት ማግሥት የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ባልደረባ በመሆን የሥራና የኃላፊነትን "ሀ ሁ!" መማር ብቻ ሳይሆን የተቋሙን መላ ሠራተኞች ፍቅር ያተረፈበት፤ ዛሬም በሥራ አመራር ቦርድ አባልነት ለማገልገል ዕድል ያገኘበት ተቋም ስለሆነ ለዚህ አንጋፋ ድርጅት ሠራተኞች፣ የማኔጅመንትና የቦርድ አባላት ከፍ ያለ ምሥጋና እያቀረበ ለተጎናጸፉት ስኬትም ደስታውን በአክብሮት ይገልጻል:: የመመሠጋገን ትሩፋት ለተሻለ ውጤት የሞራል ስንቅ ስለሚሆን በስፋት ሊለመድ ይገባዋል የሚባለውም ስለዚሁ ነው:: ባሕር ማዶኞች "Thank you is the best prayer that anyone could say" የሚሉትም ውጤቱ ስለገባቸው ይመስላል።

**ሌላው የሚበረታታ አርዓያነት፤**

የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት በዚሁ በያዝነው ሣምንት ውስጥ "የሠላምና የምሥጋና ኮንፍረንስ" ኅዳር 25 ቀን 2016 ዓ.ም ለማካሄድ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን በኃላፊዎቹ በኩል ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል::

የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ሼህ ሡልጣን ሐጂ አማን ኤባ ፕሮግራሙን አስመልክተው ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል ፤ "የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የዘመናት የተቋም ጥያቄያቸው መልስ ማግኘቱንና ኢስላማዊ እሴቶችን ያከበሩ የፋይናንስ ተቋማት መስፋፋታቸውን ምክንያት በማድረግ ታላላቅ እንግዶች በሚገኙበት መርሐ ግብር ለማመሥገን መወሰናቸውን" አስታውቀዋል። በተከታታይ ቀናትም በበርካታ የሀገሪቱ አካባቢዎች ይሄው የምሥጋና ኮንፍረንስ እንደሚካሄድም አረጋግጠዋል።

እንደ ሀገር ከተቆራኙን ብሔራዊ በሽታዎቻችን መካከል በቀዳሚነት የሚጠቀሰው አንዱ ችግራችን ለማመሥገንና ለመመሠጋገን ንፉግ መሆናችን እንደ ባሕል የተጣበቀ ደዌ ሆኖብን ይሆንን ብለን ብንጠይቅ ክፋት የለውም:: በሀገር አቀፍም ይሁን በከተሞች ደረጃ መልካም ስኬቶች ሲመዘገቡ ቀድሞ ለማመሥገን ከመቸኮል ይልቅ አቃቂር ለማውጣት መሽቀዳደም እንደ ወግና ልማድ ተጣብቶን ያለ ክፉ በሽታ ሆኖብንስ እንደሆን?

መልካም ውጤት ያስመዘገበን ሠራተኛ አመስግኖ፣ ሸልሞና አድንቆ ማበረታታት ተዘውትሮ በተግባር ሲተረጎም አይስተዋልም:: እርግጥ ነው በከተሞችና በክልል መስተዳድሮች አማካይነት በአሥራ ሁለተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች የሚሰጠው ምሥጋናና ሽልማት በወደፊቶቹ ሀገር ተረካቢ ወጣቶች ሕይወት ውስጥ በጎ ተፅዕኖ እንደሚያመጣ ፍሬው የሚታየው ውሎ አድሮ ነው። ይህ ማበረታቻ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ፈጻሚዎቹን በማመስገን አደራ ማለቱ አግባብ ይሆናል::

በግል፣ በቡድንም ሆነ እንደ ሀገር በስኬቶቻችንና ውጤታማ በሆንባቸው ጉዳዮቻችን በሙሉ ማመሥገንና መመሠጋገን ባሕላችን ሆኖ ሥር እንዲሰድ ተግተን ልናስተምርና በተግባር ልናሳይ ይገባል:: ባለ ውለታዎቻችንን ማመሥገንና መዘከር፣ ላበረከቱትና ትተውት ላለፉት መልካም ሌጋሲም ከዘመን ዘመን እየተመሠገኑ እንዲኖሩ በየአደባባዮቻችን መታሰቢያ ማቆም ትርፉና ትሩፋቱ ከፍ ያለ ስለሚሆን በአግባቡ ልንመካከርበት ይገባል::

ተቋማትም በአቅማቸው ልክ ውጤታማ ሠራተኞቻቸውንና ኃላፊዎችን በማመሥገን መደናነቅና መከባበር መልሶ ያስከብራል እንጂ ጉዳት የለውም:: ነገሮች እንደተጠበቀው ባይሆኑስ ፈጣሪ በሕይወታችን ውስጥ የተበላሸውን ጅምራችንን ለማቃናት ድርሻ አይኖረውምን? በሚገባ ይኖረዋል እንጂ:: ስለዚህም ስለ ስኬታችንና ስላስመዘገብነው ውጤት ግዙፍነት ብቻ ሳይሆን በጉድለታችንም ቢሆን ፈጣሪን ስለ ብዙ ጉዳዮች ልናመሠግነው ይገባል::

አንድ የሀገራችን ጎምቱ ዘማሪ ባዜመው የመንፈሳዊ መዝሙር ግጥም ውስጥ እንደተቀኘው ነገሮች እንኳን እንደተጠበቀው ባይሳኩ ፈጣሪን ከልብ በማመሥገን ድል ማግኘት ይቻላል:: በምሥጋና የሚናፈቀው ስኬት ሊገኝ ይችላል:: ከላይ የጠቀስናቸው ሀገራት ታሪክ የሚያስታውሰን ይህንን እውነታ ነው::

**«በምሥጋና ሆ! በምሥጋና**
**ድል ይገኛልና::**
**ሸለቆ አሸቆልቁለው ሲያስቅሱ፣**
**ሰዎች ለምሥጋና ቢነሱ፤**
**በኃዘኑ ፈንታ ደስታ፣**
**በልቅሶውም ምትክ ዕልልታ::**
**ሰማያት እንደ ናስ ሲዘጉ፣**
**በምሥጋና ሕይወት ቢጠጉ፣**
**ያንዣበበው ጥላ ሲገፈፍ፣**
**አመስግኖ በአምላክ መደገፍ::**

በዓሉ የሀገራችን ባሕል ባይሆንም በውጭ ሀገራት ለተበተኑት ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሙሉ መልካም የምሥጋና ቀናት (Happy Thanksgiving!) በማለት ምኞታችንን እንገልጻለን::

**ሰላም ለሕዝባችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።**

# ተናጋሪው ዶሴ

## የዘራፊው ቡድን መጨረሻ

**አስመረት ብስራት**



ወንጀል ፈፃሚዎቹ በወጣትነት የእድሜ ክልል ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ አካላዊ ጥንካሬ እና ትኩስነት የሚታይባቸው ሲሆን፤ ወጣትነታቸውን በሥራ እና በትጋት ማሳለፍ የግድ መሆኑን ዘንግተዋል፡፡ ከእነርሱ አልፎ ወጣትነት የማሕበረሰብ ሁለንተናዊ ጌጥ እና ውበት እንዲሁም የዕድገት ሚስጥር መሆኑን አልተረዱም፡፡

የወጣትነት አቅማቸውን በበጎ ሥራ ላይ አውለው መልካም መዓዛ እንዳለው ሽቶ ለሁሉም በአስደሳች መልኩ ከመድረስ ይልቅ፤ የሰው ጥሪት ነጣቂ፣ ማሕበረሰቡን አስለቃሽ እና በሁሉ የተጠሉ መሆኑን ምርጫቸው አድርገዋል። ፊሊሞንና ቸርነት በዚህ ምርጫቸው ደግሞ ምንም አይነት የፀፀት ስሜት ሲሰማቸው አይታዩም።

### ጥምረት ስጥፋት

ወጣቶች ናቸው። ሁለቱም በሀያዎቹ የዕድሜ ክልል የመጀመሪያ ዓመታት ገደማ ላይ ይገኛሉ። ተጣብቀው ሲያወሩ የተመለከታቸው እስከ ሞት የማይለያዩ ምርጥ ጎደኞሞች መሆናቸውን ለመገመት ይገደዳል። በእርግጥም እነርሱም በጭራሽ መለያየት አይፈልጉም፤ መኖሪያቸው የተለያየ ቤት ቢሆንም፤ ለአዳር ሲለያዩ በካባድ ቅሬታ ውስጥ ገብተው ነበር።

በጎደኛ የፍቅር መለኪያነት እስኪጠሩ ድረስ እነ እንቶኔን መሆን ነው አይለያዩም የማይላቸው አልነበረም። በትምህርታቸው ከአስረኛ ክፍል መዝለል ያልቻሉት እነዚህ ወጣቶች፤ የትምህርትን ነገር ተከድኖ ይብሰል በማለት ወደ ሱሱ ዓለም ከገቡ ዓመታትን አስቆጥረዋል። ያገኙትን አብረው አጥፍተው መልሰው ሌላ ለሱሳቸው ማስፈፀሚያ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ተፍ ተፍ ማለትን የእለት ከእለት ተግባራቸው ካደረጉ ሠነባብተዋል።

አሁን ግን ትንንሽ ብሮች እያገኙ ጫት ሲቅሙና ሲያጨሱ መዋል ብሎም ሲጠጡ ማምሸት ሰልችቷቸዋል። የተሻለ ብር የሚያገኙበትን እቅድ ማውጣት ከጀመሩ ሰነባብተዋል። ለእቅዳቸውም መሳካት ምን ምን ያስፈልጋል? እነኚህ አስፈላጊ ነገሮችንስ ለማግኘት ምን መስራት አለብን? የሚሉና ሌሎች ጥያቄዎችን እያነሱ ምላሽ ለመስጠት ማጥናት እና ጥረት ማድረግ ከጀመሩ ሰነባብተዋል።

አሁን ግን እቅዱም መስመር እየያዘ ላሰቡት ስራ መሳካትም የሚያገለግሉ ቁሶችም እየተገኙ መምጣት ጀመሩ። ለማስፈራራት የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች፤ የዘረፉትን የሚጭኑበት መኪና አግኝተው ተዘጋጁ። ዝግጅቱ እንደተጠናቀቀ ለጥፋት የመሰረቱት ጥምረት ሰምሮ ወደ ተግባር የሚቀየርበት ቀን ደረሰ።

### ተደጋጋሚው ጥፋት

ከዚህ ቀደም ለእቅዳቸው መሳካት ኢላማ ውስጥ በገባው አንድ የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ የዝርፊያ ተግባራቸውን የጀመሩት ወጣቶች ማንም ሳይደርስባቸው ሙሉ የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ እቃ ዘርፈው ጭነው ሸጠዋል። በቀደመው የዘረፋው ተግባር የልብ ልብ የተሰማቸው ወጣቶች አንድ ሌላ የኤሌክትሪክ መሸጫ ሱቅ አይናቸው ገብቷል።

የኤሌክትሪክ እቃዎች እጃቸው ቢገባ የተሻለ ገንዘብ ሊያስገኝላቸው እንደሚችሉ አምነዋል። ለእዚህ ስራም ሁለቱ ብቻ በቂ አለመሆናቸውን ተገንዝበው ሌሎች ለዚህ ስራ ብቁ ናቸው የሚሏቸውን ሰዎች አዘጋጅተዋል። አይን የተጣለበትም ከአክሱም ሕንፃ ጎን የሚገኝ ኤቨር ግራንድ ሕንፃ ላይ ያለ ፌሰል ዲኖ የኤሌክትሪክ እቃዎች መሸጫ ሱቅ ነበር፡፡ በቅድሚያ ለመዝረፍ በቂ ጥናት አደረጉ።

ጥናቱም ዝግጅቱም ተጠናቆ በሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት አስር ሰዓት ሲሆን፤ ቂርቆስ ክፈለ ከተማ ወረዳ 01 በሚገኘው ፌሰል ዲኖ የኤሌክትሪክ እቃዎች መሸጫ ሱቅን በር ገንጥለው በመግባት በብዙ ሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ የሚያወጡ የኤሌክትሪክ ሽቦዎችና የኤሌክትሪክ እቃዎች ዝርፊያ ፈፀሙ። ከዝርፊያው በተጨማሪ በጥበቃ ላይ የነበረ ሰራተኛ ላይ አደጋ አድርሰው ተሰወሩ።

### ተጎጂው የጥበቃ ሰራተኛ

አቶ ያዕቆብ ጀልዱ ይባላሉ። የሁለት ልጆች አባት ለፍቶ አዳሪ ጎልማሳ ናቸው። ቀን ቀን ያገኙትን ሥራ እየሠሩ ምሽቱን በጥበቃ ሰራ ላይ ያሳልፋሉ። ልጆቻቸው ቢናፍቋቸው እንኳን ለእነሱ የተሻለ ሕይወት ለመስጠት ሲሉ፤ ሳያገኙዋቸው ባላቸው እውቀት እና አቅም ልክ ሌት ከቀን ይለፉ ነበር። ከልጆቻቸው ጋር የሚገናኙት በሳምንት አንድ ቀን እረፍት ሲሆን ብቻ ነበር። በዛ እለትም እንደተለመደው ከልጆቻቸው አጠገብ ሳይሆኑ እንደውም ሳይገናኙ ቀኑን አሳልፈው ማታ ወደ ጥበቃ ሥራቸው ገቡ።

አቶ ያዕቆብ በማግስቱ ግን የእረፍት ቀናቸው ስለነበር ከልጆቹ ጋር ውለው እንደሚያድሩ እያሰቡ ደስታ ተሰምቷቸው ነበር። በዚህ ስራቸውን በትጋት በሚያከናውኑበት ጊዜ፤ የደሞዝ ጭማሪ ማግኘታቸው ደግሞ ደስታቸውን አጥፍ ድርብ አድርጎላቸው ነበር።

ምሽት ጥበቃ ላይ እያሉ አካባቢው ላይ በንቃት ያለውን እንቅስቃሴ ሲመለከቱ ቆይተው፤ ድካም ስለተሰማቸው ወደ ማረፊያ ገብተው አረፍ ብለው ነበር። ዘራፊዎቹ በክትትላቸው የጥበቃ ሰራተኛው በዛ ሰዓት ለማረፍ እንደሚገቡ ያውቁ ነበር። ጥበቃው ግን እንደተለመደው ገብተው ቢተኙም እንቅልፍ ቶሎ አልወሰዳቸውም ነበር፡፡

የሰው እግር ኮቴ ድምፅ ሲሰሙ ጆሯቸውን ቀስረው ማዳመጥ ጀመሩ፡፡ ከእግር ኮቴው ድምፅ በኋላ የበር መገንጠል ድምፅ ሲሰሙ ተነስተው በመሮጥ ድምፁን ወደሰሙበት አቅጣጫ አመሩ። ሆኖም ሁኔታው ቀላል አልነበረም። ፊሊሞን የተሰኘው ዘራፊ ጥበቃው ሳይሰነዝሩ ቀድሞ በፌሮ ብረት ሁለት ጊዜ ጭንቀላታቸውን መታቸው፡፡

ደም ሲፈሳቸው ራሳቸውን ስተው መሬት ላይ ወደቁ፡፡ ሁለተኛው ዘራፊ ቸርነት በበኩሉ አቶ ያዕቆብ ጀልዱ ሲነቁ፤ በወደቁበት እንዳይንቀሳቀሱ ያለበለዚያ በያዘው ትልቅ ሳንጃ የሞት አደጋ እንደሚያደርስባቸው እየዛተ ነገራቸው፡፡ ጩቤ በማውጣት « እንዳትነቃነቅ ካለበለዛ እገድልሃለሁ፤» በማለት አስፈራራቸው። በእርግጠኝነት የሞት አደጋ እንዳንዣበበባቸው የተረዱት ጥበቃ፤ ዘራፊዎቹ በመሳሪያ በማስፈራራት ሲያንገላቷቸው ምላሻቸው ዝምታ ሆነ፡፡

ዘራፊዎቹ የሰረቁትን ዕቃ በመኪና ጭነው ከአካባቢው ተሠወሩ፡፡ በእለቱ ጥበቃ ላይ የነበሩት፤ አቶ ያዕቆብ ጀልዱም ሲነጋ ሰዎች አግኝተዋቸው፤ በሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም ወደ ካዛንችስ ጤና ጣቢያ መወሰዳቸውን እና ሕክምና እግኝተው ከሞት መትረፋቸውን የወንጀል ምርመራው መዝገብ ያመለክታል፡፡

### የፖሊስ ወንጀል ምርመራ

ቡድን አዋቅሮ ወንጀሉ የተፈፀመው እንዴት እና በማን እንደሆነ ሲያጣራ የነበረው የፖሊስ መርማሪ ቡድን፤ ድርጊቱን የፈፀመው አንደኛ በለሚኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 የቤት ቁጥር አዲስ በሆነ ቤት ውስጥ የሚኖረው ፊሊሞን የተሰኘ የ25 ዓመት ወጣት መሆኑን አረጋገጠ። ወጣት ፊሊሞን ትዳር እንዳልመሠረተ እና ቸርነት ከተሰኘ የ22 ዓመት ወጣት እንዲሁም ከሌሎች ጋር ተባብረው ድርጊቱን መፈፀማቸው የፖሊስ የምርመራ ቡድን አወቀ፡፡

ቦሌ ክፍለ ከተማ ልዩ ስሙ የረር ጎሮ አካባቢ የሚኖረው እስከ 10ኛ ክፍል ተምሮ በኋላም ወደ ሥርቆት የገባው ቸርነትም አድራሻው በፖሊስ የምርመራ ቡድን ደንብ ታወቀ፡፡ ሁለቱ በዝርፊያው ላይ መሳተፋቸው የተደረሰባቸው ፊሊሞን እና ቸርነት ከሌሎቹ ካልተያዙ ግብረ አበሮቻቸው ጋር በመሆን ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለእራሳቸው ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ዘረፉ ማከናወናቸውን ፖሊስ መረጃውን አሰባሰበ።

በሰኔ 29 ቀን 2014 ዓ.ም ከሌሊቱ በግምት 10 ሰዓት ሲሆን፤ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታው አክሱም ሕንፃ ጎን ኤቨር ግራንድ ሕንፃ ላይ የግል ተበዳይ ፌሰል ዲኖ የኤሌክትሪክ እቃዎች መሸጫ ሱቅ በሩን ገንጥለው ወደ ውስጥ በመግባት መስረቃቸው በማስረጃ ተረጋገጠ፡፡

በኤሌክትሪክ እቃ መሸጫ ቤት ውስጥ የነበረ ባለ 2 ነጥብ 5 የኤሌክትሪክ ገመድ ብዛቱ 48 ጥቅል የሆነ የአንዱ ጥቅል ወጋ ብር 4 ሺህ 200 ጠቅላላ ብር 201 ሺህ 600 ብር የሚያወጣ ንብረት መስረቃቸው ታወቀ፡፡ በተጨማሪ ውፍረቱ ባለ 1 ነጥብ 5 ብዛቱ 55 ጥቅል የሆነ የአንዱ ጥቅል ዋጋ 2 ሺህ 460 ብር የሚያወጣ በጠቅላላ ብር 132 ሺህ ብር የሚያወጣ የኤለክትሪክ ገመድ መዝረፋቸውን የምርመራ ቡድኑ አረጋገጠ፡፡

ባለ ስድስት የሚባል 12 ጥቅል የኤሌክትሪክ ገመድ እና ውፍረቱ ባለ 3 የሚባል እንዲሁም ባለ አራት የተሰኘ 3 ጥቅልና ሌሎችም የመሳሰሉትን መዝረፋቸውን ፖሊስ አረጋገጠ።

እነ ፊሊሞን በአጠቃላይ የዋጋ ግምቱ ብር 623 ሺህ 600 ብር የሚገመት ንብረት ለመውሰድ እንዲያመቻቸው ወይም ንብረት በሚወስዱበት ጊዜም ሆነ በአወሳሰዱ ወቅት የገጠማቸውን ተቃውሞ ለማስቆም የጥበቃ ሰራተኛው ላይ ጉዳት ማድረሳቸው በማስረጃ ተደግፎ በምርመራ ቡድኑ ተረጋግጦ በዝርዝር ተቀመጠ።

አንደኛ ተከሳሽ ፊልሞን ጥበቃ ላይ የነበሩትን አቶ ያዕቆብን በፌሮ ብረት ሁለት ጊዜ ጭንቀላታቸውን በመምታት ደም እንዲፈሳቸውና ራሳቸውን ስተው መሬት ላይ እንዲወድቁ ማድረጉ በዝርዝር በምርመራ መዝገቡ ተካተተ፡፡

ሁለተኛ ተከሳሽ ቸርነት ወንዶ ጥበቃው አቶ ያዕቆብ ጀልዱ በወደቁበት ትልቅ ሳንጃ ጩቤ በማውጣት ‹‹እንዳትነቃነቅ ካለበለዛ እገድልሃለሁ፡፡›› ብሎ በማስፈራራት ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎች ንብረቶችን በሰሌዳ ቁጥር ኮድ 3 – 42430 ኦሮ መኪና ጭነው በሁለተኛ ተከሳሽ በቸርነት አሽከርካሪነት የወሰዱ መሆኑን አረጋግጦ ለፌዴራል አቃቤ ሕግ መዝገቡን አስተላለፈ፡፡

የፌደራል አቃቤ ሕግ በበኩሉ ከፖሊስ የመጣለትን ማስረጃ አደራጅቶ ተከሳሾች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዴሪ ወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1) (ሀ) እና 671 (1) (ለ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በፈፀሙት ከባድ የውንቡድና ወንጀል ክስ መሠረተባቸው፡፡

### ውሳኔ

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ ችሎት ግንቦት 18 ቀን 2015 በዋለው ችሎት ክሰና ማስረጃውን ከሕግ ጋር አገናዝቦ ውሳኔ አሳለፈ፡፡ አንደኛ ተከሳሽ ፊልሞን ባንቶ በተከሰሰበት ከባድ የውንብድና ወንጀል 14 ዓመት ፅኑ አስራት ይገባዋል ሲል ውሳኔውን አሳለፈ፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ አቶ ቸርነት ወንዱም በ13 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተወስኖ መዝገቡ ተዘጋ።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ሕዳር እና ፅዳት

ሚዛን

ሕዳር 12 ታሪካዊ ቀን ነው፡፡ በዚህ ቀን ብዙ ኢትዮጵያውያን በፋሺስት ጣልያን መስዋዕትነት የከፈሉበት ቀን ነው፡፡ ከዚያ ባሻገር ግን ቀኑ በመላው ኢትዮጵያ ጽዳት የሚካሄድበት እለት ነው፡፡ በብዙ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ከየቤቱ ቆሻሻ እየወጣ ይቃጠላል፡፡ አሁን እየደበዘዘ መጣ እንጂ በተለይ አዲስ አበባ በጭስ ተሸፍና ንጋት ላይ እስከተወሰነ ሰዓት ድረስ ሰው ከሰውም አይተያይም ነበር፡፡ ይህ ልምድ ታሪካዊም መንፈሳዊም ዳራ አለው፡፡ በታሪካዊ ጎኑ ሲታይ የሕዳር በሽታ ከሚባለው ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ፈረንጆቹ ‹‹ስፓኒሽ ፍሉ›› ይሉታል፡፡ ይህም በፈረንጆቹ 1911 የተከሰተ ወረርሽኝ በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ ከተከሰቱት ወረርሽኞች ሁሉ አስከፊውና ከሃምሳ ሚሊዮኖች በላይ ሰዎችን የጨረሰ ሲሆን እኛም ሀገር ገብቶ ቀላል የማይባል ሕዝብ ፈጅተል፡፡ የታሪክ ምሁሩ ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው ሰሞኑን በሸገር ሬድዮ ከጋዜጠኛ መዓዛ ብሩ ጋር ባደረጉት ሰፊ ቃለምልልስ በሽታው በሕዳር ወር በመከሰቱ የሕዳር በሽታ ከመባሉ ባለፈ የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር መንገድ ስራ በጀመረበት ወቅት በሽታው በመነሳቱ ምክንያት ባቡሩ ያመጣው በሽታ ነው በማለት "የባቡር በሽታ" ይባል እንደነበር ይናገራሉ።

በወረርሽኙ ምክንያት በአዲስ አበባ ብቻ በሕዳር ወር 1911 ዓ.ም ከ6 ሺ ሰው በላይ መግደሉን ተከትሎ መንግስት በጀርመን ሀኪሞች ምክር 'የበሽታው መንስዔ ቆሻሻ እንደሆነ በመታመኑ' ሕዝቡ ቆሻሻን ከቤቱ አውጥቶ እንዲያቃጥል፣ አካባቢውን እንዲያፀዳና በተጨማሪ በሽታው በአየር ይተላለፋል ተብሎ ስለታመነ 'አየሩን በማጠን' በሽታውም በወቅቱ ስለጠፋ ከጊዜ በኋላም 'አየሩ ስለታጠነ ነው በሽታው የጠፋው።' ተብሎ በየዓመቱ ቆሻሻን ማቃጠል ልማድ ሆኖ እስካሁንም ቆይቷል፡፡

ዘንድሮም እንደወትሮው ባይሆንም ሰው ማለዳ ተነስቶ ቆሻሻ ሲያቃጥል አስተውለናል፡፡ መቼም በየሰፈሩ ሕዳር ሲታጠን ከየቤቱ ሊቃጠል የሚወጣው የቆሻሻ አይነት በጣም አስቂኝ ነው። ከዛፍ ርጋፊ አንስቶ ጭራሽ እሳት ውስጥ ሊገባ የማይችል ነገር ሁሉ ከያለበት ይወጣል። አንዳንዱማ የሚያቃጥለውን ነገር ብዛት እና የሚፈጥረውን የጭስ መጠን ሲታይ ጭራሽ ቆሻሻን አቃጥላለሁ በሚል ሰበብ የአዞን መሸንቆርን ለማስከተል ታጥቆ የተነሳ ነው የሚመስለው። እንደውም አንዳንዱ በአካባቢ በቅርቡ እየታየ ላለው ሙቀት ምክንያቱ ‹‹አምና ሕዳር ሲታጠን ያቃጠልነው ቆሻሻ ጭስ አዞንን በመቅደዱ ነው›› እያለ ይሳለቃል፡፡

የሆነ ሆኖ ቆሻሻን የማስወገድ ስራው በአግባቡ እየተካሄደ ባለበት ወቅት አንድ ጎረቤታችን ያለቀ ነው ያሉት የሽቶ ጠርሙስ እሳቱ ውስጥ ጨምረው የሽቶ እቃው በመፈንዳቱ ቀላል የማይባል ትርምስ ተፈጥሮ ነበር፡፡ እውነቱን ለመናገር አውጥቶ ማቃጠል ቢቻል ማቃጠል መጥፎና የደከመ አስተሳሰብን ነበር፡፡

እኛ ቤት ብዙ የሚቃጠል ነገር ባለመኖሩ እናቴ ለቃጠሎ ያወጣችው ጥርሱ ያለቀውን መጥረጊያ ነበር፡፡ እሱንም ቢሆን እየከፋት ነበር ያቃጠለችው፡፡ ሌላ መጥረጊያ እንደሚገዛላት አሳምነናት እና ይሄኛው ዘመኑ እንዳለፈበት ብዙ ሰብከናት ነው እሺ ያለችው፡፡ እንደ እናቴ እምነት ከቤት ውስጥ ቆሻሻ ተብሎ ሊቃጠል የሚገባው ምንም አይነት እቃ የለንም፡፡ እንኳን እሳት ውስጥ ሊገባ ከእጃችን እንኳ ሲወድቅ የምትናደደው ንዴት በዚህ ዘመን አንድ ሰው ፕሮማክስ ስልኩ ሲጠፋበት ከሚናደደው ንዴት ያልተናነሰ ነው፡፡ በእናቴና በጊቢያችን ውስጥ ባለ ማንኛውም እቃ መሀከል ያለ ግንኙነት ጥብቅ ነው፡፡ ስለዚህ እንዲህ በቀላሉ መልቀቅ አትፈልግም፡፡ መጥረጊያው ራሱ ወደ እሳት ሲገባ እንዲሁ በከንቱ አልነበረም፡፡ አብረውት የተቃጠሉ የግቢውን ሌሎች ቆሻሾችን ጠርጎ ሲጨርስ ምን ያህል ጥሩ መጥረጊያ እንደነበር እና ሲገዛ ዋጋው ምን ያህል እንደነበር እንዲሁም ሲያጸዳ ምን ያህል ጥሩ እንደሆነ አጭር የስንብት ንግግር አድርጋ ነው ወደ እሳቱ እንዲሰናበት የተደረገው፡፡

የእኛ ሰፈር የቆሻሻ ማቃጠል ስርዓት አስቂኝ ክፍል አለው፡፡ ሁሉም ሰው ቆሻሻውን ሊያቃጥል በጠዋት ተነስቶ ሲጠራርግ እስከ ዛሬ ያልተነኩ ቆሻሻዎችን ሁሉ መዝዞ ያወጣል፡፡ ይህን ያህል እምቅ ቆሻሻ በሰፈራችን እንዳለ የምናውቀው ራሱ የዚያን ቀን ነው፡፡ ከዚያ ይህ ቆሻሻ ሰብሰብ ይልና ለቃጠሎ ሲዘጋጅ እድሉ ከሚያልፍ ተብሎ ሌሎች እስካሁን ቆሻሻ ናቸው ተብለው በይፋ ስያሜ ያልተሰጣቸው እንደ የእኛ ቤት መጥረጊያ ያሉትም ይጨመራሉ፡፡ ቆሻሻው ይከመራል፡፡ በሽታውን ሁሉ ውሰድልን፤ ጤና ስጠን፤ ሀገራችንን ሰላም አድርግልን ተብሎ ይለኮሳል፡፡ ከዚያ ቆሻሻው ተቃጥሎ እስከሚያልቅ ጊዜ ስለሚፈጅ ሁሉም ወደየጉዳዩ ይሄዳል፡፡ ከዚያ ያለ የተቃጠለ ቆሻሻ አመድ እዚያው ንፋስ ሲያበነው እና እግረኛ ሲያምሰው ውሎ ሌላ አዲስ ቆሻሻ ሆኖ ይከሰታል፡፡

ስናጠቃልለው ሕዳር ሲታጠን ጥሩ ባሕል ነው፡፡ ቆሻሻን ማስወገድ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን ቆሻሻ ሲወገድ ሂደት አለው፡፡ የመጀመሪያው ሂደት ቆሻሻ የሆነውን እና ያልሆነውን መለየት ነው፡፡ ብዙዎቻችን የያዝነውን ቆሻሻ፤ ቆሻሻ መሆኑን እንኳ አንረዳውም፡፡ ቆሻሻ ባይሆን እንኳ አንደማያስፈልገን እና ቦታ እየያዘብን እንደሆነ አናምንም፡፡ አብሮን ብዙ ስለኖረ ከማይጠቅመን ነገር ጋር ፍቅር ይዞናል፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ ቆሻሻ እና አላስፈላጊ የሆነውን ነገር መለየት ያስፈልገናል። ከዚያም የትኛው ቆሻሻ እንዴት ይወገዳል የሚለውን መገንዘብ አለብን። አንዳንድ ቆሻሾች ይቃጠላሉ፡፡ ሌሎች በሌላ መንገድ ይወገዳሉ። ሁሉንም ላቃጥል ማለት ሌላ ችግር ይወልዳል፡፡ አንዳንድ ቆሻሾች የሚቃጠሉ ቢሆን እንኳ የሚቃጠሉት ራቅ ባለ ቦታ እንጂ ግቢ ውስጥ አይደለም፡፡ በሕይወታችንም ውስጥ ሁሉን ችግር በአንድ መንገድ ለመፍታት መሞከር ነው ችግር ውስጥ የሚከተንና ችግራችንን እንዴት እንደምናስወግድ መለየት አለብን፡፡ በመጨረሻም አይጠቅመንም ያልነውን ነገር ስናስወግድ በቅጡ እንዳይመለስ አድርገን ነው መሆን ያለበት፡፡ አልያም በእጃችን ያወጣነውን ቆሻሻ በእግራችን ይዘነው እንመለሳለን፡፡ በሕይወታችንም ላይ በተመሳሳይ የምንነካካቸው ነገር ግን በቅጡ የማናስወግዳቸው ችግሮቻችን ለጊዜው ከፊታችን ዘወር ቢሉም ኋላ ላይ ግን ዞረው ወደ ሕይወታችን መመለሳቸው አይቀርምና ስናስወግድ በአግባቡ መሆን አለበት፡፡

**ቸር እንሰንብት !**


# ዓለም አቀፍ

## በኢራቅ እና በሶሪያ ያለው የአሜሪካ ጦር አራት ጊዜ ጥቃት ደረሰበት

በኢራቅ እና በሶሪያ ያለው የአሜሪካ ጦር አራት ጊዜ ጥቃት ደረሰበት፡፡ በኢራቅ እና በሶሪያ የሚገኘው የአሜሪካ ጦር በድሮን እና በሮኬት አራት ጊዜ ጥቃት እንደደረሰበት የአሜሪካ ባለስልጣናት ተናግረዋል። በጥቃቱ በሰውም ይሁን በመሰረተ ልማት ላይ ጉዳት አለመድረሱን ሮይተርስ ዘግቧል።

ባለስልጣናቱ እንደገለጹት፤ በሰሜን ምስራቅ ሶሪያ የሚገኘው የአሜሪካ ጦር በበርካታ ሮኬቶች እና በድሮን ጥቃት ደርሶበታል። በኢራቅ አይን አል አል አሳድ በሚገኘው የአሜሪካ ጦር ሰፈር ላይ በአንድ ጊዜ በበርካታ ድሮኖች ጥቃት ተፈጽሞበታል ተብሏል። ራሱን የእስላሚክ ሪዚስታንስ ብሎ የሚጠራው ቡድን በእነዚህ ቦታዎች ለደረሰው ጥቃት ኃላፊነቱን ወስዷል።

በአሜሪካ የጦር ሰፈሮች ላይ ጥቃት የተሰነዘረው



**የአሜሪካን ጦር ሰፈር፤**

አሜሪካ በኢራን በሚደገፈው ካታይብ ሄዝቦላ ላይ ጥቃት ካደረሰች ከአንድ ቀን በኋላ ነው። ይህን ጥቃት የኢራቅ መንግስት ሉአላዊነትን የሚጥስ ነው በሚል አውግዞታል። የአሜሪካ ባለስልጣናት የእስራኤል እና ሀማስ ጦርነት ከተጀመረ ከ10 ቀናት በኋላ በአሜሪካ እና ሌሎች ዓለምአቀፍ ኃይሎች ላይ ትንኮሳዎች በመፈጸማቸው ምክንያት ጥቃት ማድረሷን ተናግረዋል።

ባለስልጣናቱ እንደገለጹት ከባለፈው ሀሙስ ጀምሮ በኢራቅ 36፣ በሶሪያ ደግሞ 37 ጥቃቶች ተፈጽመዋል።

በሶሪያ ከ12 ዓመት በፊት የተቀሰቀሰው የተቃውሞ ሠልፍ ወደ እርስ በርስ ጦርነት አምርቶ በሺዎች የሚቆጠሩትን ቀጥፏል፡፡ ጦርነቱን ተከትሎ ‹‹የመካከለኛው ምሥራቅ ገነት›› የምትባለው ሶሪያ ወደ ሲኦልነት ተቀይራለች። ከአሥራ ሦስት ሚሊዮን የሚበልጡ ዜጎቿ ተፈናቅለዋል፤ ከአምስት ሚሊዮን በላይ ተሰደዋል። ይህን ተከትሎም የአሜሪካ ጦር ወደ ስፍራው ማቅናቱ ይታወሳል፡፡

## ጃፓን በ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ለወሲብ ባርነት ለዳረገቻቸው ሴቶች ካሳ እንድትከፍል ተወሰነ

ጃፓን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በወታደራዊ የወሲብ ንግድ ቤቶች ውስጥ እንዲሰሩ አስገድዳቸዋለች ለተባሉ ሴቶች ካሳ እንድትከፍል ተወሰነባት። ይህንን ውሳኔ ያሳለፈው የደቡብ ኮሪያው ፍርድ ቤት ነው።

ለጃፓን ወታደሮች ሲባል ለወሲብ ባርነት ተዳርገዋል የተባሉ 16 ሴቶች ቀደም ሲል ጉዳያቸው ውድቅ ተደርጎ ነበር። በደቡብ ኮሪያዋ መዲና ሴኡል በሚገኝ የአውራጃ ፍርድ ቤትም በአውሮፓውያኑ 2016 ክሳቸውን ማቅረባቸው ይታወሳል። ፍርድ ቤቱም ከአምስት ዓመታት በኋላ ሉዓላዊ ያለመከሰስ መብትን በመጥቀስም ነበር ውድቅ ያደረገው። የሴኡል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ውሳኔ በመሻርም ብያኔውን አስተላልፏል።

ደቡብ ኮሪያ በጃፓን መንግሥት ላይ ስልጣን አላት ያለው ፍርድ ቤቱ ለዚህም ሴቶቹ በጃፓን ውስጥ ይኖሩ ስለነበር እና ሕጋዊ ያልሆነ ተግባርም ስለተፈጸመባቸው እንደሆነም ጠቅሷል። “ሉዓላዊም ይሁን ምን ሕገወጥ ድርጊቶች ሲፈጸመው የትኛውንም የመንግሥትን ያለመከሰስ መብት የማይቀበል የጋራ ዓለም አቀፍ እንዳለ ማሰብ ያስፈልጋል” ብሏል።

ሊ ዮንግ ሱ የተባሉ የ95 ዓመት ተሟጋች እና ሰለባ ፍርድ ቤቱ ላስተላለፈው ብይን በሚያመሰግኑበት ወቅት በስሜት ተሞልተው ነው። ከፍርድ ቤት ሲወጡም “አመሰግናለሁ፣ በጣም አመሰግናለሁ” ሲሉም ለጋዜጠኞች ተናግረዋል። ብያኔውን ሳያዩ በሞት ለተለዩት ተጎጂዎችም ውሳኔውን መንገር ቢችሉም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ለጃፓን ወታደሮች ሲባል ከ200 ሺህ በላይ ሴቶች እና ታዳጊዎች ለአስገዳጅ ወሲባዊ ንግድ ተዳርገዋል ተብሎ ይገመታል። በእነዚህ የወታደራዊ የወሲብ ንግድ ቤቶች ውስጥ ከነበሩት መካከል አብዛኞዎቹ ኮሪያውያን ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከቻይና፣ ፊሊፒንስ፥ ኢንዶኒዥያ እና ታይዋን የመጡ ነበሩ።

የጃፓኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዮኮ ካሚካዋ ውሳኔውን “የሚያሳዝን እና ፍጹም ተቀባይነት የሌለው” እንደሆነ ተናግረዋል።“ የኮሪያ ሪፐብሊክ የተጣሰውን የዓለም




አቀፍ ሕግ እንዲያስተካክል ተገቢውን እርምጃ በአስቸኳይ እንዲወስድ ጃፓን በድጋሚ አጥብቃ ትጠይቃለች” ሲሉም መናገራቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# መጋቢ አዕምሮ

# ጎበዝ ተማሪ የመሆን ሚስጥር



**አስናቀ ፀጋዬ**

የዘንድሮ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ሆይ! መቼም በ2015 ዓ.ም የመልቀቂያ ፈተና የወሰዱ ተማሪዎችን ውጤት ሰምታችኋል፡፡ እጅግ አስደንጋጭ ነበር፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ 3 ነጥብ 2 ከመቶ ያህሉ ብቻ ተማሪዎች ነበሩ ፈተናውን ማለፍ የቻሉት፡፡ ይህ የሆነው ታዲያ አንድም የፈተና ቁጥጥሩ ከዚህ ቀደም ከነበረው ጠንካራ በመሆኑና በተማሪዎች በኩል ለፈተናው የተደረገው ዝግጅት በቂ ባለመሆኑ ነው፡፡ እናም ዘንድሮ ደግሞ እናንተ ይህንን የመልቀቂያ ፈተና ለመውሰድ ተረኞች ናችሁ።

ምንም እንኳን በ2015 ዓ.ም የተመዘገበው ውጤት አስደንጋጭ ቢሆንም እናንተ በዚህ ውጤት መደንገጥ የለባችሁም፡፡ ይህን ውጤት እንደመማሪያ እንጂ ተስፋ መቁረጫ አድርጋችሁ መውሰድ አይጠበቅባችሁም፡፡ ብልህ ተማሪ ከሌሎች ውድቀት ነው የሚማረው፡፡ ጎበዝ ተማሪ ራሱን የሚያዘጋጀው ገና ከአሁኑ ነው፡፡ ጎበዝ ገበሬ ቀደም ብሎ ማሳውን በሚገባ ስለሚያዘጋጅና ወቅቱን ጠብቆ ስለሚዘራ ነው መልካም አዝመራን የሚያጭደው፡፡ ጎበዝ ተማሪም ጥሩ ውጤት ማምጣት ከፈለገ ገና ከአሁኑ ነው ራሱን ማዘጋጀት የሚጠበቅበት፡፡

እናም ተማሪዎች ዓላማችሁን ስታውቁት ከእናንተ በላይ ጎበዝ የሚሆን፤ የሚፈልገውን የሚያሳካ የለም፡፡ አይደለም ለራሳችሁ ለማንም ትተርፋላችሁ፡፡ ለቤተሰቦቻችሁ ኩራት መሆን ትችላላችሁ፡፡ ሕልማችሁን መኖር ትችላላችሁ፡፡ ማንም ከእናንተ ብዙ ነገር ቢጠብቅ አትፍረዱበት። ጎበዝም ብትሆኑ፤ ዩኒቨርሲቲ እንድትገቡ ቢጠብቅ እናንተ አትፍረዱበት፡፡ ስለሚገባችሁ ነው፡፡ በቃ ትልቁ ቦታ ይገባችኋል፡፡ ለዛ ነው ሕይወታችሁን መቀየር ያለባችሁ፡፡

አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ! ሁለት ወንድማማቾች ናቸው፡፡ የአንድ እናትና የአንድ አባት ልጆች። አንደኛው ሰካራም፣ ተደባዳቢ፣ ሌባ፣ ቀማኛና ወንበዴ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ጠበቃ ነው፡፡ የሕግ ሰው፣ የተከበረ፣ ሰዎች የሚወዱት ትልቅ ተከፋይ ጠበቃ ነው፡፡ እርሱን ጥብቅና ያቆመ ድርጅትና ግለሰብ የማይረታው ጉዳይ የለም፡፡ በጣም ስኬታማ ጠበቃ ነው፡፡ ሁለቱ ወንድማማቾች ተጠየቁ። እንዴ! አንድ ቤት ነው ያደጋችሁት፡፡ ወንድምህ ነው፣ ያውም የሥጋ፡፡ አንተ እንዴት ጠበቃ ልትሆን ቻልክ? አንተኛውስ እንዴት ዱርዬና ሰካራም ልትሆን ቻልክ? ተባለ፡፡

ሰካራሙ ‹‹አባቴ ነዋ! አባቴ እኮ ሰካራም ነው። ማታ ጠጥቶ እየመጣ እናቴን ይደበድባታል። ታዲያ እሱን እያየሁ አድጌ እንዴት ነው ሰካራም የማልሆነው›› ሲል መለሰ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ አንተስ ምን ብታደርግ ነው ጥሩ ጠበቃ ልትሆን የቻልከው? ከአንድ ቤት ወጥተህ ያውም ወንድምህ ሰካራምና ሌባ ሆኖ ተብሎ ሲጠየቅ ‹‹አባቴ ነዋ!›› አለ፡፡ እንዴት? ሲባል ‹‹አባቴ እናቴን ማታ ጠጥቶ ገብቶ ሲደበድባት እያየሁ እንደእሱ አይነት ሰው አልሆንም ብዬ ለራሴ ቃል ገባሁ፡፡ በፍፁም እንደሱ አልሆንም ብዬ ቃል ገባሁ፡፡ ራሴን ለውጥኩኝ›› አለ፡፡

ሁለቱም ልጆች የገጠማቸው ችግር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሁለቱም በከባድ ሁኔታ ውስጥ ሆነው በአንድ ቤት ውስጥ ነው ያደጉት፡፡ አንደኛው ጠበቃ ሆነ፡፡ ሌላኛው ደግሞ ሌባ፡፡ ስለዚህ ሕይወትን የሚቀይረው ምርጫ ነው፡፡ ሕይወትን የሚቀይሩት ሁኔታዎች አልያም ደግሞ ሰዎች አይደሉም የሚቀይሩት፡፡ ተማሪዎች ቁርጣችሁን እወቁ! አስማሪዎቻችሁን ጎበዝ ማድረግ አትችሉም፡፡ የአስራ አንደኛና አስራ ሁለተኛ ክፍልን ብቻ ነው የምፈተነው ማለት አትችሉም፡፡ ከዘጠነኛ እስከ አስራ ሁለተኛ የክፍል ደረጃ ያለውን ነው የምትፈተኑት፡፡

ስለዚህ መቀየር የማትችሉትን ነገር መቀበል ነው ያለባችሁ፡፡ ዝናቡን ልታቆሙት አትችሉም። ዣንጥላ ግን ትዘረጋላችሁ፡፡ ቢደበድባችሁ ተጠያቂው እናንተ ናችሁ፡፡ ለምን ዝናብ ዘነበ ማለት አትችሉም፡፡ ለምን አልተጠለልንም ነው መልሱ።አያችሁ! አሁን በዚህ ሰዓት ከባድ ሁኔታ ውስጥ እንዳላችሁ ሁሉም ይረዳችኋል፡፡ ጥሩ አድርጋችሁ አልተማራችሁም። አንዳንዴ መሸፈን የሚገባችሁን ያህል ምዕራፍ ጨርሳችሁ ላይሆን ይችላል፡፡ ከዛም ወደ ፈተና ትገባላችሁ፡፡ ከባድ ነው፡፡ ከዛ ደግሞ ዩኒቨርስቲ እንድትገቡ ትጠበቃላችሁ፡፡ ለጥቆ ደግሞ የሆነ ቦታ እንድትደርሱ ትፈለጋላችሁ፡፡ ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ውስጥ መቀየር የማትችሉትን መቀበል አለባችሁ። ‹‹በቃ! አዎ እውነት ነው፡፡ እኔ የቤተሰቦቼን አስተሳሰብ መቀየር አልችልም። አስተማሪዬን መቀየር አልችልም፡፡ ሁኔታዎችን መቀየር አልችልም፤ መቀየር የምችለው አንድ ነገር ነው እርሱም ራሴን ነው›› ማለት አለባችሁ፡፡

ራሳችሁን ለመቀየር መነሳት አለባችሁ፡፡ ለምን መሰላችሁ መቀየር የምትችሉት ራሳችሁን ነዋ! ያላችሁ እድል እሱ ነው፡፡ እጃችሁ ላይ ላለው መታመን ያለባችሁ ራሳችሁ ናችሁ፡፡ ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ ታዲያ ጎበዝና ውጤታማ እንድሆን?፣ ቤተሰቦቼን እንዳስደስት ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ? ከኔ ምን ይጠበቃል? ካላችሁ....

አሁን በዚህ ሰዓት እጃችሁ ላይ ያለው ነገር ትምህርታችሁ ነው፡፡ ሌላ እጃችሁ ላይ ምንም ነገር የለም፡፡ ትምህርታችሁ ላይ ጎበዝ ከሆናችሁ ነገ በምትፈልጉት ጉዳይ ስኬታማ ትሆናላችሁ። ትንሹ ላይ ስትታመኑ ትልቁ ላይ ትሾማላችሁ፡፡ ለምሳሌ ትምህርት አልወድም ልትሉ ትችላላችሁ። ማን ይወዳል? ማንም እኮ አይወድም፡፡ ግን ምን ታደርጉታላችሁ የግድ መማር አለባችሁ፡፡ እንቁራሪት መብላት ግዴታችሁ ቢሆን ምን ታደርጋላችሁ? የምትወዷቸውን ሰዎች አጠገባችሁ አስቀምጠው ይህን እንቁራሪት ካልበላችሁ እጨረሳችኋለሁ ብትባሉ ምንድን ነው የምታደርጉት? ምርጫ የላችሁም ትበሉታላችሁ፡፡

እንደውም ብራያት ሬሲ የተሰኘ አንድ ታላቅ ደራሲ ‹‹Eat That Frog›› የሚለው መጽሐፉ እንቁራሪት መብላት ግዴታችሁ ከሆነ ሁለት ነገር ከሆነ ሁለት ነገር እመክራችኋለሁ ይላል፡፡ የመጀመሪያው መጨፈን ነው፡፡ ከዚያም ትልቁን አስቀድማችሁ ብሉት፡፡ ይህ ማለት አንዳንድ ግዜ መብላት ያላባችሁ ግዴታ የሆነ እንቁራሪት በሕይወታችሁ አለ፡፡ ከዚህ ውስጥ አንዱ ትምህርት ነው፡፡ ትምህርት ስትማሩ ደስ ላይል ይችላል፡፡ ግን ደግሞ መማር ግዴታ ነው፡፡ አሁን ከተወጣችሁት ግን ነገ የምትስቁት እናንተ ናችሁ፡፡

ለማንኛውም አሁን በዚህ ሰዓት እናንተ በትምህርታችሁ ደስተኛ ላትሆኑ ትችላላችሁ። ‹‹እዚህ ትምህርት ቤት የምመጣው እኮ ለእናቴና ለአባቴ ብዬ ነው፤ ለማን ብዬ ነው›› እያላችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ችግር የለውም ወደ ትምህርት ቤት ኑ፡፡ ምንም ችግር የለውም ተማሩ፡፡ እጃችሁ ላይ ላለው ለትምህርታችሁ ታመኑ፡፡ አሁን በዚህ ሰዓት ፊዚክስ ከብዶህ ሊሆን ይችላል፡፡ ከገባውና ከጎንህ ካለው

**«ብልህ ተማሪ ከሌሎች ውድቀት ነው የሚማረው፡፡ ጎበዝ ተማሪ ራሱን የሚያዘጋጀው ገና ከአሁኑ ነው፡፡ ጎበዝ ገበሬ ቀደም ብሎ ማሳውን በሚገባ ስለሚያዘጋጅና ወቅቱን ጠብቆ ስለሚዘራ ነው መልካም አዝመራን የሚያጭደው። ጎበዝ ተማሪም ጥሩ ውጤት ማምጣት ከፈለገ ገና ከአሁኑ ነው ራሱን ማዘጋጀት የሚጠበቅበት»**

ጎበዝ ተማሪ ተረዳ፡፡ ሂሳብ ከብዶሽ ሊሆን ይችላል። ቆንጆ አድርጎ የሚያስረዳ መምህር ካለ እርሱን ተከታተይ፡፡ ዛሬን ታመኑ፡፡ መማር ምን ይጠቅማል መሰላችሁ? አሁን ተምራችሁ የት ልትደርሱ ነው የሚሉትን ተዋቸውና የምትወዱትን የምትማሩ ከሆነ ማንም አይደርስባችሁም፡፡

አንድ ምሳሌ እንካችሁ፡- አስር ሰዎች ናቸው፡፡ አንድ ቤት ውስጥ ለጥ ያለ እንቅልፍ ወስዷቸዋል። እዛ ቤት ውስጥ ለአንድ ሰው ብቻ የሚበቃ ምግብ አለ፡፡ ዝም ብላችሁ አስቡት፡፡ ማን የሚበላ ይመስላችኋል? ቀድሞ የተነሳው ነው ምግቡን ሊበላ የሚችለው፡፡ እንግዲህ መማር ማለት በተኙት መካከል መንቃት ነው፡፡ ስለችግሩ አብዝቶ ማውራት መፍትሔ አያመጣም፡፡ ‹‹አስተማሪው እንዲህ አድርጎኝ፣ ከባድ ነው ትምህርቱ›› ብትሉ ማንም አይሰማችሁም፡፡ ችግሩን አትፈቱትም፡፡ ጨለማን እየተራገማችሁ ብርሃን አታመጡም፡፡ ስለብርሃን ማሰብና ወደተግባር መግባት ነው የሚያስፈልገው፡፡

‹‹ራሴን የምቀይረው እኔው ነኝ ማንም አይደለም የኔን ሕይወት ሊቀይር የሚችለው›› ማለት አለባችሁ፡፡ ደሞም ፈጣሪ በሁላችሁም ውስጥ አንድ ትልቅ ኃይል አስቀምጧል፡፡ ቆፍራችሁ እስኪታወጡት ድረስ ነው፡፡ ትንሽ ሰነፍ እንደሆንን የምናስበው አንዳንዴ ‹‹እኔ እኮ እጥራለሁ፤ አነባለሁ ግን ጥሩ ውጤት አላመጣም፣ ቤተሰቦቼ አይረዱኝም አስተማሪዎቼ አይረዱኝም ምን ላድርግ፤ መለወጥ እኮ እፈልጋለሁ›› ትሉ ይሆናል፡፡ እናንተ ውስጣችሁ ያለውን ነገር አልገባችሁም፡፡ ከቻላችሁ ‹‹ምንድነው የምፈልገው?›› ብላችሁ ማሰብ ጀምሩ፡፡ ምንድን ነው የምትፈልጉት? ዓላማችሁን ለማወቅ ሞክሩ፡፡ ዓላማን ማወቅ ጎበዝ መሆንን አይጠይቅም፡፡ ከእናንተ የሚጠበቀው ዓላማችሁን ለማወቅ ፍቃደኛ መሆን ነው፡፡

‹‹የዛሬ አስር ዓመት ከእንቅልፌ ስነቃ ምን አይነት ቦታ ላይ ነው ራሴን የማገኘው?›› ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቁ፡፡ የዛሬ ዓመት፣ አምስትና አስር ዓመት የት ነው የምደርሰው? ምን አይነት ቦታ ላይ ራሴን ባገኝ ነው ደስ የሚለኝ?›› በሉ፡፡ ዝም ብላችሁ አስቡት፡፡ ‹‹ቤተሰቦቼን ማስደሰት የምችለው ምን አይነት ቦታ ላይ ስደርስ ነው? ከአስር ዓመት በኋላ ምን አይነት ሁኔታ ላይ ብሆን ነው እኔስ ደስተኛ የምሆነው?›› ብላችሁ አስቡ፡፡ ዓላማን ማወቅ ጉብዝና፣ ጥበብ፣ ችሎታና ክሂል አይጠይቅም፡፡ ቁጭ ብሎ ራስን መጠየቅ ነው፡፡

አንድ ታሪክ እንካችሁ፡- የአስራ ሦስት ዓመት ታዳጊ ነው፡፡ እግር ኳስ ለመጫወት ሁሌም ወደ ሜዳ ይሄዳል፡፡ ሁሌም ቢሆን ልምምድ ቦታ አይቀርም፡፡ ግን ኳስ አይችልም፡፡ እንዲሰለፍም አይፈቀድለትም። ሁሌ ወደ ሜዳ መጥቶ ይለማመዳል፡፡ ጥግ ላይ ሆኖ አባቱ ያየዋል፡፡ የሆነ ግዜ ግን ልጁ ጠፋ፡፡ ለአራት ቀን ወደ ሜዳ አልመጣም፡፡ በአምስተኛው ቀን ልጁ እዛ ሜዳ ተከሰተ፡፡ ልክ ሲመጣ የእርሱ ቡድን ግጥሚያ ነበረው፡፡ ከዛም ወደ አሠልጣኙ ጠጋ ብሎ አሰልፈኝ አለው፡፡ አሠልጣኙም እየሳቀ ‹‹አንተ ትቀልዳለህ እንዴ የት ኳስ የምትችለውን ነው የማሰልፍህ፤ ደሞም የት ጠፍተህ ነው የመጣኸው በል ዞር በል አለው፡፡ ልጁ ግን ካላስገባኸኝ ብሎ ድርቅ አለ። ከዛም አሠልጣኙ ‹‹ይሄ ልጅ ምን ታይቶት ነው እንደው አስገብቼ ልሞክረው እንዴ›› ብሎ አሰለፈው። ያ የማይችለው ልጅ ወደ ሜዳ ገብቶ ተጫወተ። በእርሱ ምክንያት ቡድኑ አሸነፈ፡፡ ብዙ ጎሎች አገባ። አሠልጣኙም ደነገጠ፡፡ ጨዋታው ሲያልቅ ልጁን ጠርቶት ‹‹አንተ እስከዛሬ ድረስ ለምንድን ነው ያልተጫወትከው፤ ዛሬ ምን አግኝተህ ነው?›› ብሎ ጠየቀው፡፡ ልጁ መለሰ ... አባቴ ስለሚያየኝ ነው አለ። አሠልጣኙ ገርሞት ዞር ዞር ብሎ ሲያይ ማንም የለም። ‹‹ምንድን ነው የምትዋሸው ማንም የለም እኮ›› አለው፡፡ ልጁም ቀጠለና ሁልጊዜ ለልምምድ አንተ ጋር ስመጣ አባቴ እዛ ጋር ቁጭ ብሎ ያየኛል፡፡ ግን ዓይነ ስውር ነበር፡፡ ከአራት ቀን በፊት ግን ሞተ፡፡ ዛሬ ከላይ ሆኖ እንደሚያየኝ እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው እንደዚህ የተጫወትኩት›› አለው፡፡

አስባችሁታል ይህ ልጅ ሰነፍ ስለሆነ አይደለም። ግን አባቴ ካላየኝ ለምን እጫወታለሁ ብሎ ስለሚያስብ ነው በደምብ ያልተጫወተው፡፡ ዛሬ ግን ሲሞት ከላይ ሆኖ ያየኛል ብሎ እርግጠኛ ሆኖ ከልቡ ተጫወተ። እናንተም ተማሪዎች ሁላችሁም የሚገርም አቅም አላችሁ፡፡ አይደለም ለራሳችሁ ለማንም ትተርፋላችሁ፡፡ ለቤተሰቦቻችሁ ኩራት መሆን ትችላላችሁ፡፡ ሕልማችሁን መኖር ትችላላችሁ፡፡ ማንም ከእናንተ ብዙ ነገር ቢጠብቅ አትፍረዱበት። ጎበዝ እንድትሆኑና ዩኒቨርስቲ እንድትገቡ ቢጠብቅ አይግረማችሁ፡፡ ትልቁ ቦታ ስለሚገባችሁ ነው፡፡ ለዛ ነው ሕይወታችሁን መቀየር ያለባችሁ፡፡ ለዛ ነው ሰበብ መደርደሩን ማቆም ያለባችሁ፡፡

ከዚህ በኋላ ሰበብ አልደረድርም ማለት አለባችሁ። ከዛሬ ጀምሮ በትንሹ ለራሳችሁ ትታመናላችሁ፡፡ በየቀኑ በትንሹ ታጠናላችሁ። ተራራ የሚወጣ ሰው ቢያንስ አንድ እርምጃ እየተራመደ ነው፡፡ ተራራውን ሳይወጣ እንዲሁ ሽቅብ እያየ ይህን ተራራ እንዴት ልወጣ ነው በዛ ላይ ፀሐዩ እያለ ሰበብ ከደረደረ ተራራውን አይወጣውም፡፡ የሚያመነታ ሰው ከመንገድ ይቀራል። እንዲያ ከሆነ ደግሞ እንዲህ አይነት ሰው ለማንም አይሆንም፤ እናንተም እንደዛው፡፡ ምክንያት ስታበዙ ከመንገድ ትቀራላችሁ፡፡ ያኔ ማንም በእናንተ ደስተኛ አይሆንም፡፡ በራሳችሁ ታዝናላችሁ፡፡ ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ራሳችሁን ቀይሩ፣ በትንሹ ለራሳችሁ ታመኑ፣ ጣሩ ከዛም ዓላማችሁን ቁጭ ብላችሁ አስቡ፡፡ ከዚህ ውጪ ከእናንተ የሚጠበቅ ምንም ነገር የለም፡፡

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የአየር መንገዱ የስኬት በረራዎች

**ፍሬሕይወት አወቀ**




ኢትዮጵያ ውስጥ በመንግሥት ከሚተዳደሩና ስኬታማ ከሆኑ ድርጅቶች መካከል ግንባር ቀደሙ ነው። ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ላይ በማስተዋወቅም እንዲሁ ይጠቀሳል፡፡ በዓለም የአቪየሽን ኢንዱስትሪ አየር መንገዱ በሚሰጣቸው ቀልጣፋና ምቹ አገልግሎቶቹ የተነሳ ተፈላጊነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፤ የተሰጡት እውቅናዎችና ሽልማቶችም እንዲሁ በርካታ ናቸው፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፡፡

የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ኩራት የሆነው ይህ አየር መንገድ አገሪቱ አሉኝ ከምትላቸው አንጡራ ሃብቶቿ መካከል አንዱና ትልቁ ሀብቷ ነው። በሚሰጣቸው አገልግሎቶቹ ከኢትዮጵያም አልፎ በአፍሪካ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ለመሆን በቅቷል፡፡ በየጊዜው በሚያስመዘግበው ውጤትም ከስኬት ማማ ላይ በመውጣት አይነ ግቡ መሆኑን ቀጥሏል፡፡

ከሰባት አስርት ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረው አንጋፋው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ጉዞው የተሳካ፣ የተቃናና ትርፋማነቱም አስተማማኝ በሚባል ደረጃ ላይ ስለመሆኑ ያለፉት ዓመታት አፈጻጸሞቹ ይመስክራሉ፡፡

ከፍተኛ ዕድገት የማስመዝገብ አቅም እንዳለው በተጨባጭ ማሳየት የቻለው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስም ሲነሳ ለኢትዮጵያውያን በሙሉ መኩሪያና መመኪያ መሆኑም አብሮ ይነሳል፡፡ በሚሰጣቸው ቀልጣፋ፣ ምቹና ዘመናዊ አገልግሎቶቹ የኢትዮጵያን ስም በመላው ዓለም በበጎ እንዲነሳ እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ሊጠቀስ ይገባዋል፡፡

ይህ በአፍሪካም በዓለም አቀፍ ደረጃም ታዋቂ የሚባሉ አየር መንገዶችን በመወዳደር ታዋቂ መሆን የቻለው ግዙፍ ተቋም በአስገራሚ የዕድገትና የለውጥ ግስጋሴ ላይ ስለመሆኑ ሌሎች ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አየር መንገዱ የአቪዬሽን ዩኒቨርሲቲ እና ብዙ ቢሊዮን ብር አውጥቶ የገነባው ዘመናዊ ሆቴል ባለቤትም ነው፡፡ የካርጎ አገልግሎት በመስጠትም ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ወቅትም አየር መንገዱ ፈተናዎችን ተቋቁሞ ግስጋሴውን በድልና በትርፋማነት የቀጠለ ሲሆን፤ በአፍሪካ ያለውን የቀዳሚነት ስፍራ ማስጠበቅ የሚያስችሉ በርካታ ስኬቶችንም እያስመዘገበ ይገኛል፡፡

ይህ በስኬት ጎዳና ላይ መረማመድን በእጅጉ የተለማመደ ተቋም፣ በቅርቡም በአየር መንገዱ ታሪክ ትልቁ የተባለውና በአፍሪካ አቪዬሽን ታሪክም የመጀመሪያ የሆነውን 67 ቦይንግ ጀት አውሮፕላኖች ለመግዛት ከቦይንግ ኩባንያ ጋር ስምምነት ፈርሟል። በተመሳሳይም ኤር ባስ ከተባለው ኩባንያ ጋርም እንዲሁ 11 ኤር ባስ አውሮፕላኖችን ለመግዛት ስምምነት ተፈራርሟል፡፡ እነዚህ ስምምነቶች አየር መንገዱ በ2035 አሳካዋለሁ ብሎ የያዘውን ራዕይ ለማሳካት ትልቅ ግብዓት በመሆን እንደሚያገለግለው ታምኖበታል፡፡ ስምምነቱ በአፍሪካ ቀዳሚነቱን አጠናክሮ ማስቀጠል የሚያስችለው እንደሆነም ከአየር መንገዱ የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡

በቅርቡ ዱባይ በተካሄደው የ2023 የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ዓውደ ርዕይ ላይ የተገኘው የኢትዮጵያ አየር መንገድ፤ በአንድ ሳምንት ውስጥ 78 አውሮፕላኖችን ለመግዛት ነው ከአሜሪካዎቹ ቦይንግ እና ኤር ባስ ኩባንያዎች ጋር ስምምነት ያደረገው። ከኤር ባስ ኩባንያ ጋር ያደረገው ስምምነት 11 "ኤርባስ ኤ350-900ኤስ" አውሮፕላኖችን ለመግዛት ያስችለዋል። ስምምነቱ እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ስድስት አውሮፕላኖችን ማዘዝ የሚያስችል ዕድል የተካተተበት ነው፡፡ "ኤ350 ኤር ባስ" አውሮፕላን ዘመናዊ እና ቀልጣፋ ሰፊ ሰው ጫኝ እና ከ300 እስከ 410 መቀመጫዎች ያለው የረጅም ርቀት አውሮፕላን ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቦይንግ ኩባንያ ጋር ባሰረው ውል ለመግዛት ከሚያዛቸው 67 አውሮፕላኖች መካከል 11 ዱ "787 ድሪምላይነር" እና 20ዎቹ "737 ማክስ" አውሮፕላኖች ሲሆኑ፣ 36ቱ ደግሞ ሌሎች አውሮፕላኖች ናቸው፡፡

አውሮፕላኖቹ በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ አየር መንገዱ እጅ ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል። አዳዲሶቹ አውሮፕላኖች የተሻሻሉ ሞዴሎች መሆናቸውና የነዳጅ አጠቃቀማቸው ውጤታማነት ከቀደሙት አውሮፕላኖች አንጻር 20 በመቶ የበካይ ጋዞችን ልቀት እንደሚቀንሱ፣ 50 በመቶ የድምፅ ብክለትን እንደሚያስቀሩም መረጃዎች ያመለክታሉ።

የአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ጣሰው ከሁለት ወራት በፊት በቱርክ የኢኮኖሚ መዲና ኢስታምቡል በተካሄደው የዓለም አቪዬሽን ጉባዔ ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአውሮፓውያኑ አቆጣጠር 2035 ላይ የአውሮፕላኖቹን ቁጥር 271 የማድረስ እቅድ እንዳለው ማስታወቃቸው ይታወሳል። የ 130 አውሮፕላኖችን ግዢ እንደሚፈጸምም ገልጸው ነበር። ሁለቱ ስምምነቶች አየር መንገዱ በ2035 ለመድረስ ያስቀመጠውን ራዕይ መሠረት ያደረጉ ስለመሆናቸው መረጃዎች ያመለክታሉ።

አየር መንገዱ በቅርቡ ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት አምባሳደሮች በተገኙበት ከፍተኛ እምርታ ያስመዘገበበትን የካርጎ ደንበኞች ቀንንም አክብሯል። በዕለቱ የተገኙት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው እንዳሉት፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከ67 በላይ በሆኑ መዳረሻዎቹ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የካርጎ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ተመራጭ የካርጎ አየር መንገድ መሆን ችሏል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ አገልግሎት በአፍሪካ ትልቁ የአየር ጭነት አጓጓዥ ነው። 16 አውሮፕላኖችን ለካርጎ አገልግሎት መድቦ አስተማማኝ የካርጎ አገልግሎት እየሰጠ ሲሆን፣ በካርጎ አገልግሎቱ ባለፈው ዓመት ብቻ 740 ሺህ ቶን ጭነት አጓጉዟል።

በተያዘው በጀት ዓመትም የካርጎ አገልግሎቱን ወደ አንድ ሚሊዮን ለማሳደግ እየሠራ ነው። አየር መንገዱ የካርጎ ደንበኞች ቀንን ሲያከብር በዘጠኝ የኤክስፖርት ምድቦች ከፍተኛ አፈፃፀም በማስመዝገብ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ለያዙ 27 ኤክስፖርተሮች እውቅና ሰጥቷል። ዕውቅና የተሰጣቸው ኤክስፖርተሮችም ዕውቅናው በቀጣይ ተግተው መሥራት የሚያስችላቸው እንደሆነና የኢትዮጵያ አየር መንገድ በካርጎ አገልግሎቱ አመርቂ ውጤት እያስመዘገበ እንደሆነ አስታውቀዋል። በዚህም የሀገሪቱ የወጪ ንግድ እንዲያድግ በማድረግ የውጭ ምንዛሬ ግኝቱን ማሳደግ የሚያስችል እንደሆነም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአሁኑ ወቅት 147 አውሮፕላኖች ያሉት ሲሆን፣ ከቦይንግ እና ከኤር ባስ የታዘዙት 78 አውሮፕላኖች ሲጨመሩ የአውሮፕላኖቹ ቁጥር ወደ 225 ከፍ ይላል። የአየር መንገዱ የግዢ ስምምነት የደንበኞቹን ምቾትና ፍላጎት በመጠበቅ ተመራጭነቱን ለማሳደግና ተደራሽነቱን ለማስፋት ከአፍሪካ ቀዳሚ አየር መንገድ ሆኖ መዝለቅ እንዲችል እንደሚያግዘው ይጠበቃል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለደረሰበት ለእዚህ ሁሉ ስኬት የበቃው በበርካቶች አስተዋጽኦ እንደሆነ የአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ መስፍን ጣሰው በአንድ ወቅት ከፋና ብሮድካስቲንግ ሚዲያ ጋር ባደረጉት ቆይታ ገልጸዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ አየር መንገዱ እንደ ዕድል ሆኖ ጥሩ ጥሩ ሥራ አስፈጻሚዎች ገጥመውታል፡፡ በተለያየ ጊዜ አየር መንገዱን የመሩ የሥራ ኃላፊዎች በሙሉ ድርጅቱ እንዲያድግ፣ ትርፋማና ተወዳዳሪ እንዲሆን ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው፡፡ በተለይም መሰረተ ልማቶችን በማሟላት የሰው ኃይሉን በዕውቀት፣ በችሎታ ሲያንጹና ሲቀርጹ ኖረዋል፡፡ በመሆኑም በእነዚሁ ትጉህ አመራሮች አማካኝነት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሁልጊዜም ቀዳሚና ተመራጭ ሆኖ በድልና በስኬት ወደፊት እንዲጓዝ አስችሎታል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድን ስኬታማ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል ሌላው የአገሪቷ መልከዓምድራዊ አቀማመጥ ስለመሆኑም መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ኢትዮጵያ ለአረቡ ዓለም ለአውሮፓም ጭምር በቅርብ ርቀት ላይ የምትገኝ መሆኗ እንዲሁም በአሜሪካና በቻይና መካከል መገኘቷ አየር መንገዱ ትርፋማ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ መሆኑም ይገለጻል፡፡

እንደ ሌሎች የአየር መንገዶች ሁሉ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ፈተናዎች አጋጥመውት እንደነበረ ያስታወሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፣ ያም ቢሆን ጥንካሬውን ይዞ መቀጠል እንደቻለ ነው የተናገሩት፡፡ ሌሎች አየር መንገዶች የሚገጥማቸውን ፈተና መቋቋም ሳይችሉ በመቅረታቸው ሲንኮታኮቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግን በተለይም አፍሪካ ውስጥ ካሉ አየር መንገዶች በብዙ መንገድ ቀዳሚ መሆን ችሏል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ አንድ አይነት አውሮፕላን ሲገዛ አቅም አብሮ የሚገነባ መሆኑንም ዋና ሥራ አስፈጻሚው ለእዚህ አብነት አንስተዋል። የጥገና አቅም፣ የበረራ አቅም፣ ፓይለቶችን በራሱ አቅም የማሰልጠን አቅም መገንባቱን ጠቅሰው፣ ቴክኒሻኖችንም እንዲሁ በውስጥ የማሰልጠን አቅም ያለውና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አቅም በመገንባት ጭምር ወደፊትም የዕድገት ግስጋሴውን የሚቀጥል እንደሆነ ነው ያረጋገጡት፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የአየር ትራንስፖርት ኢንዱስትሪውን ጠንቅቆ እንደሚያውቅ የተናገሩት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ከሌሎቹ አየር መንገዶች ለአብነትም ከሉፍታንዛ፣ ከኤምሬትስና ከሌሎቹም ባልተናነስ መልኩ ኢንዱስትሪውን እንደሚያውቀው ገልጸዋል፡፡ ይህ ሁሉ አየር መንገዱ ወደ ጎን የሚተው እንዳይሆን እንዳደረገው አስታውቀዋል፡፡ በዚህ የተነሳም አየር መንገዱ ከቦይንግ ኩባንያ ጋር ያለው ግንኙነት እጅግ ጥብቅ የሆነና በከፍተኛ ጥንካሬ፣ በዕውቀትና በአቅም ላይ የተመሰረተ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የአየር መንገዱ ፈተናዎችን ተረማምዶ ማለፍ ሲነሳ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ዓለምን ከእንቅስቃሴ ባቀበበት ወቅት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወረርሽኙን ለመከላከል የሚያስችሉ መዳህኒቶችን በማጓጓዝ፣ አየር መንገዶች ሁሉ በተዘጋቡት በዚያ ወቅት አገልግሎት በመስጠት መላ ዓለምን ከከፉ ቀን የታደገ በመሆኑም ይታወቃል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያም አልፎ ለአፍሪካውያን ኩራት መሆን የቻለ ግዙፍ ተቋም እንደሆነ በብዙዎች ዘንድ የሚታመን ሃቅ ነው፡፡ በመሆኑም አየር መንገዱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርጉትን ዘመናዊ መሰረተ ልማቶችና አገልግሎቶች በማሟላት እንዲሁም ባለሙያዎችን በዕውቀት በማነጽ ከአገር ልጆች አልፎ የውጭ ዜጎችን ጭምር በማሰልጠን ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ከከፍታው ከፍ እያለ መብረሩን የቀጠለ ስኬታማ ተቋም መሆን የቻለ አንጋፋና ግዙፍ ተቋም ነው፡፡

ከቀድሞው ትራንስ ወርልድ ኤር ዌይስ ጋር የተመሰረተው የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ ተመራጭና አሉ ከሚባሉ አየር መንገዶች መካከል መጠቀስ ችሏል፤ በአፍሪካ ቀዳሚው አየር መንገድ መሆን ችሏል፡፡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ አየር መንገዱ ሲመሰረት ከአሜሪካ ወታደራዊ ኃይል የተገዙና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ያገለገሉ አምስት ዲሲ አውሮፕላኖች ብቻ ነበሩት፡፡ የመጀመሪያ በረራውንም አህዱ ያለው ከአዲስ አበባ ወደ ግብጽ ካይሮ በመብረር ነው፡፡ ይህም በ1938 ዓ.ም መጋቢት 30 ቀን የተደረገ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በዓለም ዙሪያ በአፍሪካ፣ በእስያ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ ክፍለ አጉራት በ127 መዳረሻዎቹ የመንገደኛና የጭነት አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን፣ በአገር ውስጥ ደግሞ 22 መዳረሻዎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የራሱ የአውሮፕላን አብራሪዎች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ሲኖረው የግል አብራሪና የግል አውሮፕላን አብራሪ ፈቃድ በመስጠት የአገር ልጆችንም ሆነ የውጭ ዜጎችን በማሰልጠን የ40 ዓመታት ልምድ እንዳለውም ይታወቃል፡፡

ለበርካታ የአፍሪካ አገራት ብሔራዊ አየር መንገዶች እና የግል አውሮፕላኖች የጥገና አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የናይጄሪያና አንዳንድ አገራት አየር መንገዶችን ደግሞ በሼር ያስተዳድራል፡፡ የኢትዮጵያውያን ሃብት የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለመንገደኞች አገልግሎት የሚውል አዲስና ዘመናዊ ቦይንግ 787 ድሪም ላይንር አውሮፕላን በማዘዝና ጥቅም ላይ በማዋል ከአፍሪካ የመጀመሪያው አየር መንገድ በመሆን ይጠቀሳል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ሽልማቶችና እውቅናዎች በማግኘትም ይታወቃል፡፡ በአቬየሽን ኢንዱስትሪው በየዓመቱ በሚደረጉ የእውቅናና የሽልማት ስነስርዓቶች ላይ የኢትዮጵያ አየር መንገድ አይታጣም። ለእዚህም ከአውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር 2020 ጀምሮ እስካሁን ድረስ “የአፍሪካ ምርጡ አየር መንገድ” የሚል ሽልማት “Business Traveller Awards” ማግኘቱን በአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የቃሊቲ ሞዴል መናኸሪያ ግንባታ - በማጠናቀቂያ ምዕራፍ

በኃይሉ አበራ

በአገሪቱ በቀጣይ ለሚገነቡ መናኸሪያዎች ሞዴል ተደርጎ በዘመናዊ መልኩ እየተገነባ የሚገኘው የቃሊቲ መናኸሪያ፣ በአንድ ጊዜ ከ120 በላይ አገር አቀፍ አውቶቡሶችን እንዲያስተናግድ ተደርጎ እየተገነባ ነው። አጠቃላይ ግንባታው በሶስት ነጥብ ዘጠኝ ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፍ ሲሆን፣ የመናኸሪያ ተርሚናሉ ዘመናዊ ሕንፃ ግንባታ ብቻ በአምስት ሺህ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ነው፡፡ ሕንፃው አምስት ወለሎችም (G+4) አሉት፡፡

የመናኸሪያ ግንባታው ውል የተገባው ሚያዝያ 6 ቀን 2011 ዓ.ም ቢሆንም፣ ግንባታው በተለያዩ ምክንያቶች ተጓትቶ ቆይቷል፡፡ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ባለቤትነት እና በኤፍኢ (EFE) ኮንስትራክሽን ደረጃ አንድ የሀገር ውስጥ ተቋራጭ ተቋራጭነት በአንድ ነጥብ አንድ ቢሊየን ብር እየተገነባ የሚገኘውን የዚህን መናኸሪያ ግንባታ በመጪው ጥር ወር መጨረሻ ለማጠናቀቅ እየተሰራ ነው፡፡

በትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የመሠረተ ልማት ማስፋፊያ ባለሙያ እና የቃሊቲ መናኸሪያ ግንባታ ፕሮጀክት መሪ መሀንዲስ አቶ ሚኪያስ ታደሰ እንደሚሉት፤ ፕሮጀክቱ 540 የመጀመሪያ የውል ቀናት የነበሩት ሲሆን፣ በመስከረም 14 ቀን 2014 ዓ.ም ለማጠናቀቅ ታቅዶ ነበር የተጀመረው፡፡ ይሁንና በዲዛይን ለውጥ እና በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ግንባታው በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ሊጠናቀቅ አልቻለም።

አጠቃላይ የፀደቀ የውሉ ጊዜ ማራዘሚያ 682 ቀናት እንዳሉት የጠቀሱት መሪ መሀንዲሱ፣ የግንባታ ማጠናቀቂያ ጊዜውም ሕዳር 12 ቀን 2015 ዓ.ም እንደነበረም አስታውሰዋል። ይሁንና ሌላ የዋጋ ማሻሻያ እንደተደረገለት ተናግረዋል፤ በዋጋ ማሻሻያው ጊዜ ተሰጥቶት ተቋራጩ እስከ ጥር 30 ቀን 2016 ዓ. ም የፕሮጀክቱ የመጨረሻ ቀሪ ስራዎችን አጠናቆ እንዲያስረክብ የጊዜ ሰሌዳ መቀመጡንም አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የመናኸሪያ ሕንጻ ግንባታው አሁን ላይ የፊዚካል አፈፃፀሙ 78 በመቶ ደርሷል፤ እስካሁን የፈጀው ጊዜም 125 በመቶ ነው፣ ግንባታው ክረምት ላይ ተቀዛቅዞ የነበረ ቢሆንም፣ አሁን ከለቀማና ከማጠናቀቂያ ስራዎች በቀር አብዛኛው የግንባታ ስራ እየተጠናቀቀ ይገኛል።

የመናኸሪያ ሕንፃው ግራውንድ + ሚዛኒ + አራት ሲሆን፣ ለቢሮ፣ ለሱቅ፣ ለካፍቴሪያ፣ ለመሡብሰቢያ አዳራሽ፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ የሚውሉ ቢሮዎችንም አካቶ ይዟል። አገልግሎቱም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ተደርጎ እየተገነባ ይገኛል፡፡

መናኸሪያው በኢትዮጵያ ሞዴል መናኸሪያ ሆኖ እየተገነባ ነው፡፡ የእቃ ማጓጓዣንና የሕዝብ ማጓጓዣን በመለየት የማጓጓዝ ሂደቱን ከመግቢያው አንስቶ እንዲዘመን ይደረጋል፤ የተሳፋሪዎች እና የተሽከርካሪው እንቅስቃሴ በማይጋጭበት ሁኔታ መናኸሪያው የራሱ የሆነ ከፀሐይ እና ከዝናብ መከላከያ ሼድ ይኖረዋል። የቲኬት መቁረጫ ፋሲሊቲዎችን ጨምሮ የመቆያ ቦታዎች እና አውቶብሶቹ የት እንዳሉ መረጃ የሚሰጡ ሲስተሞች ይገጠሙለታል፡፡ አውቶቡሶቹ ሲገቡም ሆነ ሲወጡ ዘመናዊ የሆነ እና በካርድ የታገዘ የመቆጣጠሪያ የክፍያ እና የደህንነት ሲስተሞች አሉት። የፓርኪንግ ካርድ ከፍለው በሲስተም የሚገቡበት እና የሚወጡበት አሰራር ይተገበርበታል፤ ይህም ሕገወጥ ስምሪትን ለመከላከል ያስችላል፡፡

ተቋሙ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር እንዲሆን ታስቦ መናኸሪያው እየተገነባ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ከትራንስፖርት አገልግሎት ውጪ ያሉ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ተደርጎ እየተገነባ እንደሚገኝ ተናግረዋል፤ ለዚህም በሞል ደረጃ የሚገነባ ሲሆን፣ ሱቆች፣ ባንኮች፣ ካፍቴሪያዎች እና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች የሚውሉ ክፍሎች ይኖሩታል፡፡ አገልግሎቶቹም ከትራንስፖርት አገልግሎቱ ጋር እንዳይቃረኑ ተደርገው የሚሰጡ ይሆናሉ፡፡ ሁለት አሳንሰር ወይም ሊፍት የሚኖረው ሲሆን፣ በሶስት ቦታዎችም ደረጃዎች ይኖሩታል።

ከመናኸሪያው ሕንፃ ፊት ለፊትም ለከተማ አውቶብሶች እንዲሁም ሌሎች የግል መኪና እና የታክሲ ማቆሚያ ሰፊ ቦታም አለው። በምድረ ግቢው ዶክ የሚባለው እና ከሕንፃው ጋር የሚገናኘው ተሳፋሪዎች ጸሀይና ብርድ ሳያገኛቸው የሚያርፉበትና ወደ መኪና የሚገቡበት ቦታ ተያይዞ ተገንብቶለታል፡፡ ግቢው ሶስት መውጫና መግቢያ በሮች የሚኖሩት ሲሆን፣ በቂ ጥበቃ ማድረግ የሚያስችሉ የጥበቃ ቤቶች ይኖሩታል፡፡



የቃሊቲ መናኸሪያ ህንፃ የፊትለፊት እይታ ፣



አቶ ሚኪያስ ታደሰ ፣



አቶ ሰይፉ ክንፉ፣

የምድረ ግቢው የአስፓልት ስራ እየተካሄደ መሆኑን አቶ ሚኪያስ ጠቁመው፣ ግንባታው አስፋፓልት እና ሰብ ኮርስ የሚባሉ ሁለት ንብርብር ስራዎች እንደሚቀሩት አቶ ሚኪያስ ተናግረዋል፡፡ የግቢ ስራው ብዙም እንደማያቆይ ጠቅሰው፣ ትልቁን ስራ የሚይዙት የሕንፃ ለቀማ እና የማፅዳት ስራዎች መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የግንባታው ሂደት እንዲዘገይ ዋነኛው ምክንያት በስፍራው የነበረውን የፖሊስ ካምፕ ለማንሳት ጊዜ መውሰዱ መሆኑን ጠቅሰው፣ የአየር ፀባይ፣ የዋጋ ማሻሻያ ሂደቶች እና በመሀል የነበሩ የዲዛይን ጉዳዮች ለግንባታው መጓተት ሌሎች ምክንያቶች መሆናቸውንም አመልክተዋል። ለተቋራጩ ክፍያ በወቅቱ አለመፈፀሙም የተወሰነ መዘግየት እንዲከሰት ምክንያት መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡ ሁሉም የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተሰጥቷቸው በአሁኑ ወቅት ግንባታው ወደ ማጠቃለያ ምዕራፍ መግባቱንም ገልፀዋል።

በትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የመሠረተ ልማት መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ ሰይፉ ክንፉ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ የቃሊቲ ዘመናዊ መናኸሪያ ተርሚናል ግንባታ ዘመናዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጎ እየተገነባ የሚገኝ ሲሆን፣ ከዲዛይን ጀምሮ መሟላት ያለባቸው አስፈላጊ ፋሲሊቲዎች ተለይተው የተካተቱበትም ነው፡፡

አየር መንገድን ከመሣሠሉ አንጋፋ ተቋማት ተሞክሮ በመውሰድም የጉዞ ፕሮግራም ማሳያ ስክሪኖች ጭምር እንደሚኖሩትም አቶ ሰይፉ ገልጸዋል፡፡ አውቶቡሶቹ በተመደበላቸው ሰዓት መሰረት ወደ አገልግሎቱ እንዲገቡ የሚደረግበት ሁኔታ እንደሚኖርም ጠቁመዋል። ተሳፋሪው መናኸሪያው ውስጥ ጓዙን ተሸክሞ የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ እንደማይኖርና ለእቃው ደረሰኝ ተሰጥቶት ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እቃው ለብቻው ተጭኖ ወደ አውቶብሱ የሚጓጓዝበት ዘመናዊ አሰራር የሚተገበርበት ነው ብለዋል።

ውጫዊና ውስጣዊ ችግሮች ባያጋጥሙ ፕሮጀክቱን መስከረም 30 ቀን 2016 ለማጠናቀቅ ታቅዶ እንደነበረ አቶ ሰይፉም ገልፀው፣ በዝናብ ወቅት መራዘም ምክንያት በሳይት ስራው ላይ የደረሰውን ብልሽት ለማስተካከል ግንባታው በአዲስ መልኩ እየተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል። ይህ በራሱ የፈጠረው ጫና እንዳለም ጠቅሰው፣ ጥራቱን አስጠብቆ መስራቱ ለድርድር እንደማይቀርብ ገልጸዋል። አሁን ባለው የስራ መርሀ ግብር መሠረትም ጥር 30 ቀን 2016 ዓ.ም ግንባታውን ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በፕሮጀክቱ ስራ ካጋጠሙት ችግችሮች መካከል የአየር ፀባይ አንዱ መሆኑን አቶ ሰይፉም ይገልጻሉ፡፡ ሁለተኛውም ችግር ለግንባታው የሚያስፈልገውን ገንዘብ በተፈለገው መጠን አለማግኘት መሆኑንም ተናግረዋል። ከፋይናንስ ጋር የተያያዘውን ችግር መንግሥት ፕሮጀክቱ ሞዴል መናኸሪያ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት በሰጠው ትኩረት ችግሮቹ መፈታታቸውን ገልጸዋል፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴር የአገር ፕሮጀክት መሆኑን በመረዳት በቅርበት እገዛ እያደረገ መሆኑንም አመላክተዋል።

መናኸሪያው በዋናነት ታሳቢ ተደርጎ እየተገነባ የሚገኘው አገር አቋራጭ አገልግሎትን እንዲሰጥ ተደርጎ ነው ያሉት አቶ ሰይፉ፣ አሁን በአገራችን ከሚታዩ ተሽከርካሪዎች ውጪ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ መሥሪያ ቤት በሕዝብ ትራንስፖርት በኩል በርካታ ሰዎችን በአንድ ጊዜ ለሚያንቀሳቅሱ አገልግሎቶች አቅዶ እና ፖሊሲ ቀርፆ እየሰራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የቃሊቲ መናኸሪያም አገር አቋራጭ ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሰራ እና ሌሎች ጎን ለጎን የሚሰሩ ሥራዎች መኖራቸውንም ገልፀዋል። 120 አገር አቋራጭ አውቶቡሶች አንድ ጊዜ የሚንቀሳቀሱበት መሆኑን ጠቅሰው፣ በመጠባበቂያ ያሉትን ያካተቱ ተጨማሪ መሠረተ ልማቶች ተሰርተው እስከ 30 እና 40 ዓመታት ሊያገለግል እንዲችል ተደርጎ እየተገነባ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በቅርቡም ለማሕበረሰቡ ተጨማሪ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ እና ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተያያዙ ግንባታዎችን ለማድረግ የማስፋፊያ ቦታ ከከተማ አስተዳደሩ መጠየቁንም አቶ ሰይፉ ገልጸዋል፡፡ ለእዚህም ምላሽ ከተገኘ በኋላ ተጨማሪ ስራዎችን በማካተት የሕብረተሰቡን የአገልግሎት ፍላጎቶች ለመመለስ እንደሚሰራም አመልክተዋል።

አሁን እየተሰራ የሚገኘው በየሰዓቱ እና በየደቂቃው ለሚንቀሳቀሱ አውቶቡሶች መሆኑን ገልፀው፣ በዚያው አካባቢ በሚደረገው ተጨማሪ ማስፋፊያም ተገልጋዮች ርቀው ሳይሄዱ ሌላ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚጠብቁበት ቦታ መዘጋጀት አለበት በሚል የቦታ ጥያቄው መቅረቡን ጠቁመዋል። መንግስትም ሆነ ከተማ አስተዳደሩ ይህንን እንደሚደግፉ ጠቅሰው፣ በቅርቡ አካሄዱን ጠብቆ ጥያቄው ምላሽ ያገኛል የሚል ተስፋ እንዳላቸውም አስታውቀዋል፡፡ አካባቢው የሕዝብ አገልግሎት መስጫ መሆኑን ጠቅሰው፣ የፍሳሽ መልሶ ጥቅም ማዋያ መሰረተ ልማት /ሪሳይክል ማድረጊያ/ መስሪያ ቦታ መጠየቁንም አስታውቀዋል።

አቶ ሰይፉ እንዳሉት፤ የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማዘመን መሠረተ ልማት ላይ ትኩረት መስጠት ይገባል። እስከ አሁን የሚሰጠው አገልግሎት ማንንም እያረካ አይደለም። ተገልጋዩን ብቻ ሳይሆን አገልግሎት ሰጪውን አካል ጭምር እያረካ አይደለም። በመሆኑም ይህ ዘመናዊ መናኸሪያ አንድ ዘመናዊ መናኸሪያ ሊሰጥ ከሚገባው አገልግሎት እና አቅርቦት አኳያ ተገልጋዩ ሳይጉላላ የሚፈልገውን ምቹ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል ነው።

የመናኸሪያው አገልግሎት የውጭ ዜጎችንም ታሳቢ እንደሚያደርግ አቶ ሰይፉ ጠቁመዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ በመናኸሪያዎች አካባቢ የሚሰጡ አገልግሎቶች ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን አገራችን በትኩረት እየሰራችበት የምትገኘውን የቱሪዝም ዘርፍንም ታሳቢ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህ አይነቱ አገልግሎት የአገሪቱን ገፅታ በከፍተኛ ሁኔታ የሚቀይር ከመሆኑም ባሻገር፣ ቱሪስቶች ኢትዮጵያ ውስጥ በሕዝብ ትራንስፖርት ለመንቀሳቀስ ሲፈልጉ ልዩ አገልግሎት ለመስጠት በሚቻልበት ደረጃ እና በሚፈልጉት ልክ እንዲዘምን የመናኸሪያው ፋይዳ ከፍተኛ ይሆናል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገዱ ሁሉ ደረጃውን የጠበቀና የአፍሪካ ኩራት የሆነ ዘመናዊ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ታሳቢ ያደረገ ስታንዳርድ ለማምጣት እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል። ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ላይ ሕብረተሰቡ ሳይጉላላ እና ሌሊት ተነስቶ መሠለፍ ሳይኖርበት በኦንላይን ቲኬት የሚያገኝበት አሰራር ተዘርግቶ እየተሰራ መሆኑንም አስረድተዋል።

ይሄንን ምቹ በማድረግም ማንም ሰው ሰዓቱን አስተካክሎ እና ቲኬቱን በእጁ ይዞ ሊሳፈር የሚችልበትን አሰራር በመዘርጋት ተገልጋዩን ማርካት እና የአገርንም ገፅታ መገንባት ታሳቢ ተደርጎ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ ብቻውን በቂ እንዳልሆነም አቶ ሰይፉ ተናግረዋል፡፡

በነባሩ የአውቶቡስ ተራ ትልቁ እና ትንሹ መናኸሪያም እንዲሁ አዲስ እና ልዩ ግንባታ እንደሚካሄድም አቶ ሰይፉ ጠቁመዋል፡፡ የዚህ ግንባታ የዲዛይን ስራ አልቆ ወደ ተግባር እንደሚገባ ጠቅሰው፣ ግንባታው የከተማዋን ገፅታ እንደሚቀይረውም ተናግረዋል፡፡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም በሕዝብ ማመላለሻ መናኸሪያዎች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በደረቅ ጭነት እና ፈሳሽ ጭነት ላይም እንዲሁ ደረጃዎችን አዘጋጅቶ ከየክልል አስተዳደሮች ጋር ግንባታዎችን እያካሄደ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የኮንስትራክሽን ዘርፉ ከግብርና ቀጥሎ በአገር ላይ ከፍተኛ የሥራ እድል እየፈጠረ እንደሚገኝ አመልክተው፣ የቃሊቲ መናኸሪያ ግንባታው ለበርካታ ሰዎች የስራ እድል መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡

ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ግንባታው ለ228 ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠሩ ተጠቁሟል፡፡ በየዓመቱ በአማካይ ለአንድ ሺ 392 ሰዎች ደግሞ ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠሩም ተገልጿል፡፡

ፕሮጀክቱ ተጠናቆ ስራ ሲጀምርም በተመሣሣይ በርካታ ቋሚና ጊዚያዊ የሥራ እድሎችን እንደሚፈጥርም አቶ ሰይፉ አስታውቀዋል።

በሌሎች መናኸሪያዎችም ዘመናዊ አገልግሎቱን ለማስፋት እንደሚሰራ ጠቁመው፣ በተመሳሳይ ደረጃ በላምበረት፣ በአየር ጤና እና አስኮ መናኸሪያዎች ትልቅ ስራ እየተሰራ መሆኑን ገለፀዋል። በዚህም ሕብረተሰቡ ደህንነቱ የተጠበቀ አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ ፕሮጀክት ተቀርፆ እና ጨረታ ወጥቶ ለትግበራ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ በዚህም መናኸሪያዎቹን ወደ ቃሊቲ መናኸሪያ ስታንዳርድ በሂደት የማምጣት ስራ እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

የአገር አቋራጭ ትራንስፖርት ተጠቃሚው በማለዳ የሚነሳ መሆኑን አቶ ሰይፉ ተናግረው፣ በመናኸሪያዎች አካባቢ ያለው የመብራት አገልግሎት ስታዲየም ላይ በማታ እንደሚታየው ያህል የደመቀ እንዲሆን እንደሚደረግም አስታውቀዋል። ሕብረተሰቡ የሚፈልጋቸውን አገልግሎቶች እንዲያገኝ በሚያስችል መልኩ መናኸሪያዎቹ እንደሚዘጋጁም ጠቁመዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የበጋ ስንዴ ምርት የኢትዮጵያ የብልጽግና ዘመን መቃረብ ማሳያ ነው!

ሀገራችን ኢኮኖሚያቸው በግብርና ላይ ከተመሠረቱ የዓለም ሀገራት አንዷ ተደርጋ የምትጠቀስ ነች። ለዘርፉ የሚስማማ የተፈጥሮ አካባቢ፤ ሰፊ የውሀ እና የሰው ሀብት ባለቤትም ናት። እነዚህን አቅሞች ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ አቀናጅታ መንቀሳቀስ ከቻለች ነገዎቿ ብሩህ ስለመሆናቸው ብዙዎች ይስማማሉ ።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በሀገራችን የከርሰ ምድር ውኃን ሳይጨምር 123 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የሚጠጋ የውኃ ሀብትና ከ36 ሚሊዮን ሔክታር በላይ ሊለማ የሚችል መሬት አለ፤ ከዚህ ውስጥ እስካሁን እየለማ ያለውም 16 ሚሊዮን ሔክታር ያህሉ ብቻ ነው፡፡

ከዚህ ውስጥ ከ5 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር በላይ በመስኖ የሚለማ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥም እስካሁን የለማው ከ1.1 ሚሊዮን ሄክታር የበለጠ አይደለም፤ ይህም ሀገሪቱ በዘርፉ ምን ያህል የቤት ሥራ እንደሚጠብቃት በተጨባጭ አመላካች ነው።

እንደ ሀገር በግብርናው ዘርፍ /በእርሻ/ ያለንን ይህንን ሰፊ አቅም ወደሚጨበጥ አቅም በመለወጥ፤ ሀገርን ከምግብ እህል ተመጽዋችነት ለመታደግ መንግሥት ባለፉት አራት ዓመታት ሰፋፊ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል።

በተለይም ሀገሪቱ ለስንዴ ምርታማነት ያላትን አመቺና ሰፊ የተፈጥሮ አካባቢ/መሬት/ እና የውሀ ሀብት በማቀናጀት እያካሄደ ያለው የበጋ መስኖ ልማት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ እውቅናን በማትረፍ፤ ለተሞክሮነት ተመራጭ እየሆነ ይገኛል።

ሀገራችን ከሰሃራ በታች ካሉ የአፍሪካ አገሮች ስንዴን ለማምረት የሚበቃ የተሻለ በቂ መሬት፣ ውኃ፣ አምራች ኃይል ባለቤት እንዳላት፤ ከሰሐራ በታች ካሉ የአፍሪካ ሀገራትም በስንዴ ምርት ቀዳሚ ስለመሆኗ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ደግሞ በሀገሪቱ ከአሥር ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮች ስንዴ በማምረት ላይ ተሠማርተዋል፤ ይህ አኃዝ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ አርብቶ አደር 25 በመቶ የሚሆነውን የሚሸፍን ነው ፡፡

ይህም ሆኖ ግን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሀገሪቱ በየዓመቱ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር ያላነሰ ወጪ በማድረግ ስንዴ ከውጪ ስታስገባ ቆይታለች፡፡ ለዚህ የሚሆን የውጪ ምንዛሪ ማግኘቱ በራሱ የቱን ያህል ትልቅ ሀገራዊ ፈተና እንደነበርም የሚታወስ ነው ፡፡

ይህንን እውነታ ለመለወጥ ባለፉት አራት ዓመታት በመንግሥት በኩል ሰፋፊ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ እየተሠሩም ነው። በተለይም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ዙሪያ እየተከናወኑ ያሉ ሀገራዊ ሥራዎች ተስፋ ሰጭ ከመሆን አልፈው፤ የሚጨበጥ ስኬት መገለጫ ሆነዋል፡፡

እስካሁንም በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት በዘር ተሸፍኗል። በያዝነው ዓመት በበጋ በመስኖ ልማት ብቻ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ ሰብል በመሸፈን 147 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡

ባለፉት አራት ዓመታት በስንዴ ልማቱ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ በመሠራቱ ቀደም ባሉት ጊዜያት ቢሊዮን ዶላሮችን ወጪ በማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የነበረውን ስንዴ ሙሉ በሙሉ ማስቀረት ተችሏል፡፡ ይህ በራሱ አዲስና ተስፋ ሰጪ ስኬት ነው፡፡

ከዚህም በላይ "በይቻላል" መንፈስ መነቃቃት ወደ ሥራ የተገባበት የበጋ የመስኖ ስንዴ ልማት፤ በርግጥም ቁርጠኝነት ካለ የሀገርን ትናንቶች የሚቀይሩ ሥራዎችን ዛሬ ላይ መሥራት እንደሚቻል በተግባር ያሳየ ነው።

እንደ ሀገር በምግብ እህል ራሳችንን በመቻል ከጠባቂነት ለመላቀቅ ለጀመርነው ሀገራዊ ጥረትም ሆነ ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ለጀመርነው እልህ አስጨራሽ ትግል አቅም መሆን የሚያስችል ትልቅ ውጤት ነው። በግብርናው ዘርፍ እንደ ሀገር ያስመዘገብናቸው ስኬቶች ዋነኛ መገለጫ ተደርጎም የሚወሰድ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሀገራችን የባሕር በር ጥያቄ እና አንድምታው

ሜላት ኢያሱ

የምንኖርባት ፕላኔት ሦስት አራተኛዋ በውሃ የተሸፈነ እንደሆነ ይነገራል፡፡ መቶ በመቶ በገጸ-ምድሯ ላይ የፍጡራንን አስትንፋስ የሚያስቀጥል አየር ይናኝባታል፡፡ ብርሃንና ጨለማ ጊዜያቸውን ጠብቀው ይፈራረቁባታል፡፡ ፍጡራን ከመሬት፣ ከውሃ፣ ከአየር፣ ከፀሐይ ብርሃን በሚያገኙት የተፈጥሮ ፀጋ ሕይወት ይቀጥልባታል፡፡

እነዚህ የተፈጥሮ ፀጋዎች ለፍጡራን ያለከልካይ የተሰጡ በረከቶች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ፍጡር በምድር ላይ መኖር የቻለው ምድር ለሕይወት መቀጠል የሚያስፈልጉ ነገሮችን አሟልታ በመያዟ ነው፡፡ ከነዚህ ፀጋዎች አንዱ እንኳን ቢጓደል ሕይወት አይቀጥልም፤ ይህ ደግሞ የተፈጥሮ ሕግ ነው፡፡

ሰው ቁጥሩ ጨምሮ በከለር፣ በብሔር፣ በቋንቋ በጎሳ እየተከፋፈለ ወሰን አካሎ ይሄ የኔ፣ ይሄ ያንተ፣ ማለት ከመጀመሩ በፊት መሬትም ብትሆን ፍጡራን ያለምንም ከልካይ የሚጠቀሙባት የተፈጥሮ ስጦታ ስለመሆኗ ማንም አይከራከርም፡፡

ዛሬ የሰው ልጅ በመሬት ሀብት ላይ እንዳስፈለገው የሚያዝበት ጊዜ አብቅቷል፡፡ ዓለም በአህጉር፣ በሀገር፣ በክፍለሀገር፣ በወረዳ፣ በቀበሌ መሸንሸኗን ተከትሎ እንደ ጥንቱ ወይም እንደ ዘመነ ፍጥረት በዘፈቀደ ከአንድ አህጉር ወደሌላ አህጉር፣ ከአንድ ሀገር ወደሌላ ሀገር ሄዶ የሚኖርበት ሁኔታ የለም፡፡ የመሬት ነገር ሥርዓት ተበጅቶለታል፡፡

እርግጥነው በአንድ አካባቢ የሚኖር ማኅበረሰብ የአኗኗር ሥርዓቱ፣ ቋንቋው፣ ባህሉ፣ ወጉና እምነቱ በብዙ ምክንያቶች ከሌላው ሊለይ ይችላል፡፡ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ በሚኖርበት አካባቢ ጤናማ መስተጋብር እንዲኖር የራሱን መተዳደሪያ ሕግና ሥርዓት አበጅቶ መኖር ግድ ይለዋል፡፡

ዓለምን በአህጉርና በሀገር የሸነሸናት አንዱ ምክንያት የሰዎች ማኅበራዊ መስተጋብርና የአኗኗር ሥርዓት ነው፤ (ለተለያዩ አገሮች መፈጠር ቅኝ ገዢዎች ያሳደሩት ተፅዕኖ ሳይረሳ ማለት ነው፡፡) እነዚህ ሁኔታዎች ሀገራት የራሳቸውን ድንበር እንዲያካልሉ፣ የራሳቸውን መተዳደሪያ ሕግ እንዲያወጡ፣ የራሳቸውን ባንዲራ እንዲያውለበልቡ አድርገዋል፡፡

እንግዲህ መሬት በዚህ መልክ ባለቤት ኖሯታል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ዓለማችንን ተቆጣጥሮ ‹‹Man-age›› አድርጎ ለመኖር ጠቀመን እንጂ አልጎዳንም። እንደውም በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በልማትና እድገት የፉክክርና የትብብር መንፈስ ይዘን ዓለምን እንድንለውጣት ረድቶናል፡፡

ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችና ሐይቆች እንደምንተ ነፍሰው አየር እና እንደፀሐይ ብርሃን የዓለም ሕዝብ በጋራ የሚጠቀማቸው ተፈጥሯዊ ሀብቶች እንጂ እንደ መሬት የጥቂት ሀገር ንብረት የመሆን ባሕሪ የላቸውም። የዓለም ሀገራት የሰማይ ግዛታቸውን ለአውሮፕላን ትራንስፖርት ክፍት በማድረጋቸው እና በትብብር በመሥራታቸው ተጠቃሚ የሆነው የዓለም ሕዝብ ነው፡፡

ልክ እንደዚህ ሁሉ ሐይቆችና ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን በጋራ የመጠቀሙ ጉዳይ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ተጠቃሚ የሚያደርገው ሁሉንም ነው፡፡ ከሰሞኑ የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕር በር ፍላጎት ማሳየቱ ያልተመቻቸው፣ ያስኮረፋቸውና ያስገረማቸው አካላት ተፈጥረዋል፡፡

ውቅያኖስ ግዙፍ ነው፤ የዓለም ሀገራትንም ያስተሳስራል፤ እና ይህ ዓለምን የሚያካልል የተፈጥሮ ፀጋ ሰው በሆነ አጋጣሚ ድንበር አካሎ ለፈጠራቸው አንድና ሁለት ሀገራት ብቻ መጠቀሚያ እንዲሆን ተብሎ የተፈጠረ አለመሆኑን እንኳንስ ሀገርን የሚመሩ ታዋቂ ሰዎች ይቅርና ሕጻን ልጅም ሊረዳው የሚችል እውነት ነው፡፡

ኢትዮጵያ በአቅራቢያዋ በሚገኝ ባሕር /ቀይ ባሕር/ የመጠቀም መብቷ ተፈጥሯዊ ነው፤ (ታሪካዊ እውነታዎች ሳይረሱ ማለት ነው፡፡) በባሕሩ መጠቀም የሚችሉት እጅግ በጣም በቅርበት ያሉና በእጃቸው መንካት የሚችሉት ብቻ ሳይሆኑ የሰው ልጆች ሁሉ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር በ60 ኪሎሜትር ርቀት ላይ ተቀምጣ እንደ ነጠላ ጥለት በውሃው ዳር ቀጭን መስመር ሠርተው የተቀመጡ ሀገራት ብቻ ብቸኛ ተጠቃሚ እንሁን ቢሉ ዓለም ከሚከተለው የትብብርና የዲፕሎማሲ መንገድ አንጻር የሚያዋጣቸው አይሆንም፡፡

ከዚህ አንጻር የዓለምን ተሞክሮ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳይ ዲፓርትመንት እንደ እ.ኤ.አ ከ2005 እስከ 2015 International Decade for Action ‹‹ WATER FOR LIFE›› በሚል ርዕስ ባጠናው ጥናት በዓለማችን የውሃ ጥራት እየተጓደለ በአንጻሩ የውሃ ተጠቃሚነትና ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱን ይጠቅሳል፡፡ በውሃ የተነሳ በሀገራት መካከል አለመግባባት እየተፈጠረ እንዳለና ውሃ ፖለቲካዊ ጉዳይ እስከመሆን እንደደረሰም ያትታል፡፡

ይሁንና አንዳንድ ሀገራት በማይገመት ሁኔታ ምንም አይነት ግጭት ውስጥ ሳይገቡ በትብብርና በመግባባት የጋራ ተጠቃሚነታቸውን ሲያረጋግጡ ይታያል ይላል፡፡ በውሃ ይገባኛል ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችን እና አለመግባባቶችን ለመቆጣጠር ብቸኛው መንገድም ዲፕሎማሲ እንደሆነ ጥናቱ ዓለማቀፍ ተሞክሮዎችን ዋቢ አድርጎ ይገልጻል፡፡

ጥናቱ ይፋ ከተደረገበት ጊዜ አስቀድሞ ባሉት 50 ዓመታት ውስጥ በውሃ ምክንያት ስምምነት ካደረጉና ለናሙና ከተወሰዱ 150 አገሮች ውስጥ ሠላሳ ሰባቱ ብቻ ውዝግብ ውስጥ መግባታቸው ተመላክቷል። አብዛኛዎቹ ግን ስምምነታቸውን ጠብቀው ዓለም አቀፍ ግንኙነታቸው ሳይሻክር እየኖሩ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡

እንደ ዓለም አቀፉ የምግብና የእርሻ ድርጅት መረጃ ደግሞ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ከ805 ዓመት ጀምሮ ከውሃ ጋር በተያያዘ ከ3 ሺህ 600 በላይ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ተደርገዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ ስምምነቶች ከመርከቦች መጓጓዣ ጋር ተያይዞ በሐይቆች ይገባናል ወሰን ላይ ያተኮሩ ነበሩ፡፡

ባለንበት ክፍለ ዘመን ግን ውሃ የሕልውና ጉዳይ እየሆነ መምጣቱን ተከትሎ በውሃ ሀብት በመልማት፣ የውሃ ሀብትን በጋራ በመጠቀምና በመጠበቅ ላይ ያነጣጠሩ ስምምነቶች እየበዙ መምጣታቸው ተመላክቷል፡፡ ሌላው ቀርቶ ሀገራቱ በሌላ ጉዳይ ግጭት ውስጥ ቢገቡ እንኳ በውሃ ጉዳይ ያደረጉትን ስምምነት የሚያስከብር ውል ይፈራረማሉ ይላል፡፡

በሰነዱ ላይ እንደተመላከተው፤ ካምቦዲያ፣ ላሆስ፣ ታይላንድ እና ቬትናም በማኮንግ ወንዝ ላይ የጋራ ተጠቃሚነታቸውን የሚያረጋግጥ ስምምነት እ.ኤ.አ በ1957 ተፈራርመዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ1955 እስራኤል እና ጆርዳን የጆርዳን (ዮርዳኖስ) ወንዝን በጋራ መጠቀም የሚያስችላቸውን ስምምነት አድርገዋል፡፡

የናይል ወንዝም ድህነትን ለመዋጋትና ኢኮኖሚን ለማሳደግ በቀጣናው የሚጫወተውን ሚና ታሳቢ ባደረገ መልኩ አስር የተፋሰሱ አባል አገራት እ.ኤ.አ ፌብረዋሪ 1999 በጋራ ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራርመዋል ይላል፡፡ በተመሳሳይ ዘጠኙ የኒጀር ወንዝ ተፋሰስ አባል አገራትም በጋራ የመጠቀም ስምምነት ማድረጋቸውን ሰነዱ ይጠቅሳል፡፡

እንደ ጥናቱ ማብራሪያ እነዚህ ስምምነቶች ዓለም አቀፍ የውሃ ሃብት ትብብርን አስመልክቶ ሁለት ወሳኝ ጉዳዮችን አሳክተዋል፡፡ የመጀመሪያው የሁሉንም ሀገራት ተሳትፎና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የሚችል ተቋም እንዲፈጠር ማድረጋቸው ሲሆን ሁለተኛው ለጋራ እድገትና ብልጽግና ምቹ የሆነ አመኔታ የሚጣልበትና ድጋፍ የሚደረግለት የትብብር ተቋም እንዲፈጠር ማስቻላቸው እንደሆነ ይጠቅሳል፡፡

ኢትዮጵያም የባሕር በር ጥያቄ ማቅረቧ የወጪ ገቢ ንግዷን ከማሳለጥና ከጎረቤት አገራት ጋር በትብብር ሠርቶ እድገትና ብልጽግናን ከማረጋጋጥ ያለፈ ፍላጎት የላትም፡፡ ስለዚህ ጥያቄዋ የመጪውን ዘመን ፍላጎት የዋጀና በቀጣናው ሀገራት መካከል የትብብር መንፈስ ተፈጥሮ ሕዝቦችን ከድህነትና ከጉስቁልና ሕይወት ለማላቀቅ ያለመ ነው፡፡

# እንዲህም ይኖራል

**ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።**

## ኑሮን በፈተና - ሕይወትን በፅናት

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

### የካሳሁን እናት

አዲስ አበባ ጳውሎስ ሆስፒታል ጀርባ የተወለደው ብላቴና ኑሮና ሕይወቱ ምቹ አልነበረም፡፡ በብቸኝነት የሚያሳድጉት እናቱ ስለእሱ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል። እናት በቂ መተዳደሪያ የላቸውም፡፡ ለእሳቸውና ለትንሹ ልጅ ጉሮሮ ሁሌም ሮጠው ያድራሉ፡፡

ወይዘሮዋ ገጠር ብቸና ሳሉ ልጆቻቸውን ትተው ወጥተዋል፡፡ አዲስ አበባ ከመጡ የወለዱት ካሳሁንን ነው፡፡ የካሳሁን ብቸኛ ተስፋ አንድ እናቱ ናቸው። አብሯቸው በኖረበት ዓመታት ስለእሱ አልሆኑለት የለም፡፡ እንዳይራብ፣ እንዳይጠማ በጉልበታቸው አድረዋል፡፡ እንዳያዝን እንዳይከፋ በየቤቱ ሰርተዋል፡፡

የካሳሁን እናት ስለልጃቸው የሰነቁት ተስፋ ብሩህ ነው፡፡ እንደ እኩዮቹ ተምሮ እንዲለወጥ ይሻሉ፡፡ ነገን በተሻለ ዓለም እንዲኖር ምኞታቸው ነው፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ በየሰው ቤት እንጀራ እየጋገሩ፣ የተገኘውን እየሰሩ ያኀርሱታል፡፡

እንጀራ ጋጋሪዋ የካሳሁን እናት ውሎ ሲያድር ሕይወት ከበዳቸው፡፡ ብዙ የሚያስቡለት ልጅ ባክኖ እንዲቀር አልፈለጉም፡፡ ከዛሬ የተሻለ እንዲገጥመው በብዙ ታገሉ፡፡ አሳዳጊ ሆኖ የሚወስደውን፣ አስተምሮ ቁምነገር የሚያደርሰውን ድርጅት ጠያየቁ፡፡ ያሰቡትን አላጡም፡፡ ካሳሁንን ተረክቦ እያኖረ የሚያሳድግ አንድ ‹‹ተራድኦ›› ለምኞታቸው ደረሰ፡፡



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ፤

### ሕይወት በአዲሱ ቤት...

እናትና ልጅ ተለያይተው ሊኖሩ ጊዜው ደረሰ። ካሳሁንን የመካነ እየሱስ አዳሪ ትምህርት ቤት ሙሉ ለሙሉ ተረከበው፡፡ አሁን የእናቱ ተስፋ ለመለመ፡፡ ዘወትር የሚያስቡለት ልጃቸው ጥግ ሲይዝ ውስጣቸው በእፎይታ ፈጣሪን አመሰገነ፡፡

ካሳሁን ከእናቱ ተለይቶ ትምህርቱን በብርታት ቀጠለ፡፡ አንደኛ ደረጃን ጨርሶ ከሁለተኛው ተሻገረ። ይህ ጊዜ የማንነቱን መሰረት የሚጥልበት፣ የወደፊት ሕይወቱን የሚሰራበት ነበር፡፡ እሱ ስንፍናን ሳያውቅ አጥብቆ ተማረ፡፡ ሁሌም እናቱን ሲያስታውስ የነገውን ዓለም ያስባል፡፡ በዚህች ምድር ያሉት ብቸኛ ሐብት እናቱ ናቸው፡፡ ድካም ውለታቸውን መክፈል፣ ሀሳብ ውጥናቸውን ዳር ማድረስ ዕቅዱ ነው፡፡

አስራ ሁለተኛ ክፍልን አጠናቆ ብሔራዊ ፈተና እንደወሰደ ውጤቱን ጠበቀ፡፡ ወጣቱ ተማሪ የድካሙን አላጣም፡፡ ካሳሁን ዩኒቨርሲቲ የሚያስገባውን ውጤት ማግኘቱን አረጋገጠ፡፡ ይህ እውነት ለእሱ ትልቅ ትርጉም ነበረው፡፡ ከፈጣሪ በታች ‹‹አሉኝ›› ለሚላቸው እናቱ ታላቅ ደስታን ያቀብላል፡፡ ለእሱ የወደፊት ሕይወት ብሩህ ተስፋን ይሰንቃል፡፡

ካሳሁን በዓመታት የዩኒቨርሲቲ ቆይታው የፋርማሲ ዘርፍ ትምህርቱን በርትቶ ቀጠለ፡፡ ይህ ጊዜ ለእሱ የማንነቱ ማሳያ፣ የችግር ጊዜው ማምለጫ ነው። ከዚህ ልፋት በኋላ በድህነት ላሳደጉት ምስኪን እናቱ ይደርሳል፡፡ ለራሱ ሕይወት መልካም ዓለም ያልማል፡፡

### «ያሰብኩት ተሳካ - ያለምኩት...

ካሳሁንና የዓመታት ትምህርቱ በእሱ ድል አድራጊነት ተለያዩ፡፡ የልፋት ድካሙን ውጤት ከምርቃት ልብሱ፣ ከክብር መነሳንሱ ባረጋገጠ ጊዜ የሕይወቱን ግማሽ መንገድ እንደጀመረው ተረዳ፡፡ ከዚህ በኋላ ከእሱ የሚጠበቀው የእናቱን ውለታ መመለስ፣ የድካሙን ውጤት ማፈስ ነው፡፡

ከምርቃቱ ማግስት የደረሰው የሥራ ቦታ ካለበት የሚያርቅ፣ ከውድ እናቱ የሚያለያይ ሆነ፡፡ በወቅቱ የጤና ባለሙያዎችን የሚመድበው መንግስት በመሆኑ የተባለውን ከማድረግ ሌላ ምርጫ አላገኘም፡፡ በእጁ የገባው ዕጣ ‹‹ጋምቤላ›› የሚል ጥቅል አቀበለው። ስፍራው ቢርቅም፣ ‹‹ይቅርብኝ›› አላለም፡፡ ጓዙን ሸክፎ፣ እናቱን ተሰናብቶ ወደ ምድብ ቦታው ተጓዘ፡፡

የጋምቤላ አየር ከመሀል አገር ለመጣ እንግዳ ይከብዳል፡፡ አካባቢውን ለመልመድ ጥቂት ቢቸግርም ካሳሁን በማማረር አልተቀበለውም፡፡ በተመደበበት ሆስፒታል የፋርማሲ ሙያውን በብቃት ተወጥቶ ሥራውን አስመሰከረ፡፡ አምስት ዓመታትን በጋምቤላ የቆየው ወጣት ውሎ አድሮ ውስጡ ለለውጥ ተነሳ፡፡ ራሱን መለወጥ ማሻሻል ፈለገ፡፡

ካሳሁን አዲስ አበባ መመለስ በፈለገ ጊዜ ዋንኛ ሀሳቡ ትምህርቱን ማሳደግ ነበር፡፡ ዕቅዱ አልተደናቀፈም፡፡ ሀሳቡ ተቀባይነት አግኝቶ ቀድሞ በተማረበት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመልሶ ገባ፡፡ በተለየ ጥናት የሚማርበት የ‹‹ፋርማኮሎጂ›› ትምህርት ከፍላጎቱ ተጣመረ፡፡ የ‹‹ቶክሲኮሎጂ›› ዘርፍም የፍላጎቱ መሪ ሆነ፡፡

### «ትምህርት እንደገና »

ብርቱው ካሳሁን አሁን ከሚወዳቸው እናቱ ተጠግቷል፡፡ እሳቸው ሊያዩት በናፈቁ፣ እሱም ሊያገኛቸው በወደደ ጊዜ ይገናኛሉ፡፡ ‹‹በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ›› የሆነለት ተማሪ በደስታ ትምህርቱን ቀጠለ፡፡

አሁን ካሳሁን ካሰበው ዓላማ ተገናኝቷል። የጀመረው ትምህርት ሲጠናቀቅ ገና ብዙ ዕቅድ አለው። ለእሱና ለእናቱ የተሻለ ሕይወት የትምህርቱ ለውጥና ስኬት ያግዘዋል፡፡ እናም ሌት ተቀን ያለ እረፍት

**... ወደ ገጽ 17 ዞሯል**

# ኑሮን በፈተና -...

ከ16ኛ ገጽ የዞረ

ይዋትታል፡፡ የመመረቂያ ስራውን ለማጠናቀቅ ይሮጣል፣ ይደክማል፡፡

ካሳሁን በዚህ ሩጫ መሀል ድንገት የሚሰማውን ሕመም አዳምጦታል፡፡ ይህን ስሜት ለይቶ ግን ከትምህርቱ አላስቀደመም፡፡ ቅድሚያውን ለዓላማው ሰጥቶ ቀለሙ ላይ አተኮረ፡፡ ውሎ አድሮ ሕመሙ ይብስ፣ ያስጨንቅ ያዘ፡፡

በግራ ጎኑና እጁ በኩል የሚሰማው ስቃይ ፋታ አልሰጠውም፡፡ ቀስ እያለ ከፈጣን ሩጫው አደናቀፈው። ለመመረቅ ጥቂት ጊዚያት የቀሩት ካሳሁን ከራሱ እየታገለ ጅምሩን ሊጨርስ ታተረ፡፡ አልቻለም። ሳያስበው ጎኑና እጁ ተሸማቀቀ፡፡

ካሳሁን ትምህርቱን ተወት አድርጎ ወደ ሕክምና ቀረበ። እንደታሰበው አልተሳካም። ትምህርቱን ትቶ እንደልጅነቱ ከእናቱ እጅ ወደቀ፡፡ እናት ልጃቸውን ይዘው ወደ ፀበል አመሩ፡፡ በስፍራው ቤት ተከራይተው ያለመታከት በወጉ አስታመሙት፡፡

### የእናት ትከሻ ...

የእናትና ልጅ እግር ካንዱ ወደ አንዱ መንከራተቱን ቀጠለ፡፡ የካሳሁን እናት ልጃቸው አልከበዳቸውም። ዕድሜና ድካም በጎዳው አካላቸው እየደገፉ፣ እየተሸከሙ ከጤናው ሊያገናኙት ሮጡ፡፡ ውስጡ በእጅጉ ተጎድቷልና እንዳሰቡት አልዳነላቸውም፡፡

ትናንት ብዙዎችን የደገፈ የካሳሁን እጅ በሕመም ታሰረ፡፡ ብዙ ዕቅድና ውጥን የሰነቀው ማንነቱ በድንገቴው ሕመም ተደናቀፈ፡፡ ካሳሁን ግራ ገባው፡፡ እንደዋዛ የጀመረው ሕመም አካሉን ገዝቶ፣ ዓይምሮውን እስረኛ ማድረጉ ያልተፈታ ዕንቆቅልሽ ሆነበት፡፡

እናት ልጃቸውን በማስታመም ብዛት ደከሙ፡፡ ሥራ ከጨረሰው ጉልበት የተረፈ ርጋፊ አቅም አልነበረም፡፡ ድካም ከዕድሜ መግፋት ተዳምሮ ለማስታመም፣ በርትቶ ለመጽናት አልበቃ አለ፡፡ እንዲያም ሆኖ ዝም አላሉም፡፡ በገፋ ዕድሜ፣ በደከመ አካላቸው ለልጃቸው ጤና አብዝተው ታገሉ።

ውሎ አድሮ የካሳሁን ጉዳይ ተስፋ አስቆረጠ፡፡ ትናንት ስለራእሱ፣ ተስፋ የጣለው ወጣት ዛሬ በህመም ተሸነፈ። በድህነት ደክመው ላስተማሩት እናቱ ውለታ ሳይመልስ እጁን ሰጠ፡፡ ሕክምናው፣ ጸበሉ፣ በታሰበው ልክ አልተሳካም። አሁንም ካሳሁን ጤና አላገኘም፡፡ እንደቀድሞው በሙሉነት አልተራመደም፡፡

### መልካም ዓይኖች...

እናትና ልጅ ተመልሰው ከችግር ላይ ወደቁ። በመጦሪያ ጊዚያቸው የልጅ አስታማሚ መሆናቸው ብዙዎችን አሳዘነ፡፡ እሳቸው ግን ‹‹ለላም ቀንዷ አይከብዳት›› ሆኖ በውጣውረድ ስለ ልጃቸው ፍቅር አብዝተው ታገሉ፡፡ አቅማቸው አስኪሟጠጥ ቀን ከሌት ደከሙ፡፡ ካሳሁን የእሳቸውን ልፋት ሲያስተውል እጅግ ይሰማዋል፡፡ እናቱን መጦር፣ ማገልገል ሲገባው ሕመም ባደረሰበት ፈተና ከልብ ይተክዛል፡፡

የእናትና ልጅ ፍቅር ዛሬም አልደበዘዘም፡፡ ልጅ በምድር ላይ ያሉት ብቸኛ ሀብትና ወገን እሳቸው ብቻ መሆናቸውን ያውቃል፡፡ ካሳሁን ከእሱ በፊት በገጠር የተወለዱ ሁለት እህትና ወንድም ስለመኖራቸው ሰምቷል። በአካል አለመተዋወቅና አለመግባባታቸው ግን አገናኝቶ አላቀራረባቸውም፡፡

ከቀናት በአንዱ ካሳሁን ራሱን ‹‹የወደቁት አንሱ የነዳያንና በጎ አድራጎት ማህበር›› ውስጥ አገኘው፡፡ ወደዚህ ተቋም ያደረሱት የእሱን አሳዛኝ ታሪክና ሕይወት ውጣውድ የተረዱ ሰዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ መሀል አብረውት የሰሩና የተማሩ ባልንጀሮቹ ይገኙበታል፡፡

ካሳሁን በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ገብቶ መታገዝ ጀመረ፡፡ ልበ ቀናው ወጣት ማንነቱ አልተደበቀም፡፡ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከእሱ የባሱትን ለማገዝ ውስጡ ይፈቅዳል፡፡ ከእናቱ የራቀ ሕይወትን ቢኖርም እሳቸውን ከድካም ማሳረፉ አስደስቶታል፡፡ እሱ እናቱን ሲጠራ ‹‹እመዬ›› ይላቸዋል፡፡ እመዬ እውነተኛውን እናትነት ያሳዩታል፡፡ ባገኙት ቁጥር ፍቅር ይመግቡታል፡፡

### ዘመነ- ኮቪድ ...

ካሳሁን በበጎ አድራጎቱ ማረፊያ ከገባ ጊዚያትን ቆጥሯል፡፡ እናቱ ‹‹እመዬ›› ዘወትር ዕሁድ እሱን ለማየት ከግቢው ደጃፍ ይደርሳሉ፡፡ ዕድሜያቸው ቢገፋም፣ ሕመም ቢጎዳቸውም ስለእሱ የሚሆን ጉልበት አላጡም፡፡ በመጡ ቁጥር የልጃቸውን ራስ እየዳሰሱ ያወጉታል፡፡ እሳቸው ለእሱ የዓይን ርሀቡ ናቸው፡፡ ተስፋውን አሻግሮ ያይባቸዋል፡፡ የመኖር ትርጉሙን ይፈታባቸዋል፡፡

ይህ አይነቱ የእናትና ልጅ ፍቅር ውሎ አድሮ ጋሬጣ አላጣውም፡፡ በዘመኑ በተነሳው የኮሮና ቫይረስ ምክንያት እመዬን ጨምሮ በርካቶች ወደ ግቢው እንዳይገቡ ተከለከሉ፡፡ ይህ በአዋጅ የተደነገገ ውሳኔ ለሁለቱ ነፍሶች ጭንቀትን አቀበለ፡፡ እናት ከግቢው ውጭ ሆነው በናፍቆት ዋተቱ፡፡ ልጅ በአጥር ተከቦ የእናቱን ዓይን ሊያይ አንጋጠጠ፡፡

ይህ ክፉ አጋጣሚ ናፍቆታቸውን አብሶ ለመለያየት ሰበብ ሆነ፡፡ እንዲህ መሆኑ አገር ቤት የሚኖሩትን የእመዬን ልጆች ትኩረት ሳበ፡፡ እናት በዚህ ዕድሜያቸው ለብቻቸው መኖራቸው ተገቢ አልሆነም፡፡ ልጆቹ እናታቸውን እነሱ ዘንድ ለመውሰድ አልዘገዩም፡፡ አጋጣሚው ካሳሁን ከእናቱ እንዲለያይ ምክንያት ሆነ፡፡ ከዚህ በኋላ ‹‹ልጄ›› ሲል የሚጠይቀው፣ እንዴት ነህ ብሎ የሚያየው ሰው የለም፡፡

አሁን ካሳሁን ደጅ ቆመው ‹‹አስገቡኝ›› እያሉ ስለሚማጸኑት እናቱ አያስብም፡፡ ከዚህ በኋላ የዓይን ርሀብ የለውም፡፡ በምድር ያሉት አንዲት እናቱ፣ ውዱና ወዳጁ ከዓይኖቹ ርቀዋል፡፡ ይህ እውነት ዓይምሮን ይይዛል፣ ውስጥን ይረብሻል፡፡ ካሳሁን ግን እናቱን በሀሳብ ሸኝቶ ራሱን አሳምኖ አጽናና፡፡

### በስልክ አነጋግሪኝ..

እናትና ልጅ ከተለያዩ በኋላ ግንኙነቱ በስልክ ብቻ ሆነ፡፡ እናት በናፈቁ ጊዜ ከጎናቸው ያሉ ልጆች ድምጹን ያሰሟቸዋል። ናፋቂዋ እናት የልጃቸውን ቃል ሲያደምጡ ፈጣሪን ያመሰግናሉ፡፡ እሱም ሲያገኛቸው ደስ ይለዋል። ጥቂት ቆይቶ ግን የቀጭኑ ሽቦ አንደበት ተቋረጠ፡፡ እናት የልጃቸውን ድምጽ በሰሙ ቁጥር ትካዜ ማብዛታቸው ግንኙነቱን ገደበ፡፡ የእናትና ልጅ ፍቅር በትዝታ ታጅቦ ዓመታትን አሳለፈ፡፡

የኮቪዱ ወጀብ አልፎ ሌላ ቀን በነጋ ጊዜ የካሳሁን እናት ወደነበሩበት አልተመለሱም፡፡ እርጅናው ከጤና እጦት ተዳምሮ ካሉበት ሊቀሩ ግድ ሆነ፡፡ ካሳሁን ስልክ ደውሎ በጠየቀ ጊዜ ስለእሳቸው ደህንነት ይነገረዋል። ሄዶ አለማየቱ፣ አግኝቶ አለማዋየቱ ቢያሳዝነውም በመኖራቸው ብቻ ይጽናናል፡፡

### የማለዳው እንግዶች...

ካሳሁን ባረፈበት የወደቁትን አንሱ የበጎ አድራጎት ተቋም የራሱ አልጋ አለው፡፡ ስፍራው ደህንነቱ የተጠበቀና ንጽህናው ያማረ ነው፡፡ በዙሪያው እሱን መሰል ጊዜና ቀን የጣላቸው ወገኖች ዓመታትን አብረውት ዘልቀዋል፡፡ ሁሉም በተለያየ ሕመምና ችግር ውስጥ ናቸው፡፡

አንድ ማለዳ ከዕንቅልፉ ሲነቃ የሰዎች አትኩሮት ሳበው።ጥቂት ሰዎች ወደ እሱ እየቀረቡ ነበር፡፡ የእነሱ መምጣት አዲስ ባይሆንም ሁኔታቸው አስደንግጦታል። የማለዳው እንግዶች መልካም ነገር አልያዙም፡፡ ዝግ ባለ አንደበታቸው የእናቱን ማረፍ አረዱት፡፡ የእናት ሞት ውስጥን የሚሰነጥቅ፣ ማንነትን የሚያርድ ስብራት፡፡ ቀን የሚያጨልም፣ ብርሀን የሚነጥቅ ሀያል ስሜት፡፡

ካሳሁን በችግር በድህነት ያሳደጉትን፣ በስቃይ እንክርት ያስተማሩትን የውድ እናቱን ሞት ተረዳ፡፡ በሕመሙ ጊዜ ብቸኛ ትከሻው፣ በችግሩ ሰዓት አንድዬ መከታ የሆኑት ‹‹ዕመዬ›› ከእንግዲህ የሉም፡፡ አሁን ‹‹አለኝ›› ብሎ የሚጠራው ‹‹የት ነህ ?›› ብሎ የሚፈልገው የለም፡፡ ለራሱ እውነታውን አሳምኖ ሀቁን ተቀበለ፡፡ እርሙን አወጣ፡፡

ካሳሁንን ሳገኘው የእናቱን ሞት ከሰማ ከቀናት በኋላ ነበር፡፡ በርትቷል፡፡ ራሱን አጽናንቶ ጠንክሯል፡፡ ጉብዝናውን አደነቅሁለት፡፡ በፊቱ ያስተዋልኩት ቀናነት ማንነቱን አይደብቅም፡፡ ውስጤ የተሻለ ነገን እያሳየ በብርታት እንደሚያሻግረው ሹክ አለኝ፡፡

ካሳሁን ‹‹እግዚአብሔር ሁሌም ትክክል ነው›› የሚል አቋም አለው፡፡ ይህ እውነት መሽቶ በነጋ ቁጥር ከአዲስ የብርታት ቀን ጋር ያገናኘዋል፡፡ እንደዋዛ የጀመረው ሕመም ዛሬም ግማሽ አካሉን ይዞ እንዳሻው ላይሆን ገድቦታል። እስካሁን በሕክምናው የሞከረው ሂደት ባይሳካም እሱ ግን ተስፋ አይቆርጥም፡፡

ዘወትር ከሚዲያው ሳይርቅ የዓለምን ውሎ አዳር ይከታተላል፡፡ በቻለው አቅም ሌሎችን ለማገዝ የፈጠነ ነው። ትናንት ስለነበረበት ዓለም እያሰበ አይጨነቅም። የባልንጀሮቹ ዕድገት፣ የእኩዮቹ መለወጥ አሳስቦት አያውቅም፡፡ ሁሌም የበታቾቹን እያየ ፈጣሪውን ያመሰግናል፡፡ የእሱ ዓለም አሁን ያለበት ቦታና ከጎኑ ያሉት ሰዎች ናቸው፡፡

ከአምስት ዓመታት በላይ ለቆየበት ‹‹የወደቁትን አንሱ›› የበጎ አድራጎት ድርጅት የተለየ ክብርና ምስጋና አለው። እሱ ነገ የተሻለ እንደሚሆን ያምናል፡፡ ትናንት ብዙሀንን ያገለግል የነበረ ባለሙያ እጁ ዛሬ ቢሰበሰብም ስለነገው ተስፋ አይቆርጥም፡፡

ይህ ሰው ሁሌም ስለሀገር ፍቅርና ሰላም ዕንቅልፍ የለውም። ወደ ፈጣሪው አጥብቆ ይጸልያል፡፡ እሱ ባለው አቅም የደከሙትን ለማገዝ ሁሌም በቂ መሆኑን ያውቃል። ኑሮን ተቀብሎ፣ ሕይወትን እንዲህ እየኖረ ነው፡፡ ትሁቱ፣ ልበ ቀናው ካሳሁን ቤዛ፡፡

## ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአሥራ አምስት ቀኑ ቅዳሜ የሚታተም

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

# ሀገር ዓቀፍ የማሕጸን በር ካንሰር ክትባት ዘመቻ

የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጤና ሚኒስቴር በሽታን የመከላከል እና የመቆጣጠር ተልዕኮ አንግቦ አምራችና ጤናማ ማህበረሰብ የመገንባት ሚናውን እየተወጣ ይገኛል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይህንን ተልዕኮውን የሚያሳካው በሥሩ ባቀፋቸው የተለያዩ የሥራ መምሪያዎች ነው፡፡ ከነዚህም የእናቶችና ሕጻናት ዳይሬክቶሬት አንዱ ነው፡፡ ይህ ዘርፍ አራት ቡድኖችን ይዟል ፤ እነርሱም፡- የእናቶች ቡድን፣ የሕጻናት ቡድን ፣ የወጣቶችና የአፍላ ወጣቶች ቡድን እና የክትባት ቡድን ናቸው፡፡

እንደጤና ሚኒስቴር ንዑስ የሥራ ክፍል የክትባት ቡድን በአብዛኛው በሽታን የመለካከል ሥራዎችን የሚሠራ ሲሆን እንደ ኩፍኝ ፣ ኮቪድ 19፣ የማሕጸን በር ካንሰርን የመሳሳሉትን አካትቶ ከ13 በላይ ክትባቶች በዚህ ዘርፍ ይሠጣሉ። በዛሬው ጹፋችን በጤና ሚኒስቴር የእናቶችና ሕጻናት ዳይሬክቶሬት የክትባት ክፍል አማካሪ አቶ መንግሥቱ ቦጋለ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ ስለመጣው የማሕጸን በር ካንሰር ስለ ምልክቶቹ ፣ በሽታውን ለመከላከል ስለሚሰጠው ክትባት እንዲሁም ከሁለት ወር በኋላ ሊሰጥ ስለታሰበው ሀገር ዓቀፈ ክትባት የሰጡንን መረጃ እንደሚከተው አጠናቅረን አቅርበንላችኋል፡፡

እንደ አቶ መንግሥቱ ገለጻ የማህጸን በር ካንሰር ከጡት ካንሰር ቀጥሎ በገዳይነቱ የሚታወቅ እየሆነ መጥቷል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የሚኖሩ ማህበረሰቦች ስለበሽታው የሚኖራቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑና መከላከያውን በቀላሉ ማግኘት የማይችሉ መሆኑን ተከትሎ የበሽታው ጫና ይበረታባቸዋል፡፡

ለምሳሌ በዓለም የካንሰር ድርጅት መረጃ መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ በማሕጸን በር ካንሰር በየዓመቱ ቢያንስ ወደ 7ሺህ አራት መቶ የሚሆኑ



**አቶ መንግሥቱ ቦጋለ፣**

ሴቶች ይያዛሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በየዓመቱ ከ5 ሺህ ሶስት መቶ በላይ የሚሆኑት እናቶች ሕይወታቸው ያልፋል፡፡ አቶ መንግሥቱ የማሕጸን በር ካንሰር በሽታ በገዳይነቱ ከኮቪድም ይበልጣል ይላሉ፡፡ ለምሳሌ እንደ ሀገር በኮቪድ ወረርሽኝ አጠቃላይ በሶስት ዓመት ውስጥ ሕይወታቸው ያለፉ ሰዎች ብዛት ወደ 7 ሺህ ገደማ ይገመታል፡፡ የማሕጸን በር ካንሰር በኢትዮጵያ በዓመት ከአምስት ሺህ በላይ ለሚሆኑ እናቶች ሞት ምክንያት ከሆነ በሶስት ዓመት ውስጥ 15 ሺህ ሰዎችን ይገድላል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም በሽታው ከኮቪድም በላይ ጫና ፈጣሪ መሆኑን በዚህ መረዳት ይቻላል ይላሉ አቶ መንግሥቱ፡፡

በሽታው የሚተላለፈው ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር በተያያዘ HPV (Human papilloma Virus) በሚባል ረቂቅ ሕዋስ ነው፡፡ በሽታው ሲጀምር ምልክት አያሳይም፤ እንደሌሎች የአባለዘር በሽታዎች ፈሳሽ ወይም ቁስለት የለውም፡፡ ይህ ባሕሪው ደግሞ ሳይታወቅ ስር እንዲሰድ ያደርገዋል፡፡

የማሕጸን በር ካንሰርን መከላከል ከሚያስችሉት ጉዳዮች የመጀመሪያው ክትባት ነው፡፡ ክትባቱ ከ90 በመቶ በላይ መከላከል የሚያስችል ነው፡፡ የክትባት ጊዜ ያለፈባቸውና እድሜያቸው ከ30 እስከ 49 የሚደርስ እናቶች የቅድመ ማሕጸን በር ካንሰር ምርመራ ማድርግ ሲችሉና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሱ ልጆች የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዳያደርጉ ማስተማር ሲቻል በሽታውን መከላከል ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ከ1ሺህ የሚበልጡ ጤና ጣቢያዎች የቅድመ ማሕጸን በር ካንሰር ምርመራ አገልግሎት በነጻ እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ የጤና ተቋማቱ አንድን ሰው ለመመርመር የሚፈጅባቸው ጊዜ ከአምስት ደቂቃ የማይበልጥ በመሆኑ ለምርመራ የሚሄዱ ሰዎች የሚያባክኑት ሰዓት አይኖርም፡፡

በኢትዮጵያ የማሕጸን በር ካንሰር ክትባት የተጀመረው በ2011 ዓ.ም ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ክትባቱ የሚሰጥበት መንገድ አሁን ከሚሰጥበት መንገድ ይለያል፡፡ አንድ ጊዜ ክትባት የወደሰ ሰው ከስድስት ወር በኋላ ወይም በዓመት ሁለተኛ ዙር ክትባት እንዲወስድ ይደረግ ነበር፡፡ አሁን ሳይንሱ ባስተዋወቀን አዲስ ግኝት ደግሞ በሽታውን በአንድ ጊዜ ክትባት መከላከል የሚቻል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አዲሱ ክትባት 176 በሚሆኑ የዓለም አገራት እየተሰጠ እንዳለ የተናገሩት አቶ መንግሥቱ ከአፍሪካም እንደ ናይጀሪያን የመሳሰሉ ሀገራት ክትባቱን ለሕብረተሰባቸው ከመስጠት አንጻር ቀዳሚቹ ናቸው፡፡

በሀገራችንም ከጥር ወር አጋማሽ ጀምሮ አዲሱን የማሕጸን በር ካንሰር ክትባት ለመስጠት ዝግጅት እየተጠናቀቀ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በዚህ የክትባት መርሃ-ግብር እድሜያቸው ከ9 እስከ 14 የሚሆኑ ሴት ልጆች ከትባቱን እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከስምንት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን በላይ ሴቶችን ለመከተብ መታቀዱን ተናግረዋል፡፡ ይህንን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግም በጤና ሚኒስቴር ደረጃ ሁሉም ዝግጅት እንደተጠናቀቀ ገልጸዋል፡፡

ክትባቱ በዋናነት በትምህርት ቤት ደረጃ የሚሰጥ እንደሆነ የገለጹት አቶ መንግሥቱ ከትምህርት ገበታ ውጭ ያሉትን ደግሞ በደርሶ መልስ በክትባት ጣቢያዎች እና በመደበኛነት በየጤና ድርጅቶቹ ክትባቱን እንዲያገኙ ይደረጋል ብለዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓትም በርካታ እናቶችና ታዳጊ ሴቶች በማሕጸን በር መሽታ እየተሰቃዩ መሆኑን የተናገሩት አቶ መንግሥቱ እናቶች የህመም ምልክት ከማየታቸው በፊት በአካባቢያቸው ወደሚገኙ የጤና ተቋማት በመሄድ ቅድመ የማሕጸን በር ምርመራ ማድርግ እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡ ፡ በሽታው እያደር ወደ ካንስር የመቀየር ባህሪ ስላለው አስቀድሞ የጤና ክትትል በማደረግ እራሳቸውን እንዲጠብቁ መክረዋል፡፡

ወላጆች እድሜቸው ከ9 እስከ 14 የሆናቸውን ሴት ልጆች በማስከተብ የወደፊቱ አገር ተረካቢ ትውልድን የመታደግ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ የክትባቱ አስተባባሪ አቶ መንግሥቱ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

# ማህደረ ጤና

## በምርምር ያልተደገፈው ባሕላዊ መድኃኒት

ሰስናቀ ፀጋዬ

"የባሕላዊ ሕክምና" ሀገር በቀል የሆነና በልምድ የዳበረ እንዲሁም በሕብረተሰቡ ተቀባይነት ያገኘ ዕውቀት ሆኖ የእጽዋትንና የእንስሳትን ተዋጽኦ ወይም ማዕድናትንና የእጅ ጥበብን በመጠቀም የሚሰጥ የሕክምና አገልግሎት እንደሆነ ይነገራል። በኢትዮጵያ የባሕል ሕክምና ከጥንት ጀምሮ የነበረና ዘመናዊ ሕክምና ወደሀገሪቱ ከመግባቱ በፊት ሕዝቡ በስፋት ሲገለገልበት የቆየ ነው፡፡ ዘመናዊ ሕክምና በኢትዮጵያ ከተስፋፋም በኋላ ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው የማሕበረሰብ ክፍል የዚሁ የባሕል ሕክምና ተጠቃሚ መሆኑን ጥናቶች ያረጋግጣሉ፡፡

ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ የባሕል ሕክምና ሙያ ያላቸው አዋቂዎች በተናጠልና በተበታተነ ሁኔታ አገልግሎቱን ለሕብረተሰቡ ሲሰጡ ቆይተዋል። ሕብረተሰቡም ከዘመናዊው ሕክምና ባልተናነሰ መልኩ የዚሁ ባሕላዊ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚ ነበር፡፡ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በተለይ የአዲስ አበባ የባሕል ሕክምና አዋቂዎች ማሕበር ተበታትነው እየሰሩ ያሉ በርካታ የባሕል ሕክምና ባለሙያዎችን በማሰባሰብና የማሕበሩ አባል እንዲሆኑ በማድረግ ከሚመለከተው አካል ፍቃድ አግኝተው ለሕብረተሰቡ የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ እየሰራ ይገኛል፡፡


በዚሁ መነሻነት ማሕበሩ የባሕላዊ መድኃኒት አገልግሎት ለመስጠት ያልተመዘገቡ አገልግሎት ሰጪዎች ካሉ እንዲመዘገቡና ሕጋዊ ሆነው እንዲሰሩ እያበረታታና ክትትል እያደረገ ይገኛል። የባሕል ሕክምና አገልግሎት በሚሰጡ እና ጉዳዩን በሚከታተለው በባለስልጣን መስሪያ ቤት መካከል ሆኖ በቅርበት ይሰራል፡፡ በባሕል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ስለሚከናወኑ የተለያዩ ተግባራት እቅድ ያወጣል፤ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል፤ ብሎም ከባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጋር የተለያዩ የመግባቢያ ሰነዶችን ይፈራረማል፡፡

በተጨማሪም በባሕላዊ መድኃኒት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ጉዳዩ ለሚመለከተው ባለስልጣን መስሪያ ቤት የተለያዩ የአሰራር አቅጣጫዎችና ሃሳቦች ያቀርባል፡፡ አባላቱ ጥራት ያለው የባሕል ሕክምና አገልግሎት እንዲሰጡ የራሱን ሕገ-ደንብ አውጥቶ ይንቀሳቀሳል፡፡ ከሰሞኑም ማሕበሩ አራተኛ ዓመት የምስረታ በአሉንና ጉባኤውን በአዲስ አበባ ከልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላትና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን አካሂዷል፡፡ በአሁኑ ግዜም 105 ዓባላትን ይዞ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

በዚሁ ጉባኤ ወቅት ማሕበሩ እያጋጠሙት ያሉትን ተግዳሮቶች የዘረዘረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ስለ ባሕል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥና ሙያ የተሳሳተ ግንዛቤ በስፋት መኖር፣ በሚፈለገው ደረጃ በሕብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ የመፍጠር ችግር፣ እንደ ሀገር ጠንካራ የሆነ የባሕል ሕክምና ማሕበር ያለመሆን፣ ህገ ወጥ የባሕል ሕክምና ባለሙያ መሰሎች መበራከት እና ሙያውን የማይመጥኑ የተሳሳቱ ቅስቀሳዎች መብዛት ዋና ዋናዎቹ መሆኑን ጠቅሷል፡፡

መጋቢ ጥበብ መርጌታ መንግስቱ ደስታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የባሕል ሕክምና አዋቂዎች ማሕበር ፕሬዚዳንት ናቸው፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት የባሕል ሕክምና አዋቂዎች መድሃኒት የሚያዘጋጁባቸው ከእፅዋቶች በመጥፋት ላይ የሚገኙ ከመሆናቸው አንፃር እፅዋቶቹን በአንድ ቦታ ላይ በማሰባሰብ፣ በማራባት፣ በማሳደግና በመንከባከብ ለሕክምና እንዲውሉ ለማድረግ ማሕበሩ ለሚመለከተው የመንግስት አካል ጥያቄ አቅርቧል፡፡

በዚህ ረገድ መንግስታዊም ሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ማሕበሩን በልዩ ልዩ መልኩ እንዲደግፉ ይበረታታሉ፡፡ የባሕል ሕክምናውም


መርጌታ መንግስቱ ደስታ፤

ከአጉል እምነትና ባሕል ተለይቶና ይበልጥ ታውቆ ከእፀዋት፣ እንስሳትና ማእድናት ተዘጋጅቶ በስፋት ለታካሚዎች ተደራሽ እንዲሆን ይሰራል፡፡ የባሕል ሕክምና ጥንትም የነበረና ወደፊትም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገር ስለመሆኑም የማሳወቅና ከአጉል እምነት ተለይቶ እንዲታይ የማድረግ ስራ ማሕበሩ እየሰራ ይገኛል፡፡ ከዚህ አንፃር ሕብረተሰቡም የባሕል ሕክምና ከአጉል እምነት ጋር የተሳሰረ እንዳልሆነ በመረዳት የተሻሉና ከኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ሕጋዊ ፍቃድ ያገኙ አዋቂዎችን በማግኘት ተገቢውን ባሕላዊ ሕክምና ማግኘት ይችላል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ሌሎችም የባሕል ሕክምና አዋቂዎች ሕጋዊ ሆነውና በዚሁ የመንግስት አካል ተመዝግበው ሙያቸውን በማሻሻል ተገቢውን የባሕላዊ ሕክምና አገልግሎት ለሕብረተሰቡ መስጠት ይችላሉ፡፡

ፕሬዚዳንቱ እንደሚናገሩት፣ ማሕበሩ በአሁኑ ግዜ እጩ አባላትን ጨምሮ 105 አባላት አሉት። ሕጋዊ ያልሆኑ የባሕል ሕክምና አዋቂዎችም በአዲስ አበባ የባሕል ሕክምና አዋቂዎች ማሕበር ተመዝግበውና ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው በምግብና መድሃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ባወጣው መመሪያና ሕግ መሰረት ስራቸውን እንዲሰሩና የበለጠ እውቅና እንዲገኝ ብሎም በሕገ ወጥ መልኩ በባሕል ሕክምና ስም ከሚሰሩ አካላት እንዲለዩ የማድረግ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

እስካሁን ባለው ሂደት የአንድ የባሕላዊ ሕክምና አዋቂ ችሎታ የሚመሰከረው በታካሚዎች ነው። ይሁንና አሁን ባለው ሁኔታ አንድ የባሕል ሕክምና ባለሙያ አንድ ቦታ ላይ ሶስት ዓመት ከኖረ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪነት መታወቂያ ካለው፣ በሕብረተሰቡ እውቅና ካለው ወይም ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ የባሕል ሕክምና አዋቂዎች ማሕበር የባሕል ሕክምና አዋቂ መሆኑን ካረጋገጠ፣ ከየት እንደተማረ፣ ምን እንደሚያውቅ ምን አይነት እፅዋት እንደሚችል በዝርዝር ካወቀ በኋላ ማሕበሩ በደብዳቤ ወደ አዲስ አበባ ምግብና መድሃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ይልከዋል፡፡

በመቀጠል አዲስ አበባ ምግብና መድሃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በመመሪያውና በሕጉ መሰረት ሕጋዊ የምዝገባ ሰርተፍኬት ይሰጠዋል፡፡ የባሕል ሀኪሙ ይህንኑ ሰርተፊኬት ይዞ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ማሕበሩ በስሩ ያሉ የባሕል ሕክምና አዋቂዎች የሚያዘጋጇቸው መድሃኒቶች በሳይንሳዊ መንገድ እንዲመረመሩ ለማድረግ ፍቃደኛ ነው። በቀጣይም የማሕበሩ ፍላጎት መድሃኒቱን በማስመርመርና በተገቢው የሳይንሳዊ ፍተሻ ሂደት አልፎ ጥቅም ላይ እንዲውል ነው፡፡ መንግስት የሚፈለገውን ሁኔታ ካመቻቸና በተለይ ደግሞ ለባሕላዊ ሕክምና የሚውሉ እፅዋት እየጠፉ ስለሆነ እነርሱን ለማቆየት የሚያስችል ቦታ ቢፈቅድና በእፅዋቶቹ ላይ ምርምር አድርጎ ጎጂነታቸውንና ጥቅማቸውን ካረጋገጠ ለሕብረተሰቡ የሕክምና ጠቀሜታ እንዲውሉ ማሕበሩ ይፈልጋል፤ ለዚህም የራሱን ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡


አቶ ሃብታሙ በየነ፤

በሌላ በኩል እንደ አዲስ አበባ ከተማ ማሕበሩ ሕጋዊ ሆነውና ፍቃድ አውጥተው የሚሰሩትንና ሕጋዊ ሳይሆኑ የሚሰሩትን የባሕል ሕክምና አዋቂዊችን ለይቷል፡፡ ይህ በመሆኑም ከሚመከተው አካል ጋር በመነጋገር ወደማሕበሩ እየመጡ ሕጋዊ ሆነው ቁጥጥርና ክትትሉን የሚመለከታቸው አካላት እያደረገላቸው ስራውን እንዲሰሩ እየተደረገ ነው፡፡ ማሕበሩን የሚወክሉና በክፍለከተማው የሚገኙ ባለሞያዎች በሚያመጡት መረጃ መሰረት ሕጋዊ ፍቃድ ይዘው ወደ ማሕበሩ እንዲመጡ፤ ሕብረተሰቡም ሕጋዊ በሆኑ የባሕል ሕክምና አዋቂዎች እንዲታከም ማሕበሩ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡

ከባሕል ሕክምና ጋር በተያያዘ ሕብረተሰቡ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው ማሕበሩ በዚህም ዘርፍ ያሉ ምሁራንንና የጤና ባለሞያዎችን በማምጣትና የውይይት መድረኮችን በመፍጠር ብሎም ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ሕብረተሰቡ እንዲረዳ የማድረግ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን የመድሃኒት ምዝገባና ፍቃድ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሃብታሙ በየነ እንደሚናገሩት፣ ባልስልጣኑ ባሕላዊም ሆኑ ዘመናዊ መድሃኒቶች ተመዝግበው ገበያ ላይ እንዲውሉ ይቆጣጠራል፡፡ መድሃኒቶቹ ገበያ ላይ ከዋሉም በኋላ በተጠቃሚው ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ፤ መድሃኒቱን የሚያዙ ባለሙያዎችም መድሃኒቶቹን በትክክል አውቀው እንዲሰሩ ክትትል ያደርጋል፡፡

በዚህ ሂደት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በተለይ በባሕላዊ ሕክምና ላይ የተሰማሩ ሰዎች መድሃኒታቸው ተመዝግቦ ወደ ሕጋዊ ስርዓት ገብተው እንዲሰሩ በሩን ክፍት አድርጎ እየጠበቀ ነው፡፡ አሁን ባለው ሁኔታም በኢትዮጵያ ባሕላዊ መድሃኒት በምርምር ታግዞና ተመዝግቦ ወደ ገበያ የሚወጣበት ሁኔታ የለም፡፡ ይህ እንዲሆን ግን ከምርምር ተቋማት ጋር በመገናኘት ባሕላዊ መድሃኒቶቹ ጉዳት እንደማያመጡ፣ ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ እንዲሆን ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከባሕላዊ ሕክምና አዋቂዎችና በዚህ ዘርፍ ምርምር ከሚያደርጉ ተቋማት ጋር እየተነጋገረ ይገኛል። ለዚህም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን፣ ደምቦችን፣ ሕጎችንና ፖሊሲዎችን እያረቀቀ ነው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ያሉት ባሕላዊ መድሃኒቶችና የባሕል ሕክምና አዋቂዎች በምርምር ታግዘው መድሃኒቶቻቸው ለተቃሚዎች እንዲደርሱ በማድረግ ሂደት ፍጥነት ባለመኖሮ ቻይናና ሕንድን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት ምርቶቻቸው እንዲመዘገቡላቸው ጥያቄዎችን ያቀርባሉ፡፡ ይሁንና ሀገር በቀል መድሃኒቶች እንዳይቀጭጩና እንዳይጠፉ ለማድረግ የውጪዎቹን በመጥተው ለነዚህ ቅድሚያ ተሰጥቶ እየተጠበቀ ነው፡፡ አሁንም የምርም ተቋማትና የባሕላዊ ሕክምና አዋቂዎች ተገናኝተው ቢሰሩና ወደ ውጤት ቢመጡ መልካም ነው፡፡

በተለይ ደግሞ በባሕላዊ ሕክምና አዋቂው በኩልና በተመራማሪው በኩል የሚኖረውና ‹‹መድሃኒቱ የኔ ነው›› የሚለው ስጋት የአእምሮ ንብረት ባለቤትነት እውቅና ማግኘት ከቻለና በዚህ ላይ ከተሰራ በሃገር ውስጥ ያለውን ትልቅ የባሕል ሕክምና አቅም መጠቀም ይቻላል፡፡ በትክክለኛው ሂደት የባሕል መድሃኒቶች ገበያ ላይ እንዲውሉ የማድረግ ስራው ገና ቢሆንም ሂደቶች ግን አሉ፡፡

ዳይሬክተሩ እንደሚሉት፣ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የባሕላዊ መድሃኒቶች ወደ ገበያ ወጥተው ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት ጥራታቸውን፣ ፈዋሽነታቸውንና ደህንነታቸውን ያረጋግጣል፤ ፍቃድ ይሰጣል፡፡ ለዚህም ነው ፍላጎት አሳይቶ የባሕላዊ መድሃኒቶች አዋቂዎች ወደተቋሙ መጥተው የመድሃኒታቸውን ጥራት፣ ፈዋሽነትና ደህንት እንዲያረጋግጡ እየተጠባበቀ የሚገኘው። ይህን ለማድረግ በባሕላዊ መድሃኒት አዋቂውና በተመራማሪዎች በኩል ያሉ ፍላጎቶች ናቸው የሚጠበቁት፡፡


በተለያዩ የማሕበራዊ ሚዲያዎች የሚተዋወቁ የባሕላዊ መድሃኒቶችና ሕክምና ሕጋዊ እውቅና ያላቸው አይደሉም፡፡ ለዛም የኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ሕብረተሰቡ ይህን አውቆ ራሱን እንዲጠብቅ የባሕላዊ መድሃኒቶች ጥራት፣ ፈዋሽነትና ደህንነት አረጋግጦ ሕጋዊ ፍቃድ የሚሰጠው፡፡ በርግጥ በኢትዮጵያ ባሕላዊ መድሃኒቶች በሳይንሳዊ መንገድ ታይተውና ተፈትሸው ብሎም በፋብሪካ ደረጃ ተመርተው ገበያ ላይ የዋሉ የሉም፡፡ ባስልጣን መስሪያ ቤቱም የሚሰራው የባሕላዊ ሕክምና አዋቂዎች መድሃኒት ሲያዘጋጁ በምን ያህል ደረጃ እንደቀመሙ ለማየትና የመድሃኒቶቹን ፈዋሽነትና ደህንነት ማረጋገጥ ነው።

ስለዚህ የባሕል ሕክምና አዋቂዎች መድሃኒቶቻቸውን ወደ ገበያ ከማውጣታቸው በፊት ወደ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ መጥተው የመድሃኒታቸውን ጥራት፣ ደህንነትና ፈዋሽነት ማረጋገጥና ሕጋዊ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለባቸው፡፡ የሕክምናው ቦታውና መድሃኒቱ የሚዘጋጅበት ሁኔታም በደምብ መታወቅ አለበት፡፡ ይህም የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታም አብዛኛዎቹ የባሕል መድሃኒቶች የመጀመሪያው የአመራረት ሂደት ደረጃ ላይ ነው ያሉት፡፡ እነዚህም ማድረቅና መበጥበጥ ናቸው፡፡

ይሁንና በሶስተኛ የአመራረት ሂደት ደረጃ ማለትም ባሕላዊ መድሃኒቶቹ በእንክብልና በፈሳሽ መልክ ሲቀርቡ ብዙ መታየት ያለባቸው ነገሮች አሉ፡፡ ምርምር ሊደረግባቸውም ይገባል፡፡ ስለዚህ ይህ እንዲጎለብት ነው ስራዎች እየተሰሩ የሚገኙት። ከዚህ አኳያ ምርምር ተቋማትም በራቸውን በዚህ መልኩ ክፍት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

እስካሁን ድረስ ባለው ሁኔታ በባሕላዊ መድሃኒቶች ላይ ምርምር ሲያደርግ የቆየው የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ነው፡፡ አሁን ግን ስራው ወደ አርማወር ሃንሰን ኢንስቲትዩት ዞሮ በአንድ እንዲጠቃለል ተደርጓል። በዚህም የምርምር ስራው በተሻለ ሁኔታ እየታየ ነው፡፡ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ጥናቶች ሳይተገበሩ የሼልፍ ማሞቂያ ሆነዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህን ጥናቶች ወደ ተግባር መለወጥና በኢትዮጵያ ያለውን እምቅ የባሕላዊ መድሃኒት አቅም በስፋት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

# ስፖርት



# «ለኦሊምፒክ ስፖርቶች ትኩረት ሊሰጥ ይገባል»

**- ኮማንደር ፀጋሥላሴ አረጋይ**

ዓለማየሁ ግዛው

በየአራት ዓመቱ የዓለም ሀገራትን በአንድ ጣሪያ ስር አሰባስቦ በስፖርቱ መድረክ የሚያፎካክረው ታላቁ ኦሊምፒክ ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ታላቅ የስፖርት ድግስ ውጤታማ ለመሆን ሀገራት ብዙ ይለፋሉ። በሜዳሊያ ሰንጠረዥ ቀዳሚ ሆነው ለማጠናቀቅም በብዙ የስፖርት ዓይነቶች ላይ ትኩረት አድርገው ይዘጋጃሉ፡፡ ውጤታማ በሚያደርጋቸው የስፖርት ዓይነቶች ላይ ዝግጅት የሚያደርጉትም ኦሊምፒክ ሲቃረብ ብቻ አይደለም፡፡ ለሁሉም የስፖርት ዓይነቶች እኩል ትኩረት በመስጠት ዘወትር ይሠራሉ፡፡ በኦሊምፒክ በርካታ ሜዳሊያዎችን የሚያፍሱ ሀገራት ምስጢር ይሄው ነው፡፡



ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ መድረክ በመሳተፍ ታሪካዊ የሆኑ ገድሎችን መጻፍ ከቻሉ አገራት መካከል ትጠቀሳለች። ስኬቶች ሁሉ የተመዘገቡት ግን በአንድ የአትሌቲክስ ስፖርት ያውም በረጅም ርቀት ውድድሮች ውጤት ላይ ብቻ ተንጠልጥለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ ተሳትፎዋ ከአትሌቲክስ ባሻገር የብስክሌትና የቦክስ ስፖርቶች በውጤት ባይታጀቡም ታሪክ አላቸው፡፡ ካለፈው የቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ ጀምሮም የወርልድ ቴኳንዶ ስፖርት ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ ተሳትፎዋ አዲስ ምዕራፍ ከፍታለች፡፡

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ለሁሉም ስፖርቶች እኩል ትኩረት ሰጥታ መሥራት ከቻለም በበርካታ የስፖርት አይነቶች ኦሊምፒክ ላይ መሳተፍ የሚያስችል አቅም እንዳላት ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ የቀድሞ ቦክሰኛና የአሁኑ የማረሚያ ቤቶች ቦክስ ስፖርት ክለብ ቡድን መሪ ኮማንደር ፀጋሥላሴ አረጋይ ለሁሉም የኦሊምፒክ ስፖርቶች የሚሰጠው ትኩረት እኩል እንዳልሆነ ይናገራሉ፡፡

ኮማንደር ፀጋሥላሴ እንደሚያስረዱት፣ ኢትዮጵያ የእግር ኳስ ስፖርትን ቀድመው ከተዋወቁ ሀገራት አንዷ ብትሆንም ከአንድ የአፍሪካ ዋንጫና የሴካፋ ውድድር በቀር ያሳካችው ድል የለም፡፡ በዓለም ዋንጫም መሳተፍ ተስኗት ትገኛለች።በታሪኳ በዓለም ዋንጫ መሳተፍ የቻለችውም በወጣቶች መድረክ አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለእግር ኳሱ የሚደረገው ድጋፍና የሚመዘገበው ውጤት የተገላቢጦሽ ነው፡፡ በአንጻሩ ኢትዮጵያ ከአትሌቲክስ እየተሰጠ ያለው ትኩረትና ድጋፍ አነስተኛ ነው፡፡ ይህም ያለውን አቅም መጠቀም እንዳይቻል አድርጓል፡፡

ኢትዮጵያ በኦሊምፒክ መድረክ በአትሌቲክስ፣ ብስክሌት እና ቦክስ ለብዙ ጊዜ በመሳተፍ ትታወቃለች። በአትሌቲክሱ ከፈር ቀዳጁ አትሌት አበበ ቢቂላ ጀምሮ በርካታ ሜዳሊያዎችንና ክብረወሰኖችን በእጁ ማስገባቱን ቀጥላበታለች፡፡ ይሁን እንጂ ለአትሌቲክስም የሚደረገው ድጋፍ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ የስፖርት ክለቦችም ውጤት ለሚያመጡ ስፖርቶችና ውጤት ለሌላቸው የሚሰጡት ትኩረትና የሚመድቡት በጀት እጅጉን የተለያየ ነው፡፡ ለቦክስና ብስክሌት ስፖርትም የሚሰጡት ትኩረት ከአትሌቲክሱ የተለየ እንዳልሆነ ኮማንደር ፀጋሥላሴ ያብራራሉ፡፡

ኢትዮጵያን በኦሊምፒክ ከወከሉት ስፖርቶች አንዱ በሆነው የቦክስ ስፖርት በኦሊምፒክ መሳተፍ የቻሉት ኮማንደር ፀጋሥላሴ፣ የኦሊምፒክ ስፖርቶች ትኩረት ተሰጥቷቸው ተገቢው ሥራ ሊከናወን ይገባል ይላሉ፡፡ የሀገር ባለውለታ ክለቦች ለእግር ኳስ በብዙ ሚሊየን ብሮች ሲያፈሱ ለቦክስ፣ አትሌቲክስና ብስክሌት የሚያወጡት እጅግን አናሳ እንደሆነም በማሳያነት ያስቀምጣሉ፡፡ ይህን በምሳሌ ሲያስረዱም ቦክስ በትንሽ በጀት በአፍሪካ እና በዓለም መድረክ ኢትዮጵያን መወከል ይቻላል ይላሉ፡፡ «ከተመሠረቱ ረጅም ዓመታትን ያስቆጠሩ ክለቦች በየዓመቱ ብዙ ገንዘብ ለእግር ኳስ ቢያፈሱም ውጤት አልባና ሀብትን ማባከን ብቻ ሆኖ ቀርቷል» የሚሉት ኮማንደር ፀጋሥላሴ፣ እነዚህ ክለቦች በአትሌቲክስ ውጤታማና ሀገርን ማስጠራት የሚችሉ ስፖርተኞችን ቢያፈሩም ለስፖርቱ የሚመድቡት ገንዘብ ከእግር ኳስ ጋር ሲነጻጸር የሰማይና የምድር ያህል መሆኑን ያስቀምጣሉ፡፡

አትሌቲክሱ ለቁጥር የሚታክቱ ታሪክ ሠሪ ስፖርተኞችን በየጊዜው እያፈራ የዓለም መድረክን መቆጣጠር ቢችልም የክለቦች ትኩረት እንደ እግር ኳሱ እንዳልሆነና ብዙ መሥራት እንደሚጠበቅባቸውም ያስረዳሉ፡፡ ለቦክስና ብስክሌትም የሚመጥናቸውን ድጋፍና ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ያስቀምጣሉ፡፡ «እግር ኳስ ላይ በርካታ ሚሊዮን ብር እያወጡ የቦክስ ክለብ የሌላቸውና ፍቃደኛ ያልሆኑ ክለቦችም ቁጥራቸው ጥቂት የሚባል አይደለም፡፡ የሚያስገርመውና የሚያንገበግበው ደግሞ ድሮ በቦክስ ስፖርት ታዋቂና ሀገርን መወከል የቻሉ ስፖርተኞችን ያፈሩ ክለቦች የቦክስ ክለብን አለመያዛቸው ነው፡፡» በማለትም ቁጭታቸውን ይገልፃሉ፡፡

በኦሊምፒክ መድረክ የሀገርን ክብርን አጉልቶ ለማሳየት ሁሉም ክለቦች የኦሊምፒክ ስፖርት የሆኑትን ቦክስ፣ ብስክሌትና ወርልድ ቴኳንዶን የመሳሰሉ ስፖርቶችን መያዝ አለባቸው የሚል አቋም ያላቸው ኮማንደር ፀጋሥላሴ፣ እንደ ማሳያም ድሬዳዋ ከነማ ቦክስ ስፖርትን በመያዝ ውጤታማ እንደሆነና ሀገርን መወከል የቻሉ ስፖርተኞችን ማፍራቱን ይጠቅሳሉ፡፡

ስፖርቶቹ ብዙ ገንዘብን የማይጠይቁና የሀገርን ስም በዓለም መድረክ ማስጠራት የሚችሉ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ የሚናገሩት ኮማንደር ፀጋሥላሴ፣ በተለይም የቦክስ ስፖርት ተወዳጅነት እንደመሆኑ በሁሉም ክለቦች ቢታቀፍ ደጋፊዎች ደስተኛ እንደሚሆኑ ይጠቁማል። በኦሊምፒክ ከመሳተፍም በላይ ወጣቱን ለመያዝና ጤናማ ኅብረተሰብን ለመፍጠር ቦክስ ትልቅ አቅም እንዳለውም አክለዋል፡፡

«ከመንግሥት ካዝና ለስፖርቱ የሚወጣው ገንዘብ በአግባቡ ለኦሊምፒክ ስፖርቶችና ውጤትን ማምጣት ለሚችሉ ስፖርቶች መዋል አለበት፡፡» በማለትም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡